# ጽድቀ ሃይማኖት ።

## የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ውሳኔዎች

ከሮጀር ካውሊ የተዘጋጀ

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በ፵፩ኛው ዘመን መንግሥት
ይህ መጽሐፍ በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ብ. ሰ. ቀ. ኃ. ሥ. ማ. ቤት ታተመ ።

በሙሉም በከፊልም ለማሳተም መብቱ የመንበረ ጸባዖት
ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ነው ።

# ም ስ ጋ ና ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ይህን መጽሐፍ አይተው ፣ መርምረው ቃሉን ስላረሙልኝና በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ትጋትና ኪሣራ ታትሞ እንዲወጣ ስለ ፈቀዱ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ ። ነገር ግን በመጽሐፉ ውስጥ ስሕተት ቢገኝ ኃላፊነቱ የእኔ ነው እንጂ ፣ የእርሳቸውም ሆነ በምክር የረዱኝ የሌሎችም አይደለም ።

አዘጋጁ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ ።


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መቅድም . . . . . . . . . . . . . . . . | ፯ |
| | መግለጫ . . . . . . . . . . . . . . . . | ፱ |
| ፩ | በብሉይ ኪዳን ዘመን የአይሁድ ሃይማኖት ፤ . . . | ፲፩ |
| ፪ | ሙሴ ወልደ ማይሞን የጻፈው የአይሁድ ሃይማኖት ውሳኔ ፤ . . . . . . . . . . . . . | ፲፫ |
| ፫ | የእስልምና መሠረት ፤ . . . . . . . . . | ፲፭ |
| ፬ | በሐዋርያት ዘመን የክርስትና ትምህርት ፤ . . . | ፲፯ |
| ፭ | የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ፤ . . . . . . . | ፳፩ |
| ፮ | ሐዋርያዊ ሥርዓተ ሃይማኖት ፤ . . . . . . . | ፴፩ |
| ፯ | አመክንዮ ዘሐዋርያት ፤ . . . . . . . . | ፴፯ |
| ፰ | የኒቅያ ጸሎተ ሃይማኖት ፤ . . . . . . . . | ፵፰ |
| ፱ | ጸሎተ ሃይማኖት ዘአፍራቅያ ፤ . . . . . . . | ፶፩ |
| ፲ | የአፄ ገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ ፤ . . . . . | ፷፭ |
| ፲፩ | የቅዱሳት መጻሕፍት ቍጥር ፤ . . . . . . . | ፸፩ |
| ፲፪ | የቤተ ክርስቲያን አንድነት ። . . . . . . . | ፸፯ |


www.ethiopianorthodox.org

# መ ግ ለ ጫ

« ጽድቀ ሃይማኖት » በሚል አርእስት የተጻፈው የልዩ ልዩ ሃይማኖት ውሳኔዎችንና የአዘጋጁን የግል አስተያየት የሚገልጽ ይኸን መጽሐፍ ስናሳትም ፣ በዋጋው እንጠቀምበታለን ከማለት ይልቅ መጽሐፉ በሰው እጅ እንዲውል ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ነው ።

ዘመናችን ዘመነ ብርሃን ስለሆነ የድርሰቱ ማዕበል በብዛት የሚጐርፍበት ፤ ምሥጢራት የሚገለጡበት ጊዜ ሁኗል ። ስለዚህ የውጪም የአገርም ሊቃውንት በብዛት ሲጽፉ አዲስ ድርሰትም ሲደርሱ ይገኛሉ ። በዚህ በድርሰት ክፍላችን የኛን የግላችንን ድርሰት ፤ እንዲሁም የልዩ ልዩ ሰዎችን ድርሰትና አስተያየት እየመረመርን ለማሳተም በወሰድነው እርምጃ መሠረት አሁንም ይኸን « ጽድቀ ሃይማኖት » ተብሎ የተሰየመ ጽሑፍ ከአዘጋጁ መብት በማግኘት እናሳትማለን ።

ይኸን መጽሐፍ ያዘጋጁ ሊቅ ሚስተር ሮጀር ካውሊ የተባሉ እንግሊዛዊ ናቸው ። እርሳቸውም ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እርምጃ ከፍ ያለ ቅን አስተያየት ያላቸውና በነፃም በማገልገል የሚገኙ ሲሆኑ ፤ በመጻሕፍትም በኩል ቤተ ክርስቲያናችንን ለማበልጸግ ታጥቀው የተነሡ ጥሩ ደራሲ ናቸው ። ስለዚህ ይኸን ጽሑፍ አዘጋጅተው አብያተ ክርስቲያናትን ወደ አንድነት ጐዳና እንደሚመራ አምነው ካቴድራሉ እንዲያሳትመው ስላቀረቡልን በዚህ መልክ ታትሞ ወጥቷል ።

የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፩ ።

# በብሉይ ኪዳን ዘመን የአይሁድ ሃይማኖት ።

እስከ ዛሬ ድረስ አይሁድ «እስራኤል ሆይ ፥ ስማ ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው ፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ፥ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ---» እያሉ ሲጸልዩ ኖረዋል (ዘዳግም ም. ፮ ቁ. ፬—፭ ፤ እንዲሁም መጽሐፈ ሃይማኖተ አበው « መቅድመ ኵሉ አፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ» ይላል) ፤ ይኸውም አንድ የሃይማኖት መሠረታዊ ዐዋጅ ነው ። እንዲህ ሲሉ በብዙ አማልክት አለማመናቸውን ከመግለጥ በላይ የሰውን ወንድማማችነት ፥ እግዚአብሔርም በፍጥረቱ ላይና በሰው አካሄድ ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን አረጋግጠው ይናገራሉ ። እንዲሁም እስራኤላውያን የፍሬያቸውን በኵራት ባቀረቡ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያደናቸው ያደረገውን ውለታ ሲያመሰግኑ ይናገሩ ነበር ፥

« አባቴ የተቅበዘበዘ ሶርያዊ ነበረ ፤ በቍጥር ጥቂት ሳለ ወደ ግብፅ ወረደ ፥ በዚያም ተቀመጠ ፤ ታላቅ የሆነ የበረታም ቍጥሩም የበዛ ሕዝብ ሆነ ። ግብፃውያንም ክፉ ነገር አደረጉብን ፥ አስጨነቁንም ፥ በላያችንም ጽኑ ከባድ ሥራን ጫኑብን ፤ ወደ አባቶቻችንም አምላክ ወደ እግዚአብሔር ጮኽን ፤ እግዚአብሔርም ድምፃችንን ሰማ ፥ ጭንቀታችንንም ድካማችንንም ግፋችንንም አየ ፤ እግዚአብሔርም በጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ ፥ በታላቅም ድንጋጤ ፥ በተአምራትም ፥ በድንቅም ከግብፅ አወጣን ፤ ወደዚህም ሥፍራ አገባን ፤ ወተትና ማር የምታፈስሰውንም ይህችን ምድር ሰጠን ። አሁንም እነሆ ፥ አቤቱ ፥ አንተ የሰጠኸኝን የምድሪቱን ፍሬ በኵራት አቅርቤአለሁ ።» ( ዘዳግም ም. ፳፮ ቁ. ፭—፲፩ ፤ ደግሞም ኢያሱ ፳፬ ቁ. ፩—፲፬ ፤ መዝሙር ፻፬ና ፻፭ ተመልከት ።)

ሆኖም እነዚህ ቃሎች የሃይማኖት ውሳኔዎች አይደሉም ። ሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔርን ነገር ተረድተው እርሱ ያደረገላቸውን በማሞገስ የታዘዘላቸውን እንዲፈጽሙ የሚያዝዙ ቃሎች

www.ethiopianorthodox.org

ናቸው እንጂ ፤ ከሃይማኖት የወጡትን ለመለየትና ለማውገዝ የተጻፉ አልነበሩም ። የእግዚአብሔር ሕግ ምን ይላል ? እያሉ የአይሁድ መምህራን የሚከተለውን መልስ አቅርበዋል ፤

«ረቢ ሲምላይ እንዲህ አለ ፤ ለሙሴ የተሰጡ የአሪት ትእዛዛት ፮፻፲፫ ናቸው ። ዳዊት በእሥራ አንድ ትእዛዛት አጠቃለላቸው ። በቅንነት ተመላለስ ፤ ጽድቅን አድርግ ፤ እውነትን ተናገር ፤ በአንደበት አትሸንግል ፤ ክፋትን አታድርግ ፤ አትስደብ ፤ ኀጢአተኛን ናቅ ፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን አክብር ፤ የማልኸውን አትካድ ፤ በአራጣ አታበድር ፤ መማለጃን አትቀበል ይላልና ፤ (መዝሙር ፲፭) ።

ኢሳይያስም በስድስት ትእዛዛት አጠቃለላቸው ። በጽድቅ ተመላለስ ፤ ቅን ነገርን ተናገር ፤ የሽንገላን ትርፍ ናቅ ፤ መማለጃን አትጨብጥ ፤ ክፋትን አታዳምጥ ፤ ክፋትን አትመልከት ይላልና (ኢሳ. ፴፫ ቊ. ፲፭) ።

ሚክያስም በሦስት ትእዛዛት አጠቃለላቸው ። ፍርድን አድርግ ፤ ምሕረትን ውደድ ፤ ከእግዚአብሔር ጋር በትሕትና ተመላለስ ይላልና (ሚክ፡ ፮ ቊ. ፰) ።

ኢሳይያስም በሁለት ትእዛዛት አጠቃለላቸው ። ፍርድን ጠብቁ ፤ ጽድቅን አድርጉ ይላልና (ኢሳ. ፶፮ ቊ. ፩) ።

አሞጽና ዕንባቆም በአንድ ትእዛዝ አጠቃለሉአቸው ። አሞጽ እኔን (እግዚአብሔርን) ፈልጉ ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ ይላል ። (አሞጽ ፭ ቊ. ፬) ። ዕንባቆምም ጻድቅ በእምነቱ በሕይወት ይኖራል ይላል (ዕንባቆም ፪ ቊ. ፬) ። »

ይህና ይህን የመሰለ የብሉይ ኪዳን ፤ የአይሁድም መምህራን ቃል የሕግ መምሪያና ማስተማሪያ ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ከተደነገጉት የሃይማኖት ውሳኔዎች የተለዩ ናቸው ።

ምዕራፍ ፪ ።

## ሙሴ ወልደ ማይሞን የጻፈው የአይሁድ ሃይማኖት ውሳኔ ።

ሙሴ ወልደ ማይሞን ፩ሺ፻፴፯—፩ሺ፪፻፬ ዓ. ም. የኖረ ታላቅ የአይሁድ ሃይማኖት መምህርና የትርጉም መጽሐፍ ደራሲ ነበረ ። ፲፫ቱ የሃይማኖት አዕማድ በሚለው አርእስት የሚከተለውን ጻፈ ፤ በአንቀጽ ፩—፭ የእግዚአብሔርን መኖር ፤ በአንቀጽ ፮—፱ የእግዚአብሔርን መገለጥ ፤ በአንቀጽ ፲—፲፫ የእግዚአብሔርን እገዛዝ ያስረዳል ።

«፩ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ እርሱ ለተፈጠረው ሁሉ ፈጣሪና መሪ እንደሆነ ፤ ብቻውንም ሆኖ የተሠራውን ሁሉ የሠራው ፤ የሚሠራውና ወደፊት የሚሠራው እንደሆነ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፪ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ እርሱ አንድ እንደሆነ ፤ የትም ቢሆን የእርሱን አንድነት የመሰለ እንደሌለ ፤ ብቻውን ሆኖ የነበረ ፤ ያለና ወደ ፊት የሚኖር አምላካችን እንደሆነ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፫ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ አካል እንደሌለው ፤ በግዙፍነት የተወሰነ እንዳይደለ ፤ በጭራሽም መልክ እንደሌለው በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፬ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ እርሱም መጀመሪያውና መጨረሻው እንደሆነ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፭ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ ለእርሱ ብቻ መጸለይ እንደሚገባ ፤ ከእርሱ በቀር ለሌላ መጸለይ እንደማይገባ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፮ የነቢያት ቃሎች ሁሉ የታመኑ እንደ ሆኑ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፯ ለመምህራችን ለሙሴ ሰላም ይሁንለት ፤ የእርሱ ትንቢት የታመነ እንደሆነ ፤ ለቀደሙትና በኋላው ለመጡት ነቢያት ራስ እንደሆነ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።



www.ethiopianorthodox.org

፰ ለመምህራችን ለሙሴ ሰላም ይሁንለት ፤ አሁን በእጃችን የሚገኘው ኦሪት በሙሉ ለእርሱ የተሰጠ እንደሆነ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፱ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ ይህ ኦሪት እንደማይለወጥ ፥ ከእርሱም ሌላ ኦሪት እንደማይሰጥ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፲ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ ልባቸውን ልባቸውን የሠራ ፥ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል እርሱ ነው እንደሚል ፥ እርሱ የሰዎችን አድራጎት ሁሉና አሳባቸውን ሁሉ እንደሚያውቅ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፲፩ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ ትእዛዛቱን ለሚጠብቁ መልካሙን እንደሚሰጥ ፥ ትእዛዛቱንም የሚተላለፉትን እንደሚቀጣ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

፲፪ የመሲሑን መምጣት በፍጹም እምነት አምናለሁ ፤ ምንም ቢዘገይ ከቀን ወደ ቀን እጠባበቀዋለሁ ።

፲፫ የፈጣሪ ስም የተባረከ ይሁን ፤ መታሰቢያው ዘወትርና ለዘላለም ታላቅ ይሁን ፤ እርሱን ደስ በሚያሰኘው ጊዜ ሙታን ሕያዋን ሆነው እንደሚነሡ በፍጹም እምነት አምናለሁ ።

እግዚአብሔር ሆይ ፥ ማዳንህን እጠባበቃለሁ ። »

ምዕራፍ ፫ ።

# የእስልምና መሠረት ።

ክርስቲያኖች የክርስትና መገኛ እናት የሆነውን የአይሁድን ሃይማኖት ማወቅና ማክበር ይገባቸዋል ። የእስላም ሃይማኖት ግን የተለየ ነውና የአይሁድ የክርስቲያንም ሃይማኖት እናት ወይም ልጅ ተብሎ ሊጠራ አይችልም ። ሆኖም ከአይሁድና ከክርስቲያን ሃይማኖት ውሳኔዎች ጋር እንዲነጻጸር የእስልምናን መሠረት በአጭሩ ጽፈነዋል ።

«የእስልምና የእምነት መሠረቶች ሰባት ናቸው ፤

፩ ፥ በአላህ አንድነት ማመን ፥

፪ ፥ በእርሱ መላእክት ሁሉ ማመን ፥

፫ ፥ በእርሱ መጻሕፍት ሁሉ ማመን ፥

፬ ፥ በእርሱ ነቢያት ሁሉ ማመን ፥

፭ ፥ በትንሣኤ ቀን ማመን ፥

፮ ፥ በፍርድ ቀን ማመን ፥

፯ ፥ የምናደርገውን ሁሉ የምናደርግበት ኃይል ከአላህ የመነጨ እንደሆነና ኃይሉ የእርሱ ቢሆን በምናደርገው ሁሉ ኃላፊነት የራሳችን እንደሆነ ማመን ።

የእስልምና መሠረታውያን ሕጎች አምስት ናቸው ፤

፩ ፥ ከአላህ በቀር አምላክ የለምና መሐመድ መልእክተኛው ነው ብሎ መናገር ፥

፪ ፥ በቀን አምስት ጊዜ በተወሰኑ ጊዜያት መጸለይ ፥

፫ ፥ ለሙሉ ዓመት ሀብት ሆኖ ከተቀመጠው ወርቅና ብር አንድ ዓርባኛውን አንሥቶ ለታወቁ ድኆች መስጠት ( ዘካት) ፥

፬ ፥ ረመዳን በተባለው ወር በቀን ሁሉ መጾም ፥

፭ ፥ የሚቻል ከሆነ በሕይወት ዘመን ውስጥ አንድ ጊዜ ወደ መካ መሔድ (ሃጂ) ። »

የአላህ መላእክት ሲል እነርሱ ጂብሪል (ገብርኤል) ፥ ሚካኢል (ሚካኤል) ፥ እስራፊል (ሱራፌል) ፥ ዕዝራኢል ደግሞም ብዙ ሌሎች ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

የአላህ መጻሕፍት ሲል እነርሱ ተውራት (ብሉይ ኪዳን)፣ ዘቡር (መዝሙረ ዳዊት)፣ ኢንጂል (አዲስ ኪዳን)፣ ቅዱስ ቍርዓንም ናቸው ። በእውነተኛው መልክ የሚገኘው ግን ቍርዓኑ ብቻ ነው ይላሉ ።

የአላህ ነቢያት ሲል ዋነኞቹ አዳም፣ ኖኅ፣ ኢብራሂም (አብርሃም)፣ ሙሳ (ሙሴ)፣ ኢሳ (ኢየሱስ)፣ መሐመድም ናቸው ። ከሁሉ ብልጫ ያለው መሐመድ ነው ይላሉ ።

ምዕራፍ ፱ ።

# በሐዋርያት ዘመን የክርስትና ትምህርት ።

የክርስቲያን መታወቂያ ምን ጊዜም አንድ ነው ። ሰው ሁሉ ከአባት ከእናት ይወለዳል ፤ ክርስቲያን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታና መሪነት ተቀብሎ ዳግም የተወለደ፣ የእግዚአብሐርንም ልጅነት የወረሰ ነው ። (ዮሐ. ፫ ቍ. ፩-፳፩፣ ሮሜ ፰፣ ኤፌ. ፩ ቍ. ፲፰—፪ ቍ. ፳፪) ።

ሆኖም የክርስትና ትምህርት የቀና እንዲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ የክርስቲያን መሪዎችና ሊቃውንት የሃይማኖት ውሳኔዎችን ወስነዋል ። ከሁሉም የታወቀው የኒቅያ ውሳኔ ነው ። ነገር ግን በሐዋርያት ዘመን አጫጭር የሃይማኖት መግለጫ ውሳኔዎች ይታወቁ ጀመር ። ተጠማቂዎች በተጠመቁበት ጊዜ «ኢየሱስ ጌታ ነው» እያሉ በኢየሱስ ማመናቸውንና ለሌላ ጌታ አለመገዛታቸውን ያረጋግጡ ነበር (፩ ቆሮ. ፲፪ ቍ. ፩-፫፣ የሐዋ. ፲፱ ቍ. ፭) ።

ሐዋርያት ክርስቶስ አድኖናል፣ ወንጌልን አድምጣችሁ እመኑ ብለው ሲያውጁ ነበር ፤ ቃላቸውም በግሪክ ቋንቋ ኪሪግማ (ዐዋጅ) ተባለ (፩ ቆሮ. ቍ. ፲፰-፳፭፣ የሐዋ. ፲፮ ቍ. ፳፱-፴፩) ። ደግሞም አምናችሁ እንደሆነ በቅዱስ ኑሮ ተመላለሱ ብለው ምእመናንን ያስተምሩ ነበር ፤ ይኸውም ዲዳኪ (ትምህርት) ተባለ (፪ ጢሞ. ፬ ቍ. ፩-፭ ፤ ፩ ጴጥ. ፩ ቍ. ፲፫-፳፩) ።

ቅዱስ ጳውሎስም እግዚአብሔር እየገለጠለት እንጂ እየፈጠረ አልጻፈም (ገላ. ፩ ቍ. ፲፩-፲፯)፣ ደግሞም ከሐዋርያትና ከሌሎች ምእመናን አፍ ጨምሮ ተማረ (ገላ. ፩ ቍ. ፲፰-ም. ፪ ቍ. ፲) ። እንግዲህ የጳውሎስን መልእክቶች ስናነብ ፤ ጌታችን፣ ሐዋርያትና ሌሎች ምእመናን የተናገሩትን ቃላት፣ የዘመሩትን መዝሙር፣ ያስተማሩትን ግብረ ገብነት እናገኝበታለን፣ የጋራ ቅርስና ትውፊት ነበረ ።

## ፩. ሐዋርያት ያስተላለፉት ቃል (ፓራዶሲስ) ።

ጳውሎስ የተቀበልሁትን ሰጠኋችሁ ብሎ በ፩ ቆሮ. ፲፭ ቍ. ፫-፰ የክርስቶስን ትንሣኤ የመሰከሩትን ዘርዝሮአል ፤ በ፩ ቆሮ. ፲፩ ቍ. ፳፫-፳፮ የጸሎተ ሐሙስን ነገር ገልጦ ተናግሮአል ። ከሐዋርያትም



www.ethiopianorthodox.org

ከጌታም ተቀብሎ ነገሩን ለምእመናን እንዳስተላለፈ አመለከተ ። እንዲሁ ፩ ቆሮ. ም. ፲፩ ቍ. ፪ ፤ ፪ ተሰ. ፪ ቍ. ፲፭ ተመልከት ።

## ፪. የሃይማኖት መግለጫ ውሳኔ ።

በሮሜ ፩ ቍ. ፫-፬ ጳውሎስ ከሃይማኖት ውሳኔ የጠቀሰ ይመስላል ፤

« ይህ ወንጌል ስለ ልጁ ነው ፣
በሥጋ ከዳዊት ዘር የተወለደ ፣
እንደ ቅድስና መንፈስ ከሙታን በመነሣቱ ምክንያት ፣
በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የተገለጠ ነው ። »

እንዲሁም ሮሜ ፲ ቍ. ፱-፲ ፣

«ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር ፣
እግዚአብሔር ከሙታን እስነሣው ብለህ ብታምን ትድናለህ » ይላል ።

(ደግሞም ፩ ቆሮ. ፲፪ ቍ. ፫ ፣ ፪ ቆሮ. ፬ ቍ. ፭-፯ ፣ ተመልከት) ።

## ፫. የክርስቲያን መዝሙሮች ።

በሐዋርያት ዘመን ምእመናን እንደ ዘመሩ የታወቀ ነው(ቈላ.፫ ቍ. ፲፯ ) ፤ ከመዝሙረ ዳዊት ሳይዘምሩ አልቀሩም ፣ እንዲሁም የራሳቸውን መዝሙሮች ጸፉና ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን መዝሙሮች የጠቀሰ ይመስላል ።

ለምሳሌ ኤፌ. ፭ ቍ. ፲፬ «ስለዚህ ይላል» ብሎ ይጀምራል ፣ ሆኖም ቃሉ ከብሉይ ኪዳን አልተጠቀሰምና

«አንተ የምትተኛ ንቃ ፣
ከሙታንም ተነሣ ፣
ክርስቶስም ያበራልሃል » ሲል ቃሉ የመዝሙር ቃል የሆነ ይመስላል ።

እንዲሁም ፊል. ፪ ቍ. ፮—፲፩ ፣

«፮ ፣ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ፣
ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ፣
መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም ።
፯ ፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ ፣
በሰውም ምሳሌ ሆኖ ፣
ራሱን ባዶ አደረገ ።
፰ ፣ በምስሉ እንደ ሰው ተገኝቶ ፣
ራሱን አዋረደ ፣



ለሞትም የታዘዘ ሆነ ፣
(ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ ! ) ።
፱ ፣ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው ፣
ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ፣
ስም ሰጠው ።
፲ ፣ ይኸውም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ
በኢየሱስ ስም ፣
እንዲንበረከኩ ነው ፤
፲፩ ፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር አብ ክብር ፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ብሎ ፣
ምላስ ሁሉ እንዲመሰክር ነው » ፣

የእነዚህ መዝሙሮች አጻጻፍ የጳውሎስ የሆነ አይመስልምና ከሌሎች ምእመናን ተደርሰው ይሆናል ። ( ደግሞም ፩ ጢሞ. ፫ ቍ. ፲፮ ፣ ፪ ጢሞ. ፪ ቍ. ፲፩-፲፫ ፣ ቲቶ ፫ ቍ. ፬-፯ ፣ ቈላ. ፩ ቍ. ፲፭-፳ ተመልከት) ።

## ፬ የጌታችን ቃላት ።

ጳውሎስ የጌታችንን ቃል ይጠቅሳል (፩ ቆሮ. ፯ ቍ. ፲ ፤ ፱ ቍ. ፲፬ ፤ ፲፩ ቍ. ፳፫ ፤ ፩ ተሰ. ፬ ቍ. ፲፭-፲፮፤ የሐዋ. ፳ ቍ. ፴፭ ። ደግሞም ፩ ቆሮ. ፯ ቍ.፳፭ ተመልከት ፤ «ስለ ደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም» ሲል የክርስቶስ ትእዛዞች የተጻፉበትን ጽሑፍ በእጁ የያዘ ይመስላል) ።

ከዚህም በላይ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ ብሎ ምእመናን የጌታችንን አብነት እንዲከተሉ ያሳስባል (፩ ቆሮ. ፲፩ ቍ. ፩) ።

## ፭ የክርስቲያን ምእመናን አመላለስ (ፓራይነሲስ) ።

ምእመናን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነው አባታቸውን ደስ ማሰኘት ይገባቸዋልና ሐዋርያት የቅድስናን ኑሮ አስረድተው አስተማሩ ( ፩ ተሰ. ፬ ቍ. ፩-፱ ተመልከት ) ።

አራት ዋና አርእስቶችን ይዘው ይመከሩ ነበር፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ፣

፩ ፣ ከፋታችሁን አስወግዱ ፣ የክርስቶስን ነገር ልበሱ (ይዛችሁ ልመዱ) ፤
፪ ፣ እንደሚገባችሁ ተገዙ ፤
፫ ፣ ጸልዩ ፣ ጽኑ ፣ ትጉ ፤
፬ ፣ ዲያብሎስን ተቃወሙት ።

www.ethiopianorthodox.org

በእነዚህ አርእስተ ትምህርት ጳውሎስና ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ተስማምተውባቸዋል ። ( ይህን ለማረጋገጥ ቈላ. ፫ ቍ. ፰—፲ ቍ. ፲፪ ፤ ኤፌ. ፬ ቍ. ፳፪—፮ ቍ. ፲፰ ፤ ፩ ጴጥ. ፩ ቍ. ፩—፬ ቍ. ፲፩ ፣ ያዕ. ፩ ቍ. ፩—፬ ቍ. ፲ እንጻጽር) ።

፮ ከብሉይ ኪዳን ጥቅስ የክርስቶስን ነገር ማስረዳት ።

ክርስቲያኖች መሲሕ ይመጣል የሚለው ትንቢት በኢየሱስ መምጣት ተፈጽሟል እያሉ ለአይሁድ ያስረዱ ነበር ። በበለጠ መጠን እንዲያስረዱአቸው የብሉይ ኪዳንን የትንቢት ቃሎችን አስተዋፅኦ እንደጻፉ ይገመታል ። ለምሳሌ ጳውሎስ (በሮሜ ፱ ቍ. ፴፪—፴፫) ጴጥሮስም (በ፩ ጴጥ. ፪ ቍ. ፮—፰ ) ከኢሳይያስ ፳፰ ቍ. ፲፮ እና ከኢሳ ፰ ቍ. ፲፬ ይጠቅሳሉ ፤ ሁለቱ ብቻቸውን ሆነው ሁለቱን ጥቅሶች መርጠው ያጋጩቸው አይመስልም ። ስለዚህ አይሁድን ለማስተማር ከተዘጋጀ ጽሑፍ ጠቅሰዋቸው ይሆናል የሚሉ ሊቃውንት አሉ ።

ብዙውን ጊዜ በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሱ የብሉይ ኪዳን ማስረጃዎች እነዚህ ናቸው ፦

፩ ፣ የእግዚአብሔርን ማዳንና የመንግሥቱን መቋቋም ለማስረዳት ፣ ኢዩ. ም. ፪—፫ ፣ ዘካ. ም. ፱—፲፬ ፣ ዳን. ም. ፯ ፣ ም. ፲፪ ።

፪ ፣ የክርስቲያን ማኅበር የእግዚአብሔር እስራኤል እንደሆነ ለማስረዳት ፣ ሆሴዕ ፣ ኢሳ. ፯ ቍ. ፩—፱ ቍ. ፯ ፣ ም. ፵ ቍ. ፩—፲፩ ፣ ኤር. ፴፩ ቍ. ፲—፴፬ ።

፫ ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ (አገልጋይ) መከራን ተቀባይነትና አሸናፊነቱን ለማስረዳት ፣ ኢሳ. ፵፪ ቍ. ፩—፵፬ ቍ. ፮ ፣ ም. ፵፱ ቍ. ፩—፲፫ ፣ ም. ፶ ቍ. ፬—፲፩ ፤ ም. ፶፪ ቍ. ፲፫—ም. ፶፫ ቍ. ፲፪ ፤ መዝ. ፳፩ ፤ ፴፫ ፤ ፷፰ ፤ ፻፲፯ ።

አንዳንድ ሊቃውንት «የጌታችን ትምህርት አንድ ነው ፣ የጳውሎስ ትምህርት ሌላ ነው» እስከ ማለት ደርሰዋል ፤ ሐሰት ነው ። ከላይ እንዳ ሳየነው ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋርያትና ምእመናን ተማረ ፤ ከዚህም ይልቅ ከጌታችን ተረዳ ። ጳውሎስ ጴጥሮስ ያዕቆብ ሌሎችም የጋራ የክርስት ናን ትምህርት ቅርስ አስተምረው አስተላለፉት ። ከላይ የተጠቀሰው ብቻ አይደለም ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጥምቀት ፣ ስለ ቍርባን ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፣ ስለ ክርስቶስ ምጽአትና ስለ ትንሣኤ ሙታን ያስተማ ረው ሁሉ የራሱ ፈጠራ ሳይሆን ከጌታችን የተሰጠ ፣ ሐዋርያትም ሌሎ ችም ሁሉ አስተላልፈው ለእኛም ጭምር ያደረሱት ትምህርት ነው ።

ምዕራፍ ፭ ።

# የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ።

## የኢየሩሳሌም ጉባኤ ፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ሐዋርያትን ሄዳችሁ አስተምሩ ብሎ አዘዛቸው ፤ የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በእነርሱ ተጀመረ ። ሳውል (ጳውሎስ) ክርስቶስን በራእይ አየው ፤ ፲፬ ዓመት ቈይቶ በ፵፯ና በ፵፰ ዓ. ም. አንደኛ የስብከት ጕዞን አደረገ ። እስከዚህ ዘመን ድረስ የአይሁድ ዘር የሌላቸው በክርስቶስ ቢያምኑ የኦሪትን ትእዛዝ ይጠብቁ ፣ አይጠብቁ የማለት ክርክር ስለ ተነሣ በ፵፱ ዓ. ም. ገደማ በኢየሩሳሌም ውስጥ አንድ ጉባኤ ተደረገ ።

ታሪኩ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፲፭ ተጻፈና ውሳኔው እንደሚከተለው ነው ፤

«ለጣዖት ከተሠዋ ፣ ከደምም ፣ ከታነቀም ፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል ። »

ይህም ማለት ለጣዖት ከተሠዋ ምግብ (ዘሌዋ. ፲፯ ቍ. ፰—፱) ፣ ከምንዝርናና ካልተፈቀደ ጋብቻ (ዘሌዋ. ፲፰) ፣ ደሙ ያልፈሰሰውን ሥጋ ከመብላት (ዘሌዋ. ፲፯ ቍ. ፲—፲፮) እንዲርቁ ማለት ነው ።

ምእመናን የሆኑ አይሁድና አሕዛብ በልዩ ልዩ ባህላቸው ምክንያት እንዳይቀያየሙ ይህ መሪ ቃል ተጻፈላቸው ።

ሮማውያንም ፣ ክርስቲያኖች ቄሣርን አያመልኩም እያሉ ከሐዲዎችና የመንግሥት ጠላቶች እንደሆኑ አስመስለው አሳደዱአቸው ፤ ይህ መሰደድ የዘወትር ቢሆን ስንኳ ፣ ዘመነ ሰማዕታት በተባለ በነመክስምያኖስና በነዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በረታ (፪፻፹፮-፫፻፭ ዓ. ም. )። በዚህ ዘመን ውስጥ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አልተሰበሰበም ፤ በኋላ ግን መናፍቃን በተነሡ ቍጥር ሊቃውንት ተሰብስበው ትምዘርታቸውን ይመረምሩ ነበር ። የሃይማኖት አወራረስና አጠባበቅ ነገር በሥርዓተ ቅዳሴ ምዕራፍ ፫ አንቀጽ ፳፩—፳፭ ተጻፈ ፣

www.ethiopianorthodox.org

አሥራ አምስት ነቢያት ፣
አሥራ ሁለት ሐዋርያት (ማር. ፫ ቍ. ፲፫—፲፱) ፣
ሰባ ሁለት አርድእት (ሉቃ. ፲ ቍ. ፩) ፣
ወንጌላዊ ሐዋርያና ሰማዕት የሆነ ማርቆስ ፣
ሳዊሮስ ፣ ዲዮስቆሮስ ፣ አትናቴዎስ ፣ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ፣
ቄርሎስ ፣ ጎርጎርዮስና ባስልዮስ ።

አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ የተሰበሰቡ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ፣ መቅዶንዮስን ለማውገዝ በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡ ፻፶ ሊቃውንት ፤ ንስጥሮስን ለማውገዝ በኤፌሶን የተሰበሰቡ ፪፻ ሊቃውንት ፤ እነዚህም የሃይማኖት ጠባቂዎች ናቸው ይላል ።

<u>የኒቅያ ጉባኤ ፤</u>

በ፫፻፲፯ ዓ. ም. (በ፫፻፳፭ እ. ኤ. አ) ፫፻፲፰ ሊቃውንት በኒቅያ ተሰበሰቡ ። የጉባኤው ምክንያት የአርዮስ ትምህርት ነበረ ፤ እርሱም ኢየሱስ አምላካዊ ፍጡር የሆነ ፣ ከእግዚአብሔር ያነሰ ነው ብሎ አስተማረ ።

የጉባኤው ሰብሳቢ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ ነበረ ፤ እርሱም ከቍንስጣና ከቅድስት እሌኒ የተወለደ ፣ ከ፪፻፺፫—፫፻፴፱ ዓ. ም. የነገሠ ክርስቲያን ቄሣር ነው ። አፈ ጉባኤው ቅዱስ አትናቴዎስ ነበረ ፤ እርሱም ፪፻፺፰—፫፻፷፭ ዓ. ም. የኖረ ፣ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት የሆነ ነው ።

እነዚህ ሊቃውንት የአርዮስን ነገር ሰምተው ፣ እግዚአብሔር ወልድ ጥንት ተወለደ እንጂ ፍጡር አይደለም ፣ በመለኮታዊ ባሕርይ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ ነው ብለው አርዮስን አወገዙት ፤ (ንዜኑ ህላዌሁ ለአብ ምስለ ወልዱ ፣ ቅዳሴ ሠለስቱ ምዕት ፲፰ ፣ የአብን ከልጁ ጋር ህላዌውን እንናገራለን ) ። የቀና ሃይማኖት እንዲታወቅ ሊቃውንት የሚከተለውን ውሳኔ ጻፉ ፣

«የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ በፈጠረ ፣ አንድ አምላክ በሚሆን ፣ ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።

ከአብ ህላዌ በሆነ ፣ ብቻውን ሆኖ በተወለደ ፣ የአብ ልጅ በሚሆን ፣ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ፤ እርሱም ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ፣ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን የሚሆን ፣ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ ፣ በህላዌው ከአብ ጋር አንድ ፣ የሆነ ፣ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ በእርሱ በኩል የተፈጠረ ነው ።



ስለ እኛ ስለ ሰዎች ፣ እኛንም ለማዳን ወረደ ፣ ሥጋን ለበሰ ፣ ሰውም ሆነ ፣
መከራን ተቀበለ ፣
በሦስተኛው ቀን ተነሣ ፣
ወደ ሰማይ ዓረገ ፣
በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ይመጣል ።
በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።

ከዚህም ጨምረው የአርዮስን ወገኖች አወገዙ ።

« እመቦ ዘይቤ ሀሎ ዘመን ወመዋዕል እምቅድመ ልደቱ ለወልድ እንዘ ኢሀሎ ውእቱ ፤ ( ከመወለዱ በፊት ወልድ የሌለበት ዘመን ነበረ የሚል ቢኖር ) ፤

ወእምዝ ኮነ እንዘ ኢኮነ ፤ ( ካልሆነበት ጊዜ በኋላ ሆነ የሚል ቢኖር ) ፣

አው ዘይቤ እስመ እምካልእ አካል ውእቱ ፤ አው እምካልእ ህላዌ ፤ ( ወይም ከልዩ አካል ፣ ከልዩ ህላዌ የሆነ ነው የሚል ቢኖር) ፣

አው ዘይቤ እስመ ውእቱ ይማስን ፣ ወይትዌለጥ ፤ ( ወይም በስባሽ ተለዋዋጭም ነው የሚል ቢኖር ) ፤

ሐዋርያዊ ቤተ ክርስቲያን አውግዟቸዋል ። »

ሆኖም የአርዮስ ትምህርት ዕለቱን የጠፋ አልነበረምና የቍስጥንጥንያ ጉባኤ እስከሚሰበሰብ ድረስ ክርስቲያኖች የተባሉ የክርስቶስን አምላክነት እያረጋገጡና ተከፍለውም እየካዱ ሲፋጁ ይኖሩ ነበር ።

የኒቅያ ጉባኤ የታላላቅ ጉባኤዎች መጀመሪያ ነበረ ፤ ከፊትና ከኋላ ንዑሳን ነበሩ ፣ ቍጥራቸውም ከፍትሐ ነገሥት መቅድም ላይ እንደ ተጻፈ ነው ።

፩ ፤ ዕንቆራ (፫፻፲፮ ዓ. ም.) ፣ ፈርተው ስለ ካዱ ምእመናን ።
፪ ፤ ቅርጣግና ፣ ስለ ጋብቻና ስለ ካህናት ።
፫ ፤ ግንግራ (፫፻፴፯ ዓ. ም.) ፣ ማግባትና ሥጋን መብላት ርኩስ ነው ብለው ስለ ተሳሳቱ ።
፬ ፤ አንጾኪያ ፣ ስለ ክህነት ፣ ደግሞ ጳውሎስ ሳምሳጢ ክርስቶስ ሰው ብቻ ነው ብሎ ስለ ተነሣ ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፤ ኒቅያ ፣ ከላይ እንደተጻፈው ።

፯ ፤ ሎዶቅያ ፣ ስለ ክህነት ፣ ስለ ብሕትውና ፣ ስለ ጋብቻ ።

፰ ፤ ስርድቅያ (፫፻፴፭ ዓ. ም. ) ፣ የአርዮስን ነገር አንተወውም ብለው ስለ ተበጣበጡ ሰዎች ።

የእነዚህ ጉባኤዎች ውሳኔዎች በመጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ተጽፈው ይገኛሉ ።

## የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ፤

ቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ በነገሠ በ፫፻፸፬ ዓ. ም. (በ፫፻፹፩ እ.ኤ.አ.) ፻፶ ሊቃውንት በቁስጥንጥንያ ተሰበሰቡ ፤ አፈ ጉባኤው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ሜልጥዮስ ነበረ ።

የጉባኤው ዋና ምክንያት ሦስት ነበረ ፤

፩ ፤ የአርዮስ ትምህርት አልጠፋም ነበርና ሊቃውንት የኒቅያን ሃይማኖት አጸኑት ።

፪ ፤ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት መቅዶንዮስ « መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ ህላዌን (ባሕርየ መለኮትን) ተሳታፊ አይደለም ፤ እንደ ሊቀ መላእክት ነው » ብሎ አስተማረ ። ሊቃውንት አይሆንም ብለው ከኒቅያ ሃይማኖት ውሳኔ መጨረሻ ላይ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ከሚለው በኋላ የሚከተለውን በመጨመር የመንፈስ ቅዱስን ነገር አጕልተው አስተማሩ ፤ እንዲህም አሉ ፡

« ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት በሚሰገድለትና በሚመሰገን ፣ ጌታ ፣ ሕይወትን ሰጪ በሚሆን ፣ ከአብ በሠረፀ ፣ በነቢያትም አፍ በተናገረ ፣ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።

በሁሉም ዘንድ በምትሆን ፣ ሐዋርያት በሰበሰቧት ፣ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።

ለኃጢአትም ሥርየት በምትሆነው በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ። የሙታን ትንሣኤንና ፣ የሚመጣውን ዓለም ሕይወት ፣ በተስፋ እንጠባበቃለን ። »

፫ ፤ የሎዶቅያ ጳጳስ አቡሊናርዮስ « እግዚአብሔር ወልድ ከአብ ጋር ትክክል ነው ፤ ነገር ግን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን



በነሣ ጊዜ ነፍስና አእምሮ የሌለውን ሥጋ ለበሰ ፣ ለዚሁም ሥጋ መለኮቱ ነፍስና አእምሮ ሆነው » እያለ አስተምሮ ነበር ። ሊቃውንት ግን « እንዲህ ከሆነ ሰውነቱ ጐደሎ ነውና አይሆንም ፤ ክርስቶስ ቃለ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ከነፍስዋ ነፍስን ከሥጋዋ ሥጋን ነሣ » ብለው አወገዙት ።

ከዚህም በላይ ሰባልዮስ የቅድስት ሥላሴን ነገር አደፋርሶ ስላ ስተማረ የቍስጥንጥንያ ጉባኤ አወገዘው ይባላል ፤ እንጂ ታሪኩ የተ ረጋገጠ አይደለም ። ሆኖም ትምህርቱ የታወቀ ነው ፣

«እግዚአብሔር ፤ አብም ሆኖ የሚሠራበት ጊዜ አለ ፣ ወልድም ሆኖ የሚሠራበት ጊዜ አለ ፣ መንፈስ ቅዱስም ሆኖ የሚሠራበት ጊዜ አለ » እያለ ልዩ አካልነታቸውን አፈረሰ ።

## የኤፌሶን ጉባኤ ፤

ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ በነገሠ በ፬፻፳፫ ዓ. ም. (በ፬፻፴፩ እ. ኤ. አ.) ፪፻ ሊቃውንት በኤፌሶን ተሰበሰቡ ፤ አፈ ጉባኤው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ነበረ ።

የጉባኤው ዋና ምክንያት ሁለት ነበረ ፣

፩ ፣ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ንስጥሮስ እንዲህ ብሎ አስተ ማረ ፤ «ቃል ሥጋ ከመሆኑ በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፣ ከአብ ጋር አንድ መለኮት አለው ። ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን በነሣ ጊዜ ለነሣው ሥጋ የሰው ባሕርይና የሰው አካል ነበ ረው ። እንግዲህ ሁለት አካል ፣ አንዱ በእግዚአብሔር ልጅነቱ ፣ አንዱም በማርያም ልጅነቱ ነበረው ። እመቤታችን ማርያም የክር ስቶስ እናት ናት እንጂ ወላዲተ አምላክ መባል አይገባትም ። »

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ግን ይህን ትምህርት የሚ ቃወም ጽሑፍን አዘጋጅቶ ነበርና ንስጥሮስ ተወገዘ ። ቄርሎስ እን ዲህ አለ ፤

«ክርስቶስ አምላክ ከሆነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መባል ይገባታል ፣ እናቱ ናትና ። ክርስቶስ አንድ ነውና ፤ ከተዋሐዱ በኋላ ህላዌያቱ ሁለት ናቸው ፣ ወይም ሥጋው ይህን አደ ረገ የእግዚአብሔርም ቃል ሌላን አደረገ ብሎ ክርስቶስን የሚከ ፍል ቢኖር የተወገዘ ይሁን ። »

www.ethiopianorthodox.org

ይህን የመሰለውን በብዙ ጸፊና ጽሑፉ በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበው ውስጥ (በተለይም በ፲፩ቱ አንቀጽ በተጻፈ ቃለ ውግዘት)፥ ይገኛል ።

፪ ፥ ጰላግዮስ (ፊላጎስ)፥ የተባለ መነኵሴና ተከታዮቹ እንዲህ ብለው አስተማሩ ፤

«ሀ. አዳም ኃጢአትን ባይሠራ ስንኳ ይሞት ነበር ።

ለ. በአዳም ኃጢአት የተጐዳ አዳም ብቻ ነው ።

ሐ. ሰው ሁሉ ከአዳም የወረሰው የኃጢአት ጉድፍ የለም ።

መ. ወንጌል ሰውን ወደ ሰማይ እንደሚመራ አሪት ደግሞ ሊመራው ይችላል ።

ሠ. ክርስቶስ ሳይመጣ ስንኳ ሰው ሁሉ ያለ ኃጢአት ለመኖር ይችል ነበር ።»

እነ ቅዱስ አውግስጢኖስ ይህን ትምህርት አትተው በጽሑፍ ተቃወሙትና ጰላግዮስ ራሱ ከሞተ በኋላ የኤፌሶን ሊቃውንት የጰላግዮስን ትምህርት የሚያስተምር የተወገዘ ይሁን አሉ ። አውግስጢኖስ እንዲህ አለ ፥

«ሰው ሁሉ በአዳም ምሳሌ ተወልዶአልና በኃጢአት ተረግዞ ይወለዳል (ሮሜ ፭ ቁ. ፲፪—፳፩) ። ከኃጢአት ዝንባሌ ውርስ የሚያነጻው የእግዚአብሔር ጸጋ ነውና ያለዚህ ሰው የሚገባውን ሊያደርግ አይችልም (ኤፌ. ፪. ቁ. ፩—፲፩) ። አሪት ወደ ክርስቶስ የሚመራ ነው እንጂ ሰውን ሕያው ለማድረግ የሚችል አይደለም (ገላ ፫ ቁ. ፳፩—፳፱) ።»

<u>የኬልቄዶን ጉባኤ ።</u>

የቍስጥንጥንያ የአንዱ ገዳም አበ ምኔት የነበረ አውጣኪ እንዲህ ሲል አስተምሮ ነበር ፥

«ቃለ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ እውነቱን ዋጠው ፤ መለኮትና ሥጋ ሳይገናኙ ባሕርያቸው ለየብቻ ነበረ ፥ ከተዋሐዱ በኋላ ግን ሰውነቱ ጠፋ ።»

በ፬፻፵ ዓ. ም. በቍስጥንጥንያ የነበሩ ሊቃውንት ይህን ትምህርት መርምረው ፈረዱበት እንጂ ፍጅጅቱ አላለቀም ። እንግዲህ የሮም ሊቀ ጳጳሳት ልዮን መልሱን (ጦማረ ልዮንን) እንዲህ ሲል አቀረበ ፥



«በክርስቶስ በአንዱ አካል የአምላክነት ህላዌና የሰውነት ህላዌ ተገናኝተው ሳይደባለቁ (እንበለ ቱሳሔ) ይኖራሉ ። ለየህላዌው የራሱ ግብር አለው ። አካልነቱ የሚጸና በሁለቱ ህላዌ ነው እንጂ በአንዱ አይደለም ። ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት (ከትስብእት በፊት) ሁለት ህላዌ ነበረው ወይም ከተወለደ በኋላ አንድ ህላዌ ብቻ ነበረው ማለት አይገባም ።»

ብዙ ክርክር ስለ ተነሣ መርቅያን በነገሠ በ፬፻፵፩ ዓ. ም. በ፬፻፶፩ እ-ኤ-አ) በኬልቄዶን ፮፻፴፮ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰበሰቡ ። ልዮን በመንግሥት በንጉሥም ተደገፈ ።

ዲዮስቆሮስና ተከታዮቹ ተቃወሙት ።

ሊቃውንት «ክርስቶስ ከሁለት ህላዌያት ነው እንበል» ብለው ወደ መስማማት ተቃረቡ ፤ ሆኖም የሮም መልእክተኞች «የክርስቶስ ህላዌያት ሁለት ናቸው ማለት ይገባል » አሉ ። ዓላማቸው የአውጣኪን ነገር ማጥፋት ሲሆን ሳለ ፍሬ ነገሩ የክርስቶስን አንድነት (ዋሕድናውን) ማፈራረቅ ሆነ ። እነ ዲዮስቆሮስ ግን አይሆንም አሉ ፤ ነገር ግን ዛሬም ቢሆን ከኢትዮጵያ ከግብፅ ከሕንድ ከሶርያ ከአርመን አብያተ ክርስቲያናት በቀር ሌሎች ክርስቲያኖች የኬልቄዶንን ውሳኔ ተቀብለውታል ።

<u>የኬልቄዶን ውሳኔ እንዲህ ነው ፤</u>

«ተሊወነ እንከ አበዊነ ቅዱሳን ንሜህር ኵልነ ኅቡረ ፥ ከመ ይደሉ ይትአመኑ በአሐዱ ክመ ወልድ ወእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ወውእቱ ፍጹም በመለኮት ፥ ወፍጹም በትስብእት ።

አምላክ ዘበአማን ፥ ወሰብእ ዘበአማን ዘውእቱ እምነፍስ ነባቢት ወእምሥጋ ።

ኅቡረ ህላዌ ምስለ እብ በመለኮቱ ፥ ወውእቱ ኅቡረ ህላዌ ምስሌነ በትስብእቱ ።

ዘተመሰለ ኪያነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ ።

ዘተወልደ እምአብ እምቅድመ ዓለም በመለኮቱ ፥

ወበትስብእቱሰ ተወልደ በደኃሪ መዋዕል በእንቲአነ ወበእንተ መድኃኒትነ እማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ።

ወይደሉ ይትአመኑ ከመ አሐዱ ወውእቱመ ክርስቶስ እግዚእ ወልድ ዋሕድ በክልኤ ባሕርያት ፥

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ዘእንበለ ቱሳሔ ወኢውላጤ ፣ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢቡዓዴ ፤
እንዘ ኢይጠፍእ ፍልጠተ ባሕርያት በእንተ ተዋሕዶቶሙ
ወባሕቱ እንዘ ይትዐቀቡ ዘዘዚአሆሙ በክልኤ ባሕርያት
ወእንዘ ይከውኑ (ወከዊኖሙ) አሐደ አካለ ወአሐደ ህላዌ ፤
ኢንፋቅ ወኢክፋል ለኀበ ክልኤ አካለት ፣

አላ አሐዱ ክመ ወልድ ዋሕድ እግዚአብሔር ቃል እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

በከመ ቀዲሙ መሀሩነ ነቢያት
ወለሊሁ ክርስቶስ እግዚእ መሀረነ
ወተወፈይናሁ እምተአምኖተ ሃይማኖት ዘአበዊነ ። »

<u>ትርጓሜው እንዲህ ነው ፤</u>

«እንግዲህ ሁላችን በአንድ ልብ ሆነን ቅዱሳን አባቶቻችንን ተከትለን በማይለወጥ በአንዱ ልጅና በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊታመኑ እንደሚገባ እናስተምራለን ።

በመለኮት ፍጹም ነው ፣ በሰውነትም ፍጹም ነው ።

በእውነት አምላክ ነው ፣ በእውነትም ከነባቢት ነፍስና ከሥጋ የሆነ ሰው ነው ።

በመለኮቱ ከአብ ጋር ህላዌው አንድ ነው ፣ በሰውነቱም ከእኛ ጋር ህላዌው አንድ ነው ።

ከኃጢአት በቀር እኛን የመሰለ ፤
በመለኮቱ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደ ፣

በኋለኛው ዘመን ግን በሰውነቱ ስለ እኛ ፣ እኛንም ለማዳን
አምላክን ከወለደች ከድንግል ማርያም ተወለደ ።
መደባለቅ ፣ መለወጥ ፣ መለየት ፣ መራራቅ ሳይኖር
በሁለት ባሕርያት የሆነ ፣

አንድ ልጅ ጌታ ክርስቶስ አንድና የማይለወጥ እንደሆነ ሊታመኑ ይገባል ፤

ስለ መዋሐዳቸውም የባሕርያት መለየት ሳይጠፋ
አንድ አካልና አንድ ህላዌ በመሆናቸው



በሁለቱ ባሕርያት የየራሳቸው ገንዘብ ተጠብቆ ይኖራል ፤

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል አንዱ የማይለወጥ ልጅ አንድ ነው እንጂ

በሁለት አካላት የተለየና የተከፈለ አይደለም ።
ይኸውም አስቀድሞ ነቢያት እንዳስተማሩን ፣
ራሱ ክርስቶስ እንዳስተማረንና
ከአባቶቻችን ሃይማኖት ውሳኔ እንደ ተቀበልነው ነው ። »

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ውሳኔና በተለይም ሁለት ባሕርያት ማለትን አንቀበለም ብለው ተለዩ ።

ከቀሩቱ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ሦስት መጥቀስ ይበቃል ፤ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ተከታዮቹ ሁሉ እስካሁን ከተቈጠሩት ጉባኤዎች ሌላ በተጨማሪ የሚቀጥሉትን ጉባኤዎች እንደ ዓቢይ ጉባኤዎች ይቈጥሩአቸዋል ።

<u>ሁለተኛ የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ።</u>

በ፭፻፶፫ ዓ.ም. ፻፷፭ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው የንስጥሮስን ትምህርት ይደግፋታል በተባሉ በ፫ መጻሕፍት ላይ ፈረዱ ።

<u>ሦስተኛ የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ።</u>

በ፮፻፹፫ ዓ. ም. የልዮን ወገኖች ከሚሆኑ ፪፻፹፱ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰበሰቡ ።

«የክርስቶስ የአምላክነት ፈቃድና የሰውነት ፈቃድ አንድ ናቸው» ብለው ያስተማሩ ሰዎች ስለ ተነሡ ፣ ሊቃውንት «አንድ ፈቃድ ማለት አንድ ባሕርይ ማለትን ያስከትላልና የዲዮስቆሮስን ትምህርት ይመስላል ፣ አይሆንም» አሉ ።

<u>ሁለተኛ የኒቅያ ጉባኤ ።</u>

በ፯፻፹፯ ዓ. ም. የተሰበሰቡ ሊቃውንት የአምልኮንና የጸጋን ስግደት ለይተው አስተማሩ ።

ምን ጊዜም የሃይማኖት ክርክር ተጨርሶ አላለቀም ። ለምሳሌ «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርፃል» ከማለታቸው በላይ « ከወልድም ደግሞ ይሠርፃል» ብለው ይህን ቃል ወደ ውሳኔ ያገቡት ነበሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ክርክር ምክንያት በ፩ሺህ፶፬ ዓ. ም. ገደማ ከወልድ አይሠርፅም ያለ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ከወልድ ይሠርፃል ያሉ የሮም ወገኖች ተለያዩ ። ቈይቶም በሌላ ወገን የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተሳስቷል ብለው የተቃወሙት ልዩ ወገኖች ተነሡና በጠቅላላ ፕሮቴስታንት ተባሉ ።

በእውነትም በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ አንድ ወገን፥ አንድ ማኅበር ስለሆኑ የባህል ልዩነት ፥ የአገር መራራቅ ፥ የቋንቋም መደባለቅ አንድነታቸውን ሊያስቀረው አይችልም ። ሆኖም ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እለያየት የተነሣ ሁሉ በአንድነት ሊቈርቡ አይችሉምና ክርስቶስ ራሱ ወገኖቹ አንድ እንዲሆኑ እንደ ጸለየ እኛም ጸልየን የምእመናንን አንድነት ማጽናት ይገባናል (ዮሐ. ፲፯ ፥ በተለይም ቍ. ፳- ፳፫ ።)

ምዕራፍ ፯ ።

# ሐዋርያዊ ሥርዓተ ሃይማኖት ።

ተጠማቂዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ብለው ይጠመቁ ነበር ። ከዚህም በላይ የቅድስት ሥላሴ ነገር ተነገረላቸው (ማቴ. ፳፰ ቍ. ፲፰- ፳) ፤ ሐዋርያትም አስተማሯቸው (የሐዋ. ፪ ቍ. ፵፩-፵፪) ቈይተው የተጻፉ የሃይማኖት ውሳኔዎች የተጠማቂዎች (የንዑስ ክርስቲያን) ማስተማሪያ ሆነው ያገለገሉ ይመስላል ። የቂሣርያ ጳጳስ ቅዱስ እውሳብዮስ በኒቅያ ጉባኤ እንዲህ አለ ፤

« ንዑሰ ክርስቲያን ሆነን በተማርንበት ጊዜና በተጠመቅንበት ጊዜ ከቀደሙን ኤጲስ ቆጶሳት እንደ ተቀበልነው እንዲሁም አምነን የሃይማኖታችንን ሥርዓት አቅርበንላችኋል።»

እንዲሁም ዛሬ በመጽሐፈ ክርስትና « ወእምዝ ይጼሊ ካህን ጸዋትው በእንተ ሰላም ወበእንተ ጳጳስ ወማኅበር ፤ ወጸሎተ ሃይማኖት » ይላል ።

ሐዋርያት የወንጌልን ዐዋጅ (ኪሪግማ) ተናገሩና ቃላቸው የሚከተለውን የመሰለ ነበረ ፤

«ትንቢት ተፈጸመ፤ መሲሑ መጥቶአልና አዲሱ ዘመን ተጀመረ ።
እርሱም ከዳዊት ዘር ተወለደ ።
በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደ ተጻፈ ፥ በሦስተኛው ቀን ተነሣ ።
የእግዚአብሔር ልጅና የሕያዋንም የሙታንም ጌታ ሆኖ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በክብር እንደ ተቀመጠ ነው ።

የሰው ፈራጅና መድኃኒት ሆኖ ዳግመኛ ይመጣል ። »

ከዚህም በላይ ሐዋርያት ራሳቸው የሃይማኖትን ውሳኔ ተናገሩ የሚል ታሪክ አለ ፤ እንዲህም ይላል ፥

« ጌታ ከዓረገ በኋላ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው ፤

የሃይማኖትንም ሥርዓት ተናገሩ ።

ጴጥሮስ « ሁሉን በሚችል ፥ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ» አለ ።



www.ethiopianorthodox.org

እንድርያስ « ብቻውንም ጌታችን የሆነ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ» አለ ።

ያዕቆብ « በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ ፣ ከማርያም ድንግል የተወለደ » አለ ።

ዮሐንስ « በጲላጦስ ጴንጤናዊ ዘመን መከራን የተቀበለ ፣ የሞተ ፣ የተቀበረ » አለ ።

ቶማስ « ወደ ሲኦል የወረደ ፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን የተነሣ» አለ ።

ያዕቆብ « ወደ ሰማይ ያረገ ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ » አለ ።

ፊልጶስ « ከዚያም በሕያዋንና በሙታን እንዲፈርድ ይመለሳል » አለ ።

በርተሎሜዎስ « በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ » አለ ።
ማቴዎስ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፣ በቅዱሳን አንድነት አለ » ።

ስሞዖን « በሥጋ ትንሣኤ» አለ ።

ማትያስም « በዘለዓለም ሕይወት » አለ ።

ይህ ታሪክ በአቀራረቡ እውነተኛ አይመስልም ። ሆኖም ቃሉ ከሐዋርያት ትምህርት የተቀዳ ነው ፣ በአጭርም የወንጌልን ዋና ነገር ይገልጣልና እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህ ውሳኔ ታውቆ ለንዑስ ክርስቲያን መማሪያ ሲያገለግል ኖሮአል ።

ወደ ሲኦል ወረደ ማለትና የቅዱሳን አንድነት ማለት በአመክንዮ ዘሐዋርያት በኒቅያም ሃይማኖት ቃል ውስጥ አልተጻፉምና ከዚህ በታች በአጭሩ አብራርተናቸዋል ፡—

<u>ክርስቶስ ወደ ሲኦል ወረደ</u>

ብሉይ ኪዳን ሰው ሁሉ ሙቶ ወደ ሲኦል ይወርዳል ይላል ፤ ሆኖም እግዚአብሔር የሠለጠነበት ሥፍራ ነው እንጂ ከእርሱ ሥልጣን ውጭ ያለ አይደለም ( መዝ. ፩፻፴፰ ቍ. ፰ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ሀየኒ ሀሎከ ፤ ቀላይ ሲል ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል ። አሞጽ ፱ ቍ. ፪ ) ።



ክርስቶስ ከተሰቀለ በኋላ ወደ ሲኦል ወረደ ሲል ሞትን ቀምሶ ሙታን ሁሉ ወደሄዱበት ወረደ ማለት ነው ( ማቴ. ፲፪ ቍ. ፴፱-፵ ) ።

ከዚህም በላይ ቅዱስ ጴጥሮስ « በወህኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው » እና « ወንጌል ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና » አለ ። ( ፩ ጴጥ. ፫ ቍ. ፲፱ ፣ ፬ ቍ. ፮ ) ።

አንዳንድ ሊቃውንት በብሉይ ዘመን የሞቱትን ሁሉ ክርስቶስ ሞቼላችሁአለሁ ብሎ አስረድቶ አድኖአቸዋል ብለው ይህን ቃል ይፈቱታል ። ቢሆንም ስንኳ ሙታንን ሁሉ ያዳናቸው አይመስልም ፤ በሕይወት ሳሉ የነቢያትን ቃል ካላዳመጡ ከመሞታቸው በኋላ የክርስቶስን ቃል እንዴት ያደምጣሉ ? ( ሉቃስ ፣ ፲፮ ፣ ቍ. ፴፩ ፣ ዕብራ. ፱ ፣ ቍ. ፳፯ - ፳፰ ) ። መቅድመ ወንጌልም ወኀደጎሙ ለእኩያን ህየ ውስተ ትውክልና ምስለ መላእክቲሆሙ እስከ ዕለተ ደይን ይላል ፤ ይህም ማለት ክፉዎችን በቍራኝነት እንዳሉ ከአለቆቻቸው ጋር እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተዋቸው ማለት ነው ።

ሌሎች ሊቃውንትም ሰበከላቸው ሲል ( ፩ ጴጥ. ፫ ቍ. ፲፱ ) ግሪኩ ዐወጀባቸው እንጂ አስረዳቸው ማለት አይደለም ይላሉ ፤ ነገራችሁ ተከተተ ፣ የዲያብሎስም ኃይል ተገፈፈ አለ ። ትምህርተ ኅቡአት እንዲህ ይላል ፣ እሙታን ተንሢኦ ፣ ሲኦለ ከይዶ ፣ በሞቱ ለሞት ደምሰሶ (ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ሲኦልን ጠቅጥቆ በሞቱ ሞትን አጠፋው ) ። ክርስቶስም የሰይጣንን ኃይል አጥፍቶ ምእመናንን አዳናቸው ( ዮሐ. ፫ ቍ. ፲፬ - ፳፩ ) ።

<u>የቅዱሳን አንድነት ( የቅዱሳን ማኅበር )</u>

ቅዱሳን የተባሉ ምእመናን ሁሉ ናቸው ፤ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ናቸውና ( ፩ ቆሮ. ፩ ቍ. ፪ ) ።

ጌታቸውም ሃይማኖታቸውም አንድ ስለሆነ አንድነት አላቸው ( ኤፌ. ፬ ቍ. ፩—፮ ) ። እየተረዳዱ ይኖራሉ ( ሮሜ. ፲፪ ቍ. ፲፫ ) ። አንድነታቸው የክርስቶስ ብልቶች በመሆናቸው ነው ( ፩ ቆሮ. ፲፪ ቍ. ፲፪—፴፩ ፣ ኤፌ. ፬ ቍ. ፲፩—፲፮ ) ።

እነዚህ ቅዱሳን ሞተው ሲለዩን በሞታቸው ምክንያት መጨነቅ የለብንም ፣ ሞታቸው ከክርስቶስ ፍቅር አይለያቸውም ( ሮሜ ፰

www.ethiopianorthodox.org

ቍ. ፴፰-፴፱ ) ። እንዲሁም እኛ በተራችን ሞተን ማኅበሩን ማሟላት አለብን ( ዕብራ. ፲፩ ቍ. ፴፱-፵ ) ።

ምእመናን ክርስቶስን አጥብቀው መመልከት ይገባቸዋል ፤ ይህን ሲያደርጉ የሞቱ ቅዱሳን የሃይማኖት ምስክሮች ሆነው እንደ ደመና ይከቧቸዋል ( ዕብራ. ፲፪ ቍ. ፩-፪ ) ።

እግዚአብሔር ቅዱሳንን ያከብራቸዋል ፥ ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር ይላል ( መዝ. ፩፻፲፭ ቍ. ፮ ፥ የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው ፤ ደግሞ ራእይ ፲፬ ቍ. ፲፫ ) ። የምእመን ምግባር የእምነቱ ፍሬ ስለሆነ መሞቱ አያስረሳውም ( ማቴ. ፲ ቍ. ፵፪ ) ።

የቀደሙን ቅዱሳን የሃይማኖት ምስክሮች ስለሆኑ እነርሱ የተመላለሱበትን መንገድ ይዘን እየተከተልን እናከብራቸዋለን (ፊል. ፫ ቍ. ፲፪ - ፲፯ ) ። በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በበዓለ ቅዱሳን የሚጸለይ ጸሎት እንደሚከተለው ነው ፡—

« በልጅህ ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ውስጥ የመረጥሃቸውን በአንድ ማኅበር ያያያዝህ እግዚአብሔር ሆይ ፥ በሚመስገን ቅዱስ ኑሮ ሁሉ ብፁዓን ቅዱሳንህን እየተከተልን ፥ ያለ ማስመሰል ለሚወዱህ ወዳዘጋጀህላቸው ወደማይነገር ደስታ እንድንገባ ጸጋህን ስጠን ። ( ፩ ተሰ. ፩ ቍ. ፩—፯ ተመልከት ) ።

ምእመናን በዚህ ዓለም እየተመላለሱ እንደ ጸለዩ እንዲሁም በሰማይ ሆነው በጸሎት ይሳተፋሉ ( ራእይ ፯ ቍ. ፲ ፥ ም. ፰ ቍ. ፫ ፥ ም. ፮ ቍ. ፲ ) ።

ክርስቶስ ራሱ ይማልድልናል ፥ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይትነብል ሎሙ ( ዕብራ. ፯ ቍ ፳፭ ፥ ለዘላለም ሕያው ነውና ስለ እነርሱ ይማልዳል ። ደግሞም ሮሜ ፰ ቍ. ፴፬ ።

እርሱ ራሱ ማላጅ ሲሆን ምእመናን ልጆቹ ሆነው እንዲለምኑ አዟቸዋል ( ማቴ. ፯ ቍ. ፯ ) ፥ ክብሩንም ተረድተው እንዲያመሰግኑት ፈቀዷል ( ራእይ ፲፱ ቍ. ፱- ፲ ) ።

ክርስቶስ በእኛና በእግዚአብሔር አብ መካከል ገብቶ ከእግዚአብሔር አብ የሚለየን አይደለም ፤ እርሱ ራሱ አምላክና ሰው ሆኖ የሚያስታርቀን ነው እንጂ ( ፪ ቆሮ. ፭ ቍ. ፲፰- ፲፱ ። )



እንዲሁም የሞቱ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ የሚያርቁን አይደሉም ፤ ከእኛ ጋር አንድ ማኅበር ሆነው በክርስቶስ ፍቅርና በክርስቶስ ጸሎት የተያያዙ ናቸው እንጂ ። ምእመናን ሁሉ በዓለምም ሆነ በሰማይ ቢኖሩ ወደ ሌላ ሳይሄዱ በቀጥታ በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ ይችላሉ ፤ እስመ ሐደሰ ለነ ፍኖተ ሕይወት --- ንቅረብ እንከ ይላል ( ዕብራ. ፲ ቍ. ፲፱-፳፫ የሕይወትን መንገድ ስላደሰልን እንግዲህ እንቅረብ ፥ ደግሞም ራእይ ፭ ቍ. ፰ ተመልከት ) ።

ከእኛ ጋር አንድ ማኅበር የሚሆኑ ቅዱሳን በጸሎተ ነግሥ ይታወሳሉ ፦

«ሰላም ለክሙ ማኅበረ መላእክት ትጉሃን ፤
ሰላም ለክሙ ማኅበረ ነቢያት ቅዱሳን ፥
ሰላም ለክሙ ማኅበረ ሐዋርያት ፍንዋን ፥
ሰላም ለክሙ ማኅበረ ሰማዕት ወጻድቃን ፥
ሰላም ለክሙ ማኅበረ ሥላሴ ጉቡአን ፥
ሰላም ለማርያም ዘእሳት ክዳን ። »

( ለማታንቀላፉ መላእክት ፡ ለቅዱሳን ነቢያት ፥ ለተላካችሁ ሐዋርያት ፥ ለሰማዕታትና ለጻድቃን ፡ ለማይለያዩ ሥላሴ ፥ የእሳት ልብስ ለለበስሽ ለማርያም ፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን) ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፯ ።

# አመክንዮ ዘሐዋርያት ።

አመክነየ ምክንያት መስጠት ከሚለው ፣ ግሥ የመጣ ስለሆነ አመክንዮ ማለት ምክንያት መሠረት ማለት ነው ።

ሲሞን መሠርይ ወደ ሐዋርያት ቀርቦ መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ ሽጡልኝ ፣ ተአምራትንም ቁድርግ ባላቸው ጊዜ እነ ጴጥሮስ ተቈጥተው ሰደዱት(የሐዋ. ፰ ቍ. ፲-፳፬) ፤ ሔዶ በሐሰተኛ ትምህርቱ ብዙውን ሰው ስላሳተ ሐዋርያት ይህን አመክንዮ ጽፈው ሐሰቱን ገለጡበት ይባላል ። ሆኖም ይህ ታሪክ አልተረጋገጠምና የኋላ ሊቃውንት የሐዋርያትን ትምህርት አስተጋብተው ይህን ውሳኔ የጻፉና ቃሉ ሐዋርያዊ ስለሆነ አመክንዮ ዘሐዋርያት ያሉት ይመስላል ።

ቃሉ በሥርዓተ ቅዳሴና በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበው ውስጥ ስለተጻፈ በጣም የታወቀ ሆኖአል ። ( ሥ. ቅ. ም. ፲ ) ። የሚከተለው ትርጒም ከቅዳሴ አንድም መጽሐፍ የተቀዳ ነውና አንዳንድ ማብራሪያ ጥቅስ ተጨምሮበታል ።

፩ «ነአምን በአሐዱ አምላክ ገባሬ ኵሉ ፍጥረት አብ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

( አቡሁ ሲል ነው ) ። የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሚሆን ፍጥረትን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን ።

መናፍቃን ለአብ አስገኝ አለው ብለዋልና በአሐዱ አለ (ዘዳግም ፮ ቍ. ፬ ፤ ፩ ጢሞ. ፮ ቍ. ፲፬-፲፮ ) ።

እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ ።

ለህላዌው ምክንያት የለውምና ።

አስገኝ የለውም ፤ መለኮት የተገኘበትና ያልተገኘበት ጊዜ የለም ( ራእይ ፩ ቍ ፰ ) ።

፫ በከመ አቅደምነ ነጊረ ።

አስቀድመን እንደ ተናገርን ።

አልቦ አመክንዮ ብሎ አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት ማለትን ለማምጣት ነው ።



አላ ባሕቱ ህልው በኵሉ መዋዕል ።

በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ ፤

(አንድም ፣ ባሕቲቱ ሲል ብቻውን ይኖራል አለ) ።

አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት ።

መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የለውም ።

አንድም ፣ እንደ ሮቤል በኵር ፣ እንደ ብንያም እሳሽ መቍረጫ የለውም ።

፬ ወቦቱ ብርሃን ዘኢይጠፍእ ።

በእርሱም የማይጠፋ ብርሃን አለ ።

ካደረ የማይለይ ፣ ከተሰጠ የማይነሣ ዕውቀት ፣ ክብር ፣ ጸጋ አለው ( ፩ ዮሐ. ፩ ቍ. ፩- ፯ ) ።

ወአልቦ ዘይክል ቀሪበ ኀቤሁ ።

ወደ እርሱ ለመቅረብ የሚችል የለም ።

ሊመረምረው ሊመስለው የሚችል የለም ። ራሱን ገለጠ እንጂ ሊገልጠው የሚችል የለም ፤ ልጁን አስተርጓሚ አድርጎ ላከው እንጂ የአብን ነገር ሊተረጒም የሚችል አልነበረም (ዮሐ. ፩ ቍ. ፲፬-፲፰ ፣ ዘጸአት ፴፫ ቍ. ፲፯- ፳፫ ) ።

፭ ኢኮነ ክልኤተ ወኢሠለስተ ።

ሁለተኛ አይደለም ፣ ሦስተኛ አይደለም ።

አላ አሐዱ ውእቱ ማለትን ለማምጣት ነው ። ልዩ ፣ ልዩ ፣ ማዕርግ ፣ ልዩ ልዩ ሹመት ያለው አይደለም ( ኢሳ. ፵፰ ቍ. ፱ -፲፫ ) ።

ወኢይትዌሰክ ።

ተጨማሪ የለውም ።

አርዮስ ፍጡርና ፈጣሪ አለ ፣ ዮሐንስ ተዐቃቢ ሦስት ህላዌያት አለ ፣ ጳውሎስ ሳምሳጢ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ነቢይ ነው አለ ፤ ይህም ሁሉ ሐሰት ነው ። ለእግዚአብሔርም ዘመድ የለውም ፤ ብዙ ተባዙ እንዳላቸው ደቂቀ አዳም አይደለም ። እንደ ነፍስ ፣ እንደ ሥጋ ፣ እንደ ልብ ፣ እንደ ቃል ፣ እንደ እስትንፋስም አይደለም ። (ኢሳ. ፵፮ ቍ. ፮ ፣ ቍ. ፰—፲፩) ።

፮ አላ አሐዱ ውእቱ ባሕቲቱ ዘይነብር ለዓለም ።

www.ethiopianorthodox.org

ብቻውን ለዘለዓለሙ የሚኖር እርሱ አንድ ነው እንጂ ።

እስመ ኢኮነ ስውረ ዘኢይትአመር ።

የማይታወቅ የተሰወረ አይደለምና ።

አእመርናሁ በአሪት ወበነቢያት ማለትን ለማምጣት ነው ። እንደ ምን ተገለጠ ቢሉ ፤ በፍጥረት (ሮሜ ፩ ቀ. ፲፰-፳፫) ፤ በነቢያት አፍ (፩ ጴጥ. ፩ ቀ. ፲ - ፲፪) ፤ በኢየሱስ ክርስቶስም (ዮሐ. ፩ ቀ. ፲፬-፵፯ ተገለጠና ነገሩን ብሰማ አላምንም ለሚል ሰው የሚያመኻኝበት የለውም ።

ዳዕሙ ጥዩቀ አእመርናሁ በአሪት ወበነቢያት ።

በአሪትና በነቢያት ተረድተን አውቀነዋል እንጂ ።

አሪትም ነቢያትም ፈጠረ ብለዋል ፤ (ዘፍ. ፩ ቀ. ፩ ፤ ኢሳ. ፵፩ ቀ. ፲፩- ፲፫ ፤ ም. ፳፯ ቀ. ፩-፪ ) ፤ ሁሉም የክርስቶስን ነገር ተናግረዋል (ሉቃ. ፳፬ ቀ. ፳፩- ፳፯) ።

፯ ከመ ውእቱ አኃዜ ኵሉ ።

ሁሉን የያዘ ነው ።

አንድም ፤ ሁሉን የፈጠረ ፤ ሁሉንም እንደ ጥና እንደ እንቍላል አድርጎ የያዘ ነው (ኢሳ. ፳፬ ቀ. ፰ ፤ ነህ. ፱ ቀ. ፯) ።

ወሥሉጥ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት ።

በፍጥረት ሁሉ ላይ የሠለጠነ ነው ።

መልዕልተ ኵሉ ወሥሉጥ --የሚል አብነት አለ ፤ ከሁሉ በላይ ያለ ነው ።

፰ አሐዱ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

(አቡሁ ሲል ነው) የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አንድ ነው ።

ኢየሱስን ፤ ክርስቶስ ብሎታል ፤ መሲሕ ነውና (ማቴ. ፲፯ ቀ. ፲፫- ፲፯) ። ጌታ ብሎታል ፤ ከእርሱ በቀር ጌታ የለምና (፲ ቆሮ. ፬ ቀ. ፬— ፮) ። መድኃኒት ብሎታል ፤ ከእርሱ በቀር የሚያድን የለምና (ዮሐ. ፲፬ ቀ. ፮-፯) ።

ዘተወልደ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።

ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ ።



አካል ዘእምአካል ፤ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደ (ቈላ. ፩ ቀ. ፲፩—፳) ።

ወልድ ዋሕድ ዘዕሩይ ምስሌሁ ።

ከእርሱ ጋር የተካከለ አንዱ ልጅ ።

ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው በዘመን በክብር ከእርሱ አንድ የሆነ ነው ። ሠለስቱ ምዕት ንዜኑ ህላዌሁ ለአብ ምስለ ወልዱ ወህላዌሁ ለወልድ ምስለ አቡሁ ብለው አርዮስን እንደረቱ ነው (ቅ. ሠ. ም. ፲፯ ፤ ዮሐ. ፰ ቀ. ፴ ፤ ም. ፲፬ ቀ. ፲፩) ።

፱ ገባሬ ኵሉ ሠራዊት ወሢመታት ወሥልጣናት ።

አለቅነትን ፤ ሹመትንና ሥልጣንን ሁሉ የፈጠረ ።

በሰማይ ያሉ መላእክት በምድር ያሉ ደቂቀ አዳም ቢሆኑ ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም ። (ቈላ. ፩ ቀ. ፲፩- ፲፮) ።

ዘሠምረ ይኩን ሰብአ በደኃሪ መዋዕል ።

በኋለኛው ዘመን ሰው እንዲሆን የወደደ

ነቢያት ይመጣል ያሉት ዘመን በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ (ዕብራ. ፩ ቀ. ፩- ፬ ፤ ዮሐ. ፩ ቀ. ፩ - ፲፬) ።

፲ ወነሥአ ሥጋ እምእግዝእትነ ማርያም ቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ።

ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ከእመቤታችን ማርያም ሥጋን ነሣ ።

ክርስቶስ የተፀነሰ ከመንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ ከዮሴፍ ሆነ ከሌላ ወንድ ዘር አይደለም (ማቴ. ፩ ቀ. ፲፰-፳፩ ፤ ሉቃ. ፩ ቀ. ፳፮- ፴፰) ። ሥጋን ነሣ ። ለባሴ ሥጋ እንጂ እውነተኛ ሰው አልሆነም የሚሉና የነሣው ሥጋን ነው እንጂ ነፍሱንና አእምሮውን አይደለም የሚሉ መናፍቃን አሉ ፤ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፩ ቀ. ፩-፲፬ ተረትተው ተገኝተዋል ።

ማርያም ቅድስት እመቤታችን ተብላለች ፤ ከሴቶች መካከል የተባረከች ናትና (ሉቃ. ፩ ቀ. ፳፰) ።

፲፩ ወተሐፅነ ከመ ሰብእ ዘእንበለ ኃጢእት ወአበሳ ።

ያለ ኃጢአትና ያለ በደል እንደ ሰው አደገ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥቂት በጥቂት አደገ እንጂ አምላክ ነኝና ዕለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ አላለም ። (ሉቃ. ፪ ቊ. ፴፱-፶፪) ። ኃጢአትን አላደረ ገም (ዕብራ. ፬ ቊ. ፳፫- ፳፰) ።

<u>ወአልቦ ጕሕለት ውስተ አፉሁ ።</u>

በአንደበቱ ምንም ሽንገላ የለም ።

በነገሩ ሐሰት የለበትም ፤ ለሐማሙ ኃጢአት ፥ ለረኃቡ ስስት የለውም (ዮሐ. ፬ ቊ. ፴፫-፴፱ ፥ ማቴ. ፬ ቊ. ፩- ፲፩) ።

፲፪ <u>ወእምዝ ሐመ ወሞተ በሥጋ ።</u>

ከዚህም በኋላ በሥጋ መከራን ተቀብሎ ሞተ ።

አደገ ብሎ ነበርና በኋላ ሞተ (ማቴ. ፳፯ ፥ ማር. ም. ፲፭ ፥ ሉቃ. ም. ፳፫ ፥ ዮሐ. ም፥ ፲፱) ። ስለምን ሞተ ቢሉ ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሰጠ (ማር ፲ ቊ. ፵፭) ። ሥጋው ተራበ ተጠማ ፥ መለኮቱ ግን ተአምራትን አደረገ አይባልም ፤ በሥጋ ሞተ ፥ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ እንላለን እንጂ (፩ ጴጥ. ፫ ቊ. ፲፰) ።

<u>ወተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት ።</u>

በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ።

መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ተነሣ (፩ ቆሮ. ፲፭ ቊ. ፫-፰ ፥ ማቴ. ም. ፳፰ ፥ ማር. ም. ፲፮ ፥ ሉቃ. ፳፬ ፥ ዮሐ. ም. ፳) ። ሐሙስ ማታ ፋሲካውን (ጸሎተ ሐሙስን) በልቶ ተያዘ ፤ በዕለተ ዓርብ ተሰቀለና ዓርብ አንደኛ ቀን ፥ ቅዳሜ ሁለተኛው ፥ እሑድ ሦስተኛው ነው (ማቴ. ፲፪ ቊ. ፴፰- ፵፪) ።

<u>ወዐርገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘፈነዎ ።</u>

ወደ ላከው ወደ አብ ፥ ወደ ሰማያት ዐረገ ።

በብርሃን ፥ በሥልጣን ፥ በይባቤ መላእክት ወደ ላከው ዐረገ (የሐዋ. ፩ ቊ. ፩- ፲፩) ። ከደቀ መዛሙርቱ ለምን ተለየ ቢሉ የተሰጠውን ሥራ ፈጸመው (ዮሐ. ፲፯ ቊ. ፬ - ፭ ) ፥ እንዳያዝኑም መንፈስ ቅዱ ስን ላከላቸው (ዮሐ. ፲፬ ቊ. ፳፭-፴፩) ።

፲፫ <u>ወነበረ በየማነ ኀይል ።</u>

በኃይልም ቀኝ ተቀመጠ ።

በአብ ዕሪና (ከአብ ተካክሎ) ኖረ (ዕብራ. ፩ ቊ. ፩ -፬) ። በአብ ቀኝ ሲል መክበሩን አረጋግጦአል ፤ ተቀመጠ ሲል የሠራውን ሥራ



እንደ ፈጸመው አረጋግጦአል (ዕብራ. ፲፪ ቊ. ፩-፪) ። በዚህም ዓለም የውርደትን ሥራ ይሠራ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ ግን የውርደት ሥራ የለበትም (ዕብራ. ፱ ቊ. ፳፯-፳፰) ።

<u>ወፈነወ ለነ ጰራቅሊጦስሃ መንፈስ ቅዱስ ዘወፅአ እምአብ ።</u>

ከአብ የሠረፀውን መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስን ላከልን ።

የአብንና የወልድን ነገር ተናግሮ የመንፈስ ቅዱስን ነገር ጀም ሮአል ። ከአብ አካል ዘእምአካል ፥ ባሕርይ ዘእምባሕርይ ሠረፀ ፥ ተላ ከልንም (ዮሐ. ፲፬ ቊ. ፳፮) ። ጰራቅሊጦስ ማለት በልሳነ ዮናኒ (በግ ሪክ ቋንቋ) ናዛዚ (አረጋጊ) ፥ ከሣቲ (ገላጭ) ፥ መንፅሒ (አንጺ) ፥ መጽንኢ (አጽኚ) ፥ መስተፍሥሒ (አስደሳች) ፤ መስተስርዪ (አስታ ራቂ) ማለት ነው ፤ ዋና ሥራው አጽናኝነቱ ነው (ዮሐ. ፲፬ ቊ. ፲፭- ፲፯) ።

ለእኛም ተላከ አለ ፥ በምእመናን አድሮ በመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ያበረታቸዋልና (ገላ. ፭ ቊ. ፳፪- ፳፯) ።

<u>ወአድኀነ ኵሎ ዓለመ ።</u>

ዓለምን ሁሉ ያዳነ ።

ዕውቀት በመሆን ከንዴተ አእምሮ አዳነ ፤ ብርሃን በመሆን ከኃ ጢአት ጨለማ አዳነ (፩ ዮሐ. ፫ ቊ. ፳፫-፳፬) ። ሁሉ ማለት ኵነኔ የለም ማለትን አያመጣም ፤ አንድንም የሚሉ ይጠፋሉና መንፈስ ቅዱስ ጥፋታቸውን ያስረዳቸዋል (ዮሐ. ፲፮ ቊ. ፯-፲፩) ።

<u>ዘህልው ምስለ አብ ወወልድ ።</u>

በአብና በወልድ ዘንድ የሚኖር ።

መንፈስ ቅዱስን ሰደደልን ። እነ መቅዶንዮስ መንፈስ ቅዱስን ፍጡር እንዳይሉት ሊቃውንት ኢይኤዝዞ አብ ለወልዱ በከዊነ አብ ፥ ወኢየዓቢ ወልድ በከዊነ ወልድ ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ዕሩይ ውእቱ ብለዋል (ቅዳሴ ማርያም ፶፪ ፥ አባት በመሆን አብ ልጁን አያዝዘ ውም ፥ ወልድም ልጅ በመሆን አይበልጥም ፥ መንፈስ ቅዱስም ትክክል ነው) ። ከወልድም ሠረፀ እንዳይባል ወመንፈስ ቅዱስ ይዜኑ ዘከመ ወፅአ እምአብ ወዘከመ ነሥአ እምወልድ ብለዋል ። (ቅ. ፫፪ ፥ ፵፩ ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደ ሠረፀ ፥ ከወልድም እንደ ነሣ ይናገራል ፥ ዮሐ. ፲፬ ቊ. ፳፮) ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬ ንብል እንከ ከመ ኵሉ ሠናይ ፍጥረተ እግዚአብሔር ።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ እን ናገራለን ።

ፍጥረት ንጹሕ ነው ።( ዘፍ. ፩ ቍ. ፴፩ ) ። ግዙፋዊ ነገር ሁሉ ርኩስ ነው የሚሉ ሐሰተኞች ነበሩ፤ እንዲህ ቢሆን ኖሮ ወልደ እግ ዚአብሔር ሥጋችንን እንዴት አድርጎ ነሣው ?

ወአልቦ ግዱፍ ።

ግድፈትም የለበትም ።

አዳምና ሔዋን ዛፉን አትንኩ ፣ ሕዝበ እስራኤልም እነዚህን አትብሉ ተብለው የለምን ? ቢሉ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን እንዲ ያከብሩ ነው እንጂ ፣ እነዚህ ፍጥረቶች መጥፎ ሆነው አይደለም ። ዘፍ. ም. ፫ ፣ ዘሌዋ. ም. ፲፩ ፣ ማር. ፯ ቍ. ፲፬—፳፫ ፤ የሐዋ. ፲ ቍ. ፱—፲፯ ) ። በዓለም ውስጥ ያለ ክፋት ቢበዛ የሰይጣን ሥራ ነው እንጂ የእግዚአብሔር አይደለም ( ያዕ. ፩ ቍ. ፲፩—፲፭ ፣ ዮሐ. ፰ ቍ. ፵፬ ) ።

፲፭ መንፈስሰ ሕይወተ ሥጋ ይእቲ ንጽሕት ወቅድስት በኵሉ ።

የሥጋ ሕይወት የምትሆን መንፈስ ግን ሁለመናዋ ንጽሕትና ቅድስት ናት ።

መንፈስ ( ነፍስ ) በባሕርይዋ ፈርሳ በስብሳ ትቀራለች ላሉ መናፍቃን መንፈስ ሕይወት ናት አለ ። ኃጢአት የባሕርይ ነው ፣ አዳም ኀጥእ ሆኖ ተፈጠረ ላሉ መናፍቃን መንፈስ ንጽሕትና ቅድስት ናት አለ (ምሳሌ ፳ ቍ. ፳፯ ፣ የሐዋ. ፲፯ ቍ. ፳፬-፳፱ ፣ ዘፍ. ፪ ቍ. ፯

፲፮ ወንሕነሰ ንብል ከመ ሰብሳብ ንጹሕ ወልደት ዘአልቦ ርኩስ ።

እኛስ ፣ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ፣ መዋለድም ርኩሰት እንደሌ ለበት እንናገራለን ።

( ወልደት አልቦቱ ርኩሰት የሚል አብነት አለ ፤ ትርጓሜው አንድ ነው ) ። አውስቦ ( ጋብቻ ) ርኩስ ነው ላሉ ንጹሕ ነው አለ ፣ (ዕብራ. ፲፫ ቍ. ፬ ፣ ማር ፲ ቍ. ፪—፱ ፣ ኤፌ. ፭ ቍ. ፳፩—፴፫ ። )

እስመ ፈጠሮሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ከመ ይብዝኑ ሕዝብ

እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲበዙ አዳምንና ሔዋንን ፈጠራቸውና ።

ብዙ ተባዙ ብሎ ፈጥሮአቸዋልና መዋለድ አያረክስም (ዘፍ. ፩ ቍ. ፳፰ ) ። የወለደች ሴት ትንፃ ይል የለምን ቢሉ ( ዘሌዋ. ፲፪ ) ፣



ልጅዋ የአዳም ልጅ እንደሆነበት መጠን የአዳም ኃጢአትን ወራሽ ስለሆነ ነው (መዝ. ፶ ቍ. ፭) እንጂ መውለድዋ አርከሶአት አይደለም። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲበዙ ፈልጎአልና ምእመናን ፈጣሪአቸ ውን እያመሰገኑና እያስመሰገኑ መኖር ይገባቸዋል (፩ ጴጥ. ፪ ቍ. ፱-፲ ) ።

፲፯ ንለቡ እንከ ከመ ቦ ውስተ ሥጋነ ነፍስ እንተ ኢትመውት ።

እንግዲህ የማትሞት ነፍስ በሥጋችን እንዳለች እናስተውል ።

ክርስቶስ ተነሣ ፣ በእርሱ አምነን በትንሣኤ ሙታን የምንነሣ ነንና ሙተን እንቀራለን አንበል ( ፩ ቆሮ. ም. ፲፭ ) ።

ወኢትማስን ምስለ ሥጋ ።

ከሥጋ ጋር የማትጠፋ ።

ነፍስ ፈርሳ በስብሳ ትቀራለች ላሉት ከሥጋ ጋር ፈርሳ በስ ብሳ የማትቀር ነፍስ እንዳለችን እንናገራለን ።

፲፰ ንሕነሰ ናስቄርር ኵሎ ግብሮሙ ለዕልዋነ ሃይማኖት ።

እኛስ የሃይማኖት ለዋጮችን ሥራቸውን ሁሉ እንጸየፋለን ።

የመናፍቃንን ክህደት እንነቅፋለን አለና ዐውቀው እየሳቱና እያሳቱ ከሚኖሩ ሁሉ መራቅ ይገባናል (ማቴ. ፲፰ ቍ. ፲፩—፳ ፣ ቲቶ ፫ ቍ. ፱—፲፩ ) ።

ወኵሎ ፍልጠተ ።

መለያየትን ሁሉ ።

ከምእመናን መለያየታቸውን እንነቅፋለን አለና ምእመናን እየ ተስማሙና እየተቀናኑ መኖር ይገባቸዋል ( ዕብራ. ፲ ቍ. ፳፫—፳፭ ) ።

ወዐሊወ ሕግ ።

ሕገ ወጥነትን ሁሉ ።

ሕገ ወጥነታቸውን እንነቅፋለን አለና ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ይገባቸዋል (ሮሜ ፰ ቍ. ፩—፰ ፣ ማቴ. ፭ ቍ. ፲፯—፳ ) ።

እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀቤነ ፤

እነሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና ።

www.ethiopianorthodox.org

እንድም ፡ ሃይማኖትን የሚለውጡ የመናፍቃን ግብራቸውን እንጸየፋለን ፤ ከምእመናን መለየታቸው ፡ ሕግን መለወጣቸው ( ጽሉአን ሲል ነው) በእኛ ዘንድ የተጠሉ ናቸውና ።

፲፱ ወካዕበ ነአምን ትንሣኤ ሙታን ።

ደግሞም የሙታን ትንሣኤ፥እንዳለ እናምናለን ።

ጌታችን አስተምሮታል (ማቴ.ም. ፳፬—፳፮ ፡ ሉቃስ ፳ ቍ. ፳፯—፴) ፤ ሐዋርያትም ደግመውታል (፩ ቆሮ.ም. ፲፭፡፩ ተሰ.፬ ቍ.፲፫—፲፰)። ምእመናን ከጌታ ጋር ይሆናሉ ( ፊል. ፩ ቍ. ፲፱—፳፯ ) ።

ጻድቃን ወኃጥአን ።

የጻድቃንና የኃጥአን ።

ትንሣኤ እንዳለ እናምናለን ፤ ሙታን ያላቸውን ጻድቃንና ኃጥአን ብሎ ደገመ ። ትንሣኤ ሙታን የለም ላሉትና ቢኖር ጽድቅና ኵነኔ የለም ላሉት መናፍቃን ተናገረ ( ራእይ ፳ ቍ. ፲፩—፲፭ ) ።

ጽድቅ እንደምን ነው ቢሉ ቅዱስ ጳውሎስ ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል ፡ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም አለ ( ኤፌ. ፪ ቍ. ፬—፲) ። ቅዱስ ያዕቆብ ይህን አያፈርስምን ቢሉ ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ሆናችሁ እምነታችሁን በምግባራችሁ ካልገለጣችሁ ከንቱ ነው አለ እንጂ ፡ ሰው የሚጸድቅ በክርስቶስ አምኖ የእግዚአብሔርን ጸጋ በመቀበል እንደሆነ አይክድም ( ያዕ. ፪ ቍ. ፲፰—፳፮ ) ።

ኃጢአት እንደምን ነው ቢሉ እግዚአብሔር ያዘዘውን አላደርግም ብሎ ማመፅ ነው (፩ ዮሐ. ፫ ቍ. ፬) ። እንግዲህስ ያልበደለ የለምና ሁሉ ተኰንኗል ቢሉ ኃጢአተኛ ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ( ሉቃስ ፲፭ ቍ. ፲፩—፴፪ ) ።

፳ ወዕለተ ኵነኔ ።

የፍርድ ቀን ፡

እንዳለ እናምናለን ። ዕለተ ኵነኔ ፡ ዕለተ ምጽአት ምን ጊዜ እንደሚሆን አይታወቅም ፤ ምእመናን ተዘጋጅተው መጠባበቅ አለባቸው ( ማቴ. ፳፬ ቍ. ፴፮—፶፩ ፡ ማር. ም. ፲፫ ) ።

አመ ይትፌደይ ኵሉ በከመ ምግባሩ ።

ሁሉ እንደ ሥራው መጠን የሚቀበልበት ፡

የፍርድ ቀን አለ ። ክፉ የሠራ ፍዳውን ፡ በጎ የሠራ ዋጋውን የሚያገኝበት ጊዜ አለ ( ማቴ. ፳፭ ቍ. ፴፩—፵፮ ) ።



( እንድም ፡ ከመ ይትፌደይ ይላል ፤ ፍዳውን ይቀበል ዘንድ ። እንድም ፡ ዘይትፌደይ ይላል ፤ ፍዳውን የሚቀበልበት) ።

፳፩ ዓዲ ነአምን ከመ ክርስቶስ ኢኮነ ሕፁፀ እምትስብእት ወኢምንተኒ ።

ደግሞ ፡ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ምንም ጕድለት እንደሌለበት እናምናለን ።

የጽድቅና የኵነኔ ነገር የክርስቶስን ነገር ደግሞ አመጣው ።

አላ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ በጽድቅ ።

በእውነት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ ።

ኅድረት (እምላክነት አደረበት) ላሉት ሰው ሆነ አለ ። ነፍስን አልነሣም ላሉት የሆነ ሰው ነው አለ ። ምትሀት ( መሰል ) ነው ላሉት በእውነት አለ ። ውላጤ (ተለወጠ ፡ ልዩ ሆነ) ላሉት የእግዚአብሔር ቃል ነው አለ ( ዮሐ. ፩ ፡ ቍ. ፩—፲፰ ) ።

፳፪ ወዐረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ ።

የአብ ሊቀ ካህናት ሆኖ የሰውን ወገን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ ።

ኅሩይ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ሆነ (ከእግዚአብሔርና ከሰው መካከል ያለው ምርጥ ፡ ፩ ጢሞ. ፪ ቍ. ፭—፯) ። አማላጃችንና አስታራቂአችን እርሱ ነው (፪ ቆሮ. ፭ ቍ. ፲፰—፳፩ ) ። ራሱን በመስቀል ላይ ሠውቶአልና ሊቀ ካህናት አለው (ዕብራ. ፯ ቍ. ፳፯—፳፰ ፡ ፩ ጴጥ. ፪ ቍ. ፳፪—፳፭) ።

፳፫ ኢንትገዘር እንከ ከመ አይሁድ ።

እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር ።

ክርስቶስን ሊቀ ካህናት ብሎታል ፤ ኦሪትን ፈጽሞአልና እንግዲህ አንገዘር ፡ ግዝረት ይረባናል ይጠቅመናል አንበል አለ ። እግዚአብሔር አዝዞት አልነበረምን ቢሉ ክርስቶስ ከኦሪት ባርነት ፈትቶናል (ሮሜ ፯ ፡ ገላ.ም.፭ ፡ ም ፮ ቍ. ፲፩—፲፮ ፤ ዘፍ. ፲፯ ቍ. ፱—፲፬) ።

ፍትሐ ነገሥትም ፡ ግዝረት ኅበ ዘይትገበር እምበዓለ ግዝረት በከመ ፍና ልማድ አኮ እምፍና ቀኖና ሕጋዊ አለ ( አንቀጽ ፶፩ ፡ በገዛሪ እጅ የሚሆን ግዝረት በልማድ ነው እንጂ ከመጽሐፍ የተገኘ አይደለም) ።

ነአምር ከመ መጽአ ዘይፌጽም ኦሪተ ወነቢያተ ።

ኦሪትንና ነቢያትን የሚፈጽማቸው እንደ መጣ እናውቃለን ።

www.ethiopianorthodox.org

አንገዘርም ብሎ ነበርና ሕግንና ነቢያትን የሚያሳልፋቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ አድኖናል ብሎ ምክንያትን ጨምሮ ተናገረ (ማቴ. ፭ ቍ. ፲፯) ።

አንድም ፥ እንደ አይሁድ ግዝረት ይረባናል ይጠቅመናል አን ልም ፤ ኦሪትን ነቢያትን የሚፈጽም መጥቶአልና በእርሱ ፈጻሚነት እንከብራለን እንላለን እንጂ ።

፳፬ ዘኪያሁ ይሴፈዉ ምጽአቲ ኵሎሙ አሕዛብ ።

ሕዝቦች ሁሉ የእርሱን መምጣት በተስፋ የሚጠባበቁት ።

ቀዳማዊ ምጽአቱን (መወለዱን) ቢሉ ያባቶቻቸውን ነው (ሉቃ. ፪ ቍ. ፳፱—፴፪) ፤ ደኃራዊ ምጽአቱን (ዳግም ምጽአቱን) ቢሉ የተመቸ ነው (ኢሳ. ፲፩ ቍ. ፲) ። ከሰይጣን አገዛዝ ፈታቸው ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲያገባቸው ይመጣልና ደስ አላቸው ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሠረፀ እምይሁዳ ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ የተገኘ ፥

በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም ተብሎ ነበር (ዘፍ. ፵፱ ቍ. ፲) ፥ ከያዕቆብ ልጅ ከይሁዳ ነገሥታት ተወለደ (፩ ዜና. ፪ ቍ. ፩-፲፭ ም. ፫ ፥ ማቴ. ፩ ፥ ሉቃስ ፫ ቍ. ፳፫—፴፰) ።

ወእምሥርወ ዕሤይ ።

ከዕሤይም ሥር ፥

ከዳዊት አባት ከዕሤይ ትውልድ ተወለደ (ኢሳ. ፲፩ ቍ. ፩—፭) ። ሐተታ ፤ መጽሐፍ አባትን በዐጽቅ ልጅን በሥር ይመስላል ፥ ዐጽቅ እየተቈረጠ ሥር እንደሚቀር አባት እየሞተ ልጅ ይተካልና ክርስ ቶስ የዕሤይ አባት ከሚሆን ከይሁዳ ተወለደ ። መጽሐፍም አባትን በሥር ልጅን በዐጽቅ ይመስላል ፥ ከዐጽቅ ሥር እንደሚቀድም ከልጅ አባት ይቀድማልና ክርስቶስ የዕሤይ ልጅ ከምትሆን ከቅድ ስት ማርያም ተወለደ ።

፳፭ ዘሥልጣኑ ዲበ መትከፍቱ ።

ሥልጣኑ በትከሻው ላይ የሆነ ነው ።

አለቅነት የእርሱ ነው (ኢሳ. ፱ ቍ. ፮ ፥ ማቴ. ፳፰ ቍ. ፲፰) ። በት ከሻው ላይ ማለት እንደምን ነው ቢሉ አንድም ፥ ኖላዊ (እረኛ) የተ ሰበረውን በግ ተሸክሞ ወስዶ እንደሚያጸናው ጽንዓ ነፍስ አጥቶ



የነበረ አዳምን ጽንዓ ነፍስ ሰጥቶ አድኖታል ። አንድም ፥ መስቀል ሥልጣኑ ነውና በጫንቃው ላይ ተሸከመው ።

፳፮ ሎቱ ስብሐት ወአኰቴት ።

ለእርሱ ምስጋና ገናንነት ፥

ይገባዋል ፤ ሥልጣን ያለው ነው ብሎ ነበርና መመስገን ይገባ ዋል (ፊል. ፪ ቍ. ፱—፲፩) ።

ዕበይ ወባርኮት ።

ክብር በረከት ፥

ይገባዋል ፤ ስቡሕ እኩት ዓቢይ ቡሩክ ተብሎ መመስገን ይገ ባዋል ።

ውዳሴ ወማኅሌት ።

ውዳሴ ቃለ መዝሙርም ፥

ይገባዋል ፤ በውስጥና በአፍአ ፥ በልብና በቃል መመስገን ይገባዋል (ራእይ ፯ ቍ. ፱—፲፪) ።

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙም ፤ አሜን ።

(ዕብራ. ፲፫ ቍ. ፰ ፥ ራእይ ፩ ቍ. ፰) ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፰ ።

# የኒቅያ ጸሎተ ሃይማኖት ።

ሊቃውንት አርዮስ የሚባለውን መናፍቅ እየተቃወሙ ተሰብ ስበው ጸሎተ ሃይማኖትን ጻፉ ። በቅዳሴ ሠለስቱ ምዕትና በመጽ ሐፈ ሃይማኖተ አበው ውስጥ ተጽፏል ፤ የኋላ ሊቃውንት ካወጡ ለት ትርጕም የሚቀጥለውን አውጣጥተን ጥቅሱን ጨምረናል ።

፩ <u>ነአምን በአሐዱ አምላክ ።</u>

በአንድ አምላክ እናምናለን ።

አረማውያን በብዙ አማልክት ያምናሉና አንድ ይላል (ዘዳግ. ፮ ቍ. ፬ ፤ ፩ ቆሮ. ፰ ቍ. ፬-፯) ። እነ ሰባልዮስም ፩ኛ አብ ወል ድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ገጽ ናቸው ፤ ፪ኛ ለየራሳቸው ልብ ቃል እስት ንፋስ አላቸው (አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሆሙ) ፤ ፫ኛ አብን የሚሆንበት ፥ ወልድን የሚሆንበትና መንፈስ ቅዱስን የሚሆን በት ጊዜያት ልዩ ናቸው አሉ (ቦ ጊዜ አበ ይከውን ፥ ወቦ ጊዜ ወልደ ይከ ውን ፥ ወቦ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይከውን) ። ስለዚህ አንድ አምላክ ይላል (ማቴ. ፫ ቍ. ፲፮-፲፯ ፥ ዮሐ. ፲፬ ቍ. ፳፮-፳፯) ።

<u>እግዚአብሔር አብ ።</u>

በእግዚአብሔር አብ ።

መገኛ አባት ነው (ኤፌ. ፫ ቍ. ፲፬-፲፭) ። በልደት የክርስቶስ አባት ነው (ማቴ. ፫ ቍ. ፲፮-፲፯) ፥ በጸጋውም የምእመናን አባት ነው (ሮሜ. ፰ ፲፭-፲፯) ።

ምነው ቢሉ በተሰሙ ያርሱ ፥ በጀመሩ ይጨርሱ ነውና ክርክራ ቸው በወልድ ነበር ፤ ምነው አብን አስቀደመው ቢሉ አርዮስ ወልድን ብከድ አብን አስካድኋችሁ ባለ ነበር ። ደግሞ ባባት ጀምረው በልጅ እንደ ፈጸሙ ባወቁት ገንዘብ ነው ።

<u>አኃዜ ኵሉ ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር ።</u>

ሁሉን በሚገዛ ፤ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ ።

አንድም ፥ ሁሉን እንደ ጥና ፥ እንደ ዕንቍላል በመኻል እጁ የያዘ (ዘፍ. ፩ ቍ. ፩ ፥ መዝ. ፻፩ ቍ. ፳፭-፳፯ ፥ የሐዋ. ፲፯ ቍ. ፳፬-፳፭) ።



ምነው አኃዜ ኵሉ ባልበቃቸውም ነበር ቢሉ ተረፈ ማኒ (የማኒ ተከታዮች) ነበሩ ፤ ይህን ዓለም የሚያዝና የሚከናከን የለም (አል ባቲ ሠራዒ ወመጋቢ ለዛቲ ዓለም) ፥ ደግሞም ሰማይን የፈጠረ አም ላክ ሌላ ፥ ምድርን የፈጠረ አምላክ ሌላ ስላሉ ፥ ገባሬ ሰማያት ወም ድር ይላል ።

<u>ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ።</u>

የሚታየውንና የማይታየውን ፥

ግዙፋንና ረቂቃን በፈጠረ እናምናለን (ዕብራ. ፲፩ ቍ. ፫) ። ርቀው የማይታዩና ተራቅቀው የማይታዩ አሉ ፤ ምንና ምን ቢሉ ነፍሳት ፥ ነፋሳት ፥ መላእክት ናቸው ። መላእክት ታይተዋል ቢሉ ለሰው ዓይን የሚገለጡበትና የማይገለጡበት ጊዜ አለ (ዘመሳ. ፮ ቍ. ፳፩) ።

፪ <u>ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ።</u>

በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ።

በተለየ አካሉ አንድ ነው ፤ አንድም ፥ በባሕርይ በህልውና ከአ ብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው (ኤፌ. ፬ ቍ. ፬—፮) ። ሮማው ያን ቄሣርን አምልኩ ቢሉ ምእመናን አንድ ጌታ አለን እያሉ ተሰ ደዱ ፥ ተገደሉም ።

ክርስቶስ የተቀባ ፥ መሲሕ ማለት ነው (ማቴ. ፲፮ ቍ. ፲፮) ። ኢየ ሱስ ደኅንነት መድኃኒት ማለት ነው (ማቴ. ፩ ቍ. ፳፩) ። ጌታ ተብ ሎአልና ምእመናን ለእርሱ መገዛትና በእርሱ ማመን ይገባቸዋል (ማቴ. ፲፩ ቍ. ፳፰—፴ ፤ ዮሐ. ፲፫ ቍ. ፲፬ ፥ ዮሐ. ፫ ቍ. ፲፮) ።

<u>ወልደ አብ ዋሕድ ።</u>

የአብ አንድ ልጁ ።

አሐዱ ብሎ ነበረና ለምን ዋሕድ አለ ቢሉ አንድ ጌታ ሲል ሌላ ጌታ እንደሌለ ያረጋግጣል (ዮሐ. ፩ ቍ. ፲፬) ። ተቀዳሚ ፥ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ ነው ።

ፍልብያኖስ የሚባል መናፍቅ ሁለት አካል ፥ የሰውነቱ አንድ የመለኮትነቱ አንድ ነው አለና ዋሕድ ይላል ። ቄይቶ የተነሣ ንስጥ ሮስ ወልደ እግዚአብሔርንና ወልደ ማርያምን ልዩ አደረጋቸውና ወልደ አብ ዋሕድ ይላል ተብሎ ተረታ ።

www.ethiopianorthodox.org

<u>ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።</u>

ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በኖረ ።

አንድም ፣ ከእርሱ ጋር እንደ እርሱ በነበረ (ዮሐ. ፩ ቍ. ፩—፫) ። ፎጢኖስ የሚባል መናፍቅ ፣ ከእግዝእትነ ማርያም ከተወለደ በኋላ ወልድ ተባለ እንጂ ከዚያ ቀድሞ፡ ወልድ የሚባል አልነበረም አለ (ለፌ ህላዌሁ ለወልደ እግዚአብሔር እማርያም ወአኮ እምትካት) ፤ ዓለም ሳይፈጠር ይላልና አይሆንም ።

<u>፫ ብርሃን ዘእምብርሃን ።</u>

ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ።

ከአብ ፣ ከብርሃን ፀዳል ፣ ከፍምም ነበልባል ሲወለድ አይቀዳደ ምም (ያዕ. ፩ ቍ. ፲፯ ፣ ፩ ዮሐ. ፩ ቍ. ፭) ።

<u>አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ።</u>

ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የሚሆን ።

(ቈላ. ፩ ቍ. ፲፭—፳) ። ከብርሃን ከአብ በተገኘ በብርሃን በወልድ እናምናለን ብሎ ነበርና ከባሕርይ አምላክ ከአብ በተገኘ በባሕርይ አምላክ በወልድ እናምናለን ብሎ ጨምሮአል ።

<u>ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ።</u>

የተፈጠረ ያይደለ ፣ የተወለደ ።

(ቈላ. ፩ ቍ. ፲፭ ፣ ማቴ. ፩) ። አርዮስ ሸክላ ሠሪ መሥሪያውን ሠርታ እንደምትሠራ ፣ ደበናንሣ መዶሻውን ሠርቶ ዘመደ ሐፃውንትን (የብረት መሣሪያን በየዓይነቱ) እንደሚሠራ ፈጥሮ ፈጠረበት አለና አልተፈጠረም ይላል ። እንደ አርዮስ ፍጡር ፣ እንደ ንስጥሮስ የጸጋ ልጅ ፣ እንደ ፎጢኖስ ቀድሞ አልነበረም አንልም ፤ በባሕርይ ተወ ለደ እንላለን እንጂ ።

<u>ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ።</u>

በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ የሆነ ።

መበላለጥ የለም ፤ በሥልጣን ፣ በጌትነት ፣ በባሕርይ ከአባቱ ጋር ትክክል ነው (ፊል. ፪ ቍ. ፮ ፣ ኢሳ. ፯ ቍ. ፫) ።

ከአብ ወልድ ያንሳል ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ወልድ ይልቃል (የዐ ዕድ ወልድ እምአብ ፣ ወኢይትዔረዮ መንፈስ ቅዱስ ለወልድ) የሚሉ መናፍቃን አሉና ከአብ ጋር ተካከለ ይላል ።



ዘኀቡር ህላዌሁ ምስለ አቡሁ የሚል አብነት አለ ፣ ትርጓሜው ተመሳሳይነት ያለው ነው ።

<u>፩ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ።</u>

ሁሉ በእርሱ የሆነ ።

ሁሉ በእርሱ ቃልነት ፣ በእርሱ ህልውና ተፈጠረ ( ቈላ. ፩ ቍ. ፲፭—፲፯ ፣ ዘፍ. ም. ፩) ።

<u>ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ።</u>

ያለ እርሱ ምንም የሆነ የሌለ ።

ያለ እርሱ ቃልነት ፣ ያለ እርሱ ህልውና የተፈጠረ የሌለ ።

<u>ወኢ.ምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ ።</u>

በሰማይና በምድር ካለው ሁሉ ፣

ያለ እርሱ የሆነ የለም ። በሰማይ ያሉ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከዋክ ብት ፣ መላእክት ፤ በምድር ያሉ ዛፎች ፣ ድንጋዮች ፣ እንስሳት ፣ ሰውም ቢ.ሆን ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም ።

<u>፭ ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ።</u>

ስለ እኛ ስለ ሰዎች ፣ እኛንም ስለ ማዳን ከሰማይ ወረደ ።

ሰይጣን የላሜ ልጅ ያውራዬ ውላጅ ብሎ ቢማርከን ክርስቶስ ሊያድነን ወረደ (ዮሐ. ፮ ቍ. ፴፭—፵ ፣ ሮሜ ም. ፭) ። በመለኮት መው ጣት መውረድ አለበትን ቢሉ ወረደስ የሚያሰኝ ካምባ የነበረ ከሜዳ ፣ ከግምብ የነበረ ከምድር ቢ.ወርድ ወረደ ይለዋል ፤ እርሱ ግን ከምልዓቱ ሳይጐድል ፣ ከስፋሕ አምላክነቱ ሳይጠቀለል ሥጋን ለብሶ በአካል ታግሦ በመታየቱ ወረደ ተባለ (ፊል. ፪ ቍ. ፭—፲፩) ።

መድኃኒትነቱ ማለት ሰው በገዛ ሥራው ራሱን ሊያድን ተስ ኖታልና ጌታችን በእኔ የሚያምን ይድናል ብሎ በእኛ ፈንታ ሞተ (ገላ. ፫ ቍ. ፳፩—፳፪ ፤ ፩ ጴጥ. ፪ ቍ. ፳፪—፳፭) ።

<u>ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል።</u>

በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ለበሰ ፣ ሰውም ሆነ ።

ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ማለት ነው ። እም በ ነው ፤ በግ ብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ ፣ የከፈለ ያነፃ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነው (ሉቃስ ፩ ቍ. ፳፮—፴፭) ። እምና እም አንድ ወገን ነው ፤ ከእመ ቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ኅርኅርዮስም መንፈስ ቅዱስ ቀደሳ ወአንጽሓ ለማርያም ወረሰያ ለተወክፎ ቃል አምላካዊ አለ (መንፈስ ቅዱስ ቀደሳት ፥ አነጻትና የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል አዘጋጃት) ።

መናፍቃንም ፤ አውረደ ሥጋ እምሰማይ ወእኮ እማርያም (ሥጋ ከሰማይ እንዲወርድ አደረገ ፥ ከማርያም አይደለም) ብለው የክርስቶስን እውነተኛ ሰብአዊነት እንዳያፈርሱ ከማርያም ሥጋን ነሣ ይላል (ዕብራ. ፪ ቍ. ፲፬—፲፰) ።

## ፯ ኮነ ብእሴ ።

ሰው ሆነ ።

ሰው ማለት የነፍስና የሥጋ የተዋሕዶ ስማቸው ነው ። አቡሊናርዮስ የሚባል መናፍቅ ሥጋን ብቻ ነሣ ፥ አምላክነቱ ነፍስና አእምሮ ሆነለት (ህየንተ ነፍስ ወልቡና ኮነ መለኮቱ) አለና ሰው ሆነ ይላል ። (፩ ጢሞ. ፪ ቍ. ፭ ፥ ሉቃስ ፪ ቍ. ፴፱—፶፪) ። ቅዳሴውም ከመ ሕፃናት በከየ እንዘ ይስእል እምአጥባተ እሙ ሲሳየ ፥ አንሶሰወ ገሃደ ወአስተርአየ ከመ ሰብእ ይላል (ከእናቱ ጡቶች ምግብን እየለመነ እንደ ሕፃናት አለቀሰ ፥ በግልጥ ተመላለሰ ፥ እንደ ሰውም ታየ ፤ ቅ. ዲዮስቆሮስ ፲፯—፲፰) ።

## ወተሰቅለ በእንቲአነ ።

ስለ እኛ ተሰቀለ ።

(ማቴ. ፳፯ ፥ ማር. ፲፭ ፥ ሉቃስ ፳፫ ፥ ዮሐ. ፲፱) ። እንደ ሰማዕታት ዕሜትን ሽቶ ፥ እንደ ሌባ እንደ ወምበዴ ቀምቶ አይደለምና ስለ እኛ ይላል (ማር. ፲ ቍ. ፵፭) ። ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ እንዲቀጣበት ይገባው የነበረውን ቅጣት ክርስቶስ ተቀበለውና ያድነኛል ብሎ የሚያምንበትን እንዲያድን ሞተ ።

## በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ።

በጰንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ።

የተሰቀለበት ወራት ሌላ እንዳይሆን በጲላጦስ ዘመን አለ ፤ በማናቸው ጲላጦስ ያሉ እንደሆነ በጰንጤናዊው ይላል (ማቴ. ፳፯ ቍ. ፪ ፥ ሉቃስ ፫ ቍ. ፩ ፥ የሐዋ.፬ ቍ. ፳፯ ፥ ፩ ጢሞ. ፮ ቍ. ፲፫)።የእስራኤል አገር በሮማውያን እጅ ተወርሮ ስለ ነበረ በሮሜ የነገሡ ቄሣሮች ገዦችን አቆመውበታልና ገዙት ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፳፯



ዓመት እስከ ፲፬ ዓ. ም. የነገሠ አውግስጦስ ቄሣር ነው ፤ የእርሱ ተከታይ ከ፲፬—፴፯ ዓ. ም. የነገሠ ጢባርዮስ ነው ። በ፳፮ ዓ. ም. ጢባርዮስ ጲላጦስን ሾመው ፤ የይሁዳን አገር እስከ አሥር ዓመት ድረስ ገዝቶ ሲያበቃ በ፴፮ ዓ. ም. ጲላጦስ ተሻረ (ሉቃስ ፫ ቍ. ፩) ።

## ፯ ሐመ ።

መከራን ተቀበለ ።

እንደ ሰው አንሡኝ ፥ አቅኑኝ ፥ አገሙኝ ፥ ተዠሱኝ አላለም ፤ መጠውኩ መላትሕየ ለጽፍዐት አለ እንጂ (ጕንጬን ለመመታት ሰጠሁ ኢሳ. ፶ ቍ. ፮ ፥ ማር. ፲ ቍ. ፴፫—፴፬) ።

## ወሞተ ።

ሞተ ።

ሞት የሌለበት አምላክ ሞተ ፤ ሞተ እንዘ ኢይመውት በህላዌ መለኮቱ (በመለኮት ህላዌ ሳይሞት ሞተ) ። ሰው ከዘመዱ ከልጁ ከሚስቱ ከቤቱ ሲለይ ፥ ሳይወድ የመሳን ሞት ይሞታል ፤ እርሱ ግን በፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው ለየ ። ቅዱስ ጴጥሮስ ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ አለ (፩ ጴጥ. ፫ ቍ. ፲፰ ፥ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ) ።

## ወተቀብረ ።

ተቀበረ ፥

(ማቴ.፳፯ ቍ. ፶፯—፷፯ ፥ ማር. ፲፭ ቍ. ፵፪—፵፯ ፥ ሉቃስ ፳፫ ቍ. ፶-፶፯ ፥ ዮሐ. ፲፱ ቍ. ፴፰—፵፪) ። ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል ይላል (ማቴ. ፲፪ ቍ. ፵) ።

## ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ።

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ።

ምነው ዕለቱን በተነሣ ያሉ እንደሆነ ትንቢት ተነግሮለት የታቀደ ነው እንጂ ተስኖት አይደለም ። መጻሕፍተ ብሉያት ይነሣል ብለው ነበረና ተነሣ (ኢሳ. ፶፫ ፥ የሐዋ. ፪ ቍ. ፳፩—፴፪ ፥ መዝ.፲፭ ቍ. ፰—፲፩ ፥ ማር. ፱ ቍ. ፴፩ ፥ ሉቃስ ፳፬ ቍ. ፵፩) ።

www.ethiopianorthodox.org

ተነሣና ታየ (ማቴ. ፳፰ ፥ ማር. ፲፮ ፥ ሉቃስ ፳፬ ፥ ዮሐ. ፳—፳፩ ፥ ፩ ቆሮ. ፲፭) ።

<u>፰ ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ።</u>

በክብርም ወደ ሰማይ ዐረገ ።

በብርሃን ፥ በቅዳሴ ፥ በክብር ፥ በሥልጣን ዐረገ (የሐዋ. ፩ ቍ. ፩—፲፩ ፥ ፩ ጢሞ. ፫ ቍ. ፲፮) ። ሲያርግ ግን ዛሬ ከምድር ቦታ የለውም ወይም ሥልጣን የለውም ማለት አይደለም ፤ ቅዱስ ዳዊት ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ፥ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን እንዳለው ነው (መዝ. ፵፮ ቍ. ፭ ፥ እግዚአብሔር በዕልልታ ፥ ጌታችንም በመለከት ድምፅ ዐረገ)።

<u>ወነበረ በየማነ አቡሁ ።</u>

በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ።

በአባቱ ዕሪና ኖረ ፤ ምነው ቀኝና ግራ አሰኘው ቢሉ ሥልጣኑን ቀኝ ይለዋል ፥ ለወትሮ ቀኝ ቢይዝ ያጠብቃል ፥ ቢመታ ያደቃል ። እርሱም ደዌ ኃጢአትን ቀጥቅጦ የአባቱን ፈቃድ ፈጽሞ ስለ ወጣ በቀኝ ተቀመጠ (ዕብራ. ፩ ቍ. ፩—፬ ፥ ፩ ጴጥ. ፫ ቍ. ፳፪) ።

ንጉሥ የተጣላውን ሰናፊል አትታጠቅ ፥ በትር አታንሣ ፥ እንዲህ ካለ ቦታ አትውጣ ብሎ ቦታ እንዲወስንበት ፥ ቦታ ወሰነበት ማለት አይደለም ፤ በገዛ ራሱ ሥልጣን ተቀመጠ ይላል እንጂ ።

<u>፱ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ።</u>

ዳግመኛ በክብር ይመጣል ።

እንዳረገ ፥ በብርሃን ፥ በቅዳሴ ፥ በክብር ፥ በሥልጣን ይመጣል ማቴ ፳፬—፳፭ ፥ ማር. ፲፫ ፥ ሉቃስ ፳፩ ፥ የሐዋ ፩ ቍ. ፲፩ ፥ ፩ ተሰ. ፬ ቍ. ፲፭.—፲፰ ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ) ። አንደኛ ተወልዶ በመጣበት ጊዜ የሰውን ኃጢአት እንደ ተሸከመ ፤ ሁለተኛ ሲመጣ የሚጠባበቁት ያድናቸዋል (ዕብራ. ፱ ቍ. ፳፬—፳፰) ። ሊፈርድ እንጂ ወልደ ዮሴፍ ጠራቢ ሊሉት አይመጣም ።

<u>ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ።</u>

በሕይዋንና በሙታን እንዲፈርድ ፥

ይመጣል (ራእይ ፳ ቍ. ፲፩-፲፭) ። ሙታን ያላቸው እስከ ምጽአት ድረስ የሞቱ ናቸው ፤ ሙተው ቀሩ እንዳይባል ለፍርድ ይነሣሉ ። ሕያዋን ያላቸው በዕለተ ምጽአት በቁመና የተገኙ ናቸው ፤ ሕያዋን ሆነው ሸሽተው እያመልጡምና በፍርድ ጉባኤ ይገኛሉ ።



እንደ ሥራቸው ይቀበላሉ ፤ የተወደደ ሥራቸው ምንድን ነው ቢሉ ዝንቱ ውእቱ ግብረ እግዚአብሔር ከመ ትእመኑ በዘፈነዎ ውእቱ አለ (ዮሐ. ፮ ቍ. ፳፱ ፤ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው) ።

<u>፲ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ።</u>

ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም ።

ከእግዚአብሔር አብ እንጂ ከሌላ አልተቀበለውም (ሉቃ. ፳፪ ቍ. ፳፱) ፤ ለእግዚአብሔር አብ እንጂ ለሌላ አያሳልፈውም (፩ ቆሮ. ፲፭ ቍ. ፳፬) ። ዳዊት ሰሎሞን ቢገዙ ዓርባ ዓርባ ዘመን ነው ፤ ያውም እስከ ዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ነው ። የእርሱ ግን ፍጻሜ የለውምና (ራእይ ፳፪ ቍ. ፭) ።

<u>፲፩ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ።</u>

ጌታ ፥ ሕይወትን ሰጭ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።

መንፈስ ማለት ረቂቅ ማለት ነው (ዘፍ. ፩ ቍ. ፪ ፥ ዮሐ. ፬ ቍ. ፳፬) ። ቅዱስ ማለት ለእግዚአብሔር የተለየ ፥ አምላካዊ ማለት ነው (ዘሌዋ. ፲፩ ቍ. ፵፬) ። እግዚእ ማለት ጌታ ማለት ነው (፪ ቆሮ. ፫ ቍ. ፲፯-፲፰) ። ማሕየዊ ማለት ሕያው የሚያደርግ ማለት ነው (ገላ. ፮ ቍ. ፰ ፥ ፪ ቆሮ. ፫ ቍ. ፮) ።

ነፋስ ሲነፍስ ዛፍ ይወዘወዛል እንጂ ነፋሱ ራሱ አይታይም ። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ የረቀቀ ቢሆን ፍሬው በግልጥ የሚታይ ነው (ዮሐ. ፫ ቍ. ፰ ፥ ፩ ቆሮ. ፲፪ ቍ. ፲፬ ፥ ገላ. ፭ ቍ. ፲፮—፳፮) ።

<u>ዘሠረፀ እምአብ ።</u>

ከአብ የሠረፀ ፥

(ዮሐ. ፲፭ ቍ. ፳፮) ። ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ሠረፀ ። ከሰው ልብ የሠረፀ ቃል እንዲወስድ እስትንፋስ እንደሚወጣ ሠረፀ ማለት ወጣ ማለት ነው እንጂ ያልወጣበት ጊዜ አልነበረም ። የሰው እስትንፋስ ግን ዝርው ፥ ብትን ነው ፤ ሥሉስ ቅዱስ እንደዚህ አይደለም ፥ ለመንፈስ ቅዱስም አካል አለው ። ነገሩ ተመርምሮ የማያልቅ ምሥጢር ነውና የአቴና ኤጲስ ቆጶስ ዲዮናስዮስ በመንክር ግብር ልደተ ወልድ ወጸአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር አለ (ከአብ የወልድ አወላለድና የመንፈስ ቅዱስ አሠራረፅ የሚያስደንቅ ግሩም ሥራ ነው) ።

www.ethiopianorthodox.org

ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ።

ከአብና ከወልድ ጋር እንስገድለትና እናመስግነው ።

ወልድ የአምላክነት ተካፋይ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም የአምላክነት ተካፋይ ነው ፤ ትክክል ሆኖ መከበር ይገባዋል (ኤፌ. ፬ ቊ. ፬ ፡ ማቴ. ፳፰ ቊ. ፲፱) ። ቅዳሴውም መንፈስ ቅዱስ ዕሩይ ውእቱ ይላል (ቅዳሴ ማርያም ፺፮ ፡ መንፈስ ቅዱስ ትክክል ነው) ።

መቅዶንዮስ የሚባል መናፍቅ ለአብ መንበር አለው (መዝ ፺፮ ቊ. ፰) ፡ ለወልድም መንበር አለው (መዝ. ፵፬ ቊ. ፮) ፡ ለመንፈስ ቅዱስ ግን መንበር እንዳለው የተነገረበት ቦታ የለምና ሕፁፅ ነው ብሎ ተነሣ ። በቍስጥንጥንያ ጉባኤ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ግን አፈ ጉባኤው « ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ባለ መንበር መንፈስ ቅዱስ ብሎ ተርጕሞአል» ብሎ የተናገረውን ሰምተው መቅዶንዮስን አወገዙት (ኢሳ. ፮ ፤ የሐዋ. ፳፰ ቊ. ፳፭—፳፰) ።

ዘነበበ በነቢያት ።

በነቢያት አፍ የተናገረ ።

እንደ ቤት አድሮባቸው ፡ አከላታቸውን ልብስ ፡ ልቦናቸውን መቅደስ አድርጎ ያናግራቸው የነበረ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ነው (፪ ጴጥ. ፩ ቊ. ፳—፳፩ ፡ የሐዋ. ፬ ቊ. ፳፭ ፡ ሕዝ. ፲፫ ቊ. ፩—፯) ። እግዚአብሔር አናግሮአቸዋል ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን አስጽፎአቸዋልና እነዚህ መጻሕፍት የሃይማኖት ትምህርት መሠረት ናቸው (፪ ጢሞ. ፫ ቊ. ፲፬—፲፯) ።

፲፪ ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።

(ኤፌ. ፬ ቊ. ፩—፮ ፡ ም. ፳ ቊ. ፳፩—፵፫) ። ክርስቲያን የተባሉ ምእመናን ናቸው ፡ በጸጋ ጥምቀቱ አድሮባቸው አንድ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ እንጂ ነው ። በምን ጊዜ ክርስቲያን ተባሉ ያሉ እንደሆነ አርድእት ይባሉ ነበርና በኋላ ጳውሎስ በርናባስ ሲያስተምሩ ቢበዙ ክርስቲያን አሉአቸው ፤ ክርስቶሳውያን ማለት ነው (ሉቃ. ፲ ቊ. ፩—፲፪ ፡ የሐዋ. ፲፩ ቊ. ፳፭—፳፮) ።

ከምሥራብ አረሚ ከምሥራብ አይሁድ በላይ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን አንድ ነው (ኤፌ. ፪ ቊ. ፲፩—፳፪) ። ምእመናን የሚሰበሰቡበት



ቤት በወርቅ ፡ በብር ፡ በጭቃ ፡ በጨፈቃ ቢሠራ ፤ በግብፅ በእስክንድርያ ፡ በጻድቃን በሰማዕታት በእመቤታችን ስም ቢሠራ አንድ ነው ። ምእመናንም አንድ እምነት ያምናሉ ፤ አንድ ጥምቀት ይጠመቃሉ ፡ አንድ ሥጋው ደሙን ይቀበላሉና አሐቲ አላቸው ።

እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት ።

በሁሉም ዘንድ በምትሆን ፡ ሐዋርያት በሰበሰቧት

በቤተ ክርስቲያን እናምናለን ። የቤተ ክርስቲያን

የማእዘኑ ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃአል (ኤፌ. ፪ ቊ. ፳) ። ጌታችን በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ አለ (ማቴ. ፲፮ ቊ. ፲፰) ፤ ሐዋርያትም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ወንጌልን ሰበኩ (የሐዋ. ም. ፪) ፡ ያመኑትን አጠመቁአቸው (ማቴ. ፳፰ ቊ. ፲፰—፳ ።

፲፫ ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት ።

ለኃጢአትም ስርየት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።

(ኤፌ. ፬ ቊ. ፭) ። የአይሁድ ብዙ ጥምቀት ነበራቸው ፤ ከገበያ የሚገዙትን ሁሉ ፡ የሚበሉትን ፡ የሚዘሩትን ፤ የሚለብሱትን ያጠምቁ ነበርና ድውይንም ያጠምቁ ነበር ። ከዚህ ሁሉ የክርስቲያን ጥምቀት ተለየ (ማር. ፯ ቊ. ፫—፬ ፡ ዕብራ. ፮ ቊ. ፩—፪) ።

ሐተታ ፤ በአብ ስም ፡ በወልድ ስም ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም ፤ ቢጠመቁ አንድ ነው ። በዓርባ ቀን ፡ በሰማንያ ቀን ፡ በዓርባ ዘመን ፡ በሰማንያ ዘመን ቢጠመቁ አንድ ነው ። አንድም በሊቀ ጳጳስ ፡ በጳጳስ ፡ በኤጲስ ቆጶስ ፡ በቄስ እጅ ቢጠመቁ አንድ ነው ።

መጠመቅ የሚታይ ግዙፋዊ ምልክት ሆኖ የማይታየውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ያመለክታል ። ይኸውም ጸጋ ያድነናል ፤ ሆኖም ታጥቦ ወደ ኃጢአቱ ጭቃ የሚመለስ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋ የናቀ ነው ( ሮሜ ፮ ቊ. ፩—፲፩ ፤ ፩ ቆሮ. ፲ ቊ. ፩—፭ ፡ ዕብራ. ፮ ቊ. ፬—፲፪ ) ።

ጥምቀት የትንሣኤ ሙታን መርገፍ ነው ። ልብስን ጥሎ መግባቱ የዓለምን ግሥ ጣልሁ ማለት ነው ። ገብቶ መቆሙ ወልደ እግዚአብሔር በመልዕልተ መስቀል እንደ ቆመ እኔም ለመከራ መስቀል እቆማለሁ ማለት ነው ። ሦስት ጊዜ መጥለቁ ክርስቶስ ሦስት

www.ethiopianorthodox.org

ቀንና ሦስት ሌሊት በመቃብር አደረ ማለት ነው ። ክርስቶስ ልብስ መልበሱ ምንድር ነው ያሉ እንደሆነ በሥሉስ ቅዱስ እምነት ጸንቼ ምግባርን ሠርቼ የመንግሥተ ሰማያትን ተስፋ እንዲህ አለብሳለሁ ማለት ነው (ኤፌ. ቀ. ፬ ፳፪—፳፬) ።

<u>፲፬ ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን</u> ።

የሙታን ትንሣኤን በተስፋ እንጠባበቃለን ።

ከፈረሱ ከበሰበሱ በኋላ አካል አግኝተው ታድሰው ሙታን ይነሣሉ. (፩ ቆሮ. ም. ፲፭ ፣ ራእይ ም. ፳፩) ።

አንድም ፤ እንዘ ንሴፎ ይላል ፤ ሙታን እንዲነሡ አምነን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።

<u>ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም</u> ።

የሚመጣውን ዘለዓለማዊ ሕይወት ፣

በተስፋ እንጠባበቃለን (ማቴ. ፳፪ ቀ. ፴ ፣ ራእይ ፳፪ ቀ. ፭) ። የማይወሰን የማይመጠን ይህን ያህላል ይህን ይመስላል የማይሉት ክብር ይሰጠናል ፤ ክብሩስ እንደ ምን ነው ቢሉ ምእመናን በዚህ ዓለም ውስጥ ተመላልሰው የክርስቶስን ነገር ሽተው እንደተከተሉት በመንግሥተ ሰማያት ሆነው ከክርስቶስ ጋር ይሆናሉና ደስ ይላቸዋል (ፊል. ፩ ቀ. ፳፩—፳፫) ።

<u>አሜን</u> ።

አሜን ።

የታመነ እውነተኛ ነው ፤ የክርስቲያን ልጅ ሁሉ ይወቀው (፪ ጢሞ. ፫ ቀ. ፲፬—፲፯) ።

---

<u>ቅድስት ሥላሴ</u>

የቅድስት ሥላሴ ነገር በጌታችንም በሐዋርያትም አፍ የተገለጠ ነውና የማይመረመር ምሥጢር እንደሆነ ቢመስለን ስንኳ ነገሩ እንደ ተገለጠልን መቀበል ይገባናል ። ሆኖም ለሰው ግራ እንዳይገባው ሊቃውንት በብዙ ምሳሌዎች መስለውታል ። ሥላሴን በውኃ እንደ ሆነ ፣ አካላትን በውኃነቱ ፣ በመናወጡ ፣ በርጥበቱ መስለዋል ። ሥላሴን በፀሐይ እንደሆነ ፣ አካላትን በከበቡ ፣ በብርሃኑ ፣ በሙቀቱም መስለዋል ። ሥላሴን በወይን እንደሆነ ፣ አካላትን በግንዱ ፣ በፍሬው ፣ በልምላሜው መስለዋል ። ሥላሴን በነፍስ እንደሆነ ፣ አካላትን በለባዊነት፣ በነባቢነት፣ በሕያውነት መስለዋል ። ሥላሴንም በሰው እንደሆነ፣



አካላትን በልቡ ፣ በቃሉ ፣ በእስትንፋሱ መስለዋል ። ሌሎችም በማገጥ ቅጠል መስለውታል ፤ ቅጠሉ በሦስት የተከፋፈለ ነው እንጂ አንድ ቅጠል መሆኑ አይቀርምና ።

እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ ምሳሌዎች ብቻ ናቸውና የቅድስት ሥላሴን ነገር ጨርሰው ሊያስረዱን አይችሉም ። ቅዱስ አውግስጢኖስ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ «የማይታየው ባሕርይ----ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል» ብሎ እግዚአብሔር በፍጥረቱ እንደ ተገለጠ አስተማረ (ሮሜ. ፩ ቀ. ፳-፳፩) ፤ ደግሞም «እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ» ብሎ በእግዚአብሔር አምሳል የተሠራው ሰው የእግዚአብሔርን ነገር እንደሚያስረዳ አስተማረ ( ዘፍ. ፩ ቀ. ፳፯) ። በሰው አእምሮ ውስጥ የሆነውን ነገር የማስታወስ ችሎታ አለ ፤ ነዋሪነት እንበለው ። ደግሞም ከጊዜ ወደ ጊዜ ራስነቱን የመገንዘብ ችሎታ አለ ፤ ማስተዋል (ለባዊነት) እንበለው ። እንዲሁም አንዱን ነገር የማሰብ የመውደድም ችሎታ አለ ፤ ፈቃድ እንበለው ። እነዚህ ሦስቱ የቅድስት ሥላሴ ምሳሌዎች ብቻ አይደሉም ፤ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረ ሰው የሆነ የቅድስት ሥላሴ እትማት ነው እንጂ ብሎ አስተማረ ።

ሰው እንዳይወድቅበት ጉድጓድ ይታጠራል ፤ እንዲሁም የአነ ሰባልዮስ የእነአርዮስ መወገዝ ከመሳሳት ይጠብቀናልና ግዝታቸው የሃይማኖት ወሰን ሆኖአል ። የቀናውን ሃይማኖት ይዘን የማይመረመረውን የቅድስት ሥላሴን ነገር ማመን ይገባናል ።

<u>የእግዚአብሔር ሥልጣን</u>

በዕብራይስጥ እግዚአብሔርን ጸባኦት ይላል ፤ የሠራዊት ጌታ ማለት ነው ። ይኸውም በግሪክ ፓንቶክራቶር (መላኬ ኵሉ ፣ ሁሉን የሚገዛ ) ማለት ነው ። ደግሞም አኃዜ ኵሉ (ሁሉን የሚይዝ) እንላለን ። እግዚአብሔር መልካም ሆኖ ሁሉን ከያዘ በዓለም ውስጥ ያለ ክፋት ለምን ይበዛል እያሉ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖር ወይም የእግዚአብሔርን ቸርነት እስከ መካድ ደርሰዋል ።

እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም እንዴት አድርጎ ይመራዋል? ጌታችን መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብሎ ሰበከ (ማቴ. ፬ ቀ. ፲፯) ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ተቋቁሞአል እንጂ ገና እስከ ሙላቱ አል ደረሰም ። አጀማመሩ ዘርን እንደ መዝራት ነበረ ፤ አፈጻጸሙ ምርትን

www.ethiopianorthodox.org

እንደ መከተት ይሆናል (ማቴ. ፲፫ ቁ. ፳፬-፴) ። በዛሬ ዘመናችን የእግዚአብሔር መንግሥት በመስፋፋትና በማደግ ላይ ነው ፤ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ኃይሉን ገልጦ ክፉዎችን አጥፍቶ ነገሩን ቶሎ እንዳይጨርሰው ታጋሽ ሆኖ የሚቹን ሞት የማይፈልግ አምላክ ነው። (ሕዝቅ. ፲፰ ቁ. ፴፪) ፤ ከዚህም በላይ ሰው የግድ ሳይገዛለት ወዶ ልጅነትን እንዲወርስ ፈቀደ (ሮሜ ፰ቁ. ፲፬-፲፯ ፤ ኤፌ. ፩ ቁ. ፩-፱) ።

ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ የፈቃድ ነፃነት ኖሮታል ፤ አዳምና ሔዋን ከዚያ ዛፍ ለቅማችሁ አትብሉ ተብለው ከታዘዙ ሊበሉ ላይበሉም ቻሉ ። ምርጫቸውን አድርጎ የኃጢአትን ነገር ወደ ሰብአዊ ክበብ አገቡት (ዘፍ. ፪ ፤ ሮሜ ፭ ቁ. ፲፪-፳፩) ። እግዚአብሔርም የዐመፀበትን ሰው ወደ እኔ ተመለስ ፤ ወደ መንግሥቴም ግባ ብሎ ይጠራዋል እንጂ የግድ አይለውም ። የግድ አለማለቱ ስለ ተሳነው አይደለም ፤ የጀመረውን ሁሉ ወደ አሰበው ፍጻሜ ሳያደርስ እንደማይቀር ጥርጥር የለም (ራእይ ም. ፳—፳፪ ) ።

ጥርጥር አለበት እንጂ ፤ ወይም እግዚአብሔር ክፉውን ፈጠረና ደግ አምላክ አይደለም ፣ ወይም ክፉውን አልፈጠረምና ደግነት ክፉትን ክፉትም ደግነትን እንደሚያሸንፍ በምን ታወቀ የሚል ጠያቂ ቢኖር አጠያየቁ ክፉት ከምን መነጨ የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል ። ከአዳም ከሔዋን መጣ እንዳይባል እባቡ አሳታቸው ፤ እባቡም ሰይጣን ነው (ዘፍ. ፫ ፤ ራእይ ፳ ቁ. ፩-፱) ። ሰይጣንን ያሳተ ነበረ እንዳይባል ከእርሱ በቀር የክፉት ምንጭ ያለ አይመስልም (፩ ዮሐ. ፫ ቁ. ፰ ) ። ክፉ ሆኖ ተፈጠረ ) እንዳይባል እግዚአብሔር መልካም ፈጣሪ ሆኖ የፈጠረውን ሁሉ መልካም እንደሆነ አየው (ዘፍ. ፩ ቁ. ፴፩ ።)

ሊቃውንትም ሕዝቅኤል ፳፰ ቁ. ፲፩-፲፱ እና ኢሳ. ፲፬ ቁ. ፫-፳፩ አንብበው እነዚህ ቃሎች ስለ ጢሮስና ስለ ባቢሎን ነገሥታት ምንም የተጻፉ ቢሆኑ ነቢያት የሰይጣንን አወዳደቅ ተገንዝበው የዓለማውያን ነገሥታት ምሳሌ አድርገውታል ብለው በይመስላል ከገመቱ በኋላ ሰይጣን በትዕቢት ተነፍቶ የእግዚአብሔርን ሥልጣን የቀማ መልአክ ይሆናል ብለዋል ። ቢሆንም ባይሆንም ሰይጣን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የሆነ ስጊዜው ነውና መጠቃቱ አይቀርም (፩ ጴጥ. ፭ ቁ. ፰ ፤ ራእይ ፳ ቁ. ፲ ) ።

## ምዕራፍ ፱ ።

# ጸሎተ ሃይማኖት ዘአፍራቅያ ።

ቅዱስ አትናቴዎስ በ፪፻፺፰ ዓ. ም. ገደማ ተወልዶ በ፫፻፸፫ ዓ. ም. የሞተ ታላቅ ሊቅ ነው ። የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነና ፍሬምናጦስን አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ብሎ የጵጵስናውን ማዕርግ ሰጠው ። የአርዮስን ትምህርት በኃይል ተቃወመውና ብዙ መጻሕፍትን ደረሰ ።

ከታች የተጻፈው ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ስለ ቅድስት ሥላሴ የደረሰው ነው ፤ ጸሎተ ሃይማኖት ዘአፍራቅያ (የአፍሪቃ) ተብሎ አንዳንድ ጊዜ በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበው ውስጥ ተጽፎ የሚገኝ ነው ።

በምዕራባዊው ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዓት ተብሎ የታወቀ ሌላ ውሳኔ አለ ። የቅድስት ሥላሴን ነገር በመግለጡ የአፍራቅያን ጸሎተ ሃይማኖት ይመስለዋል ። እንጂ ቃሉ ያጠረና የተለየ ነው ፣ አትናቴዎስ ራሱ የጻፈው አይመስልም ። ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት አያሌዎች ይህን ቃል ስለሚቀበሉት የምዕራባዊ ቤተ ክርስቲያን የአትናቴዎስ ጸሎተ ሃይማኖት ብለን ጨምረን ጽፈነዋል ።

### ጸሎተ ሃይማኖት ዘአፍራቅያ

ይቤ ኵሉ ለለአሐዱ ዘይፈቅድ ይድኃን ይኅሥሥ ሃይማኖተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ይእቲ ሐዋርያዊት ፤

እንተ ትሜህር ፅምረተ ሥላሴ በኢቱሳሔ ፣

ወድሙረ በኢቡዓዴ ።

አብ በአካሉ ወበግጻዌሁ ዘኢይትዌለጥ እምከዊነ አብ

ኀበ ከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፤

ወወልድ በአካሉ ወበግጻዌሁ ዘኢይትዌለጥ እምከዊነ ወልድ ኀበ

ከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ፤

ወመንፈስ ቅዱስ በአካሉ ወበግጻዌሁ ዘኢይትዌለጥ እምከዊነ መንፈስ

ቅዱስ ኀበ ከዊነ አብ ወወልድ ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዘ ንዋን በፅምረት ፤
ወድሙራን በኢተፈልጦ ።

አብ ወላዲ ፡ ወኢተወላዲ ።
ወልድ ተወላዲ ፡ ወኢወላዲ ፤ አርአያ መልክእ ዘህላዌ አብ ።
ወመንፈስ ቅዱስ ኢወላዲ ወኢተወላዲ ፤
ኢሕፁፅ ወኢፍድፉድ ፡
ኢነኪር ወኢብዑድ እምህላዌ አብ ወወልድ ።

አሐዱ መለኮቶሙ ፡
ወአሐቲ ስብሐተ መንግሥቶሙ ፤
አሐዱ አርአያ ወፀዳል ፡
አሐዱ ሕሊና ወአሐቲ ሥምረት ዘአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ።
ከመዝ ውእቱ ፅምረተ ህላዌሁ ለመለኮተ አምላክነ ።
ሥልሰት ዘኢትትፈለጥ ፤
ድምርት ዘኢትቶሳሕ ፡
ዕሪት እንተ ኢተሐፅፅ ወኢትፈደፍድ ፡
ምልዕት ዘኢትቀብል ፡
ስፍሕት በኵለሄ ዘኢትትደነገግ ።

አልባቲ ጠፈር በላዕሉ ዘይጼልላ ፡
ወኢመሠረት በታሕቱ ዘይፀውራ ።
በከመ ትትሌዓል እምሰማየ ሰማያት
ከማሁ ትቀሊ እምቃላየ ቀላያት ።
በከመ ኢያገምራ ርኅበ ዓለም
ኢያጽዕቃ መጽብብ ዘመቅፀን ።
ትፌትኖ ለልብ በማኅቶተ ጥበብ ፡
ተአምር ዘይመጽእ ከመ ዘኀለፈ ።

አብ ኢፍጡር ፡ ዘወለዶ ለወልድ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።
ነአምን እንከሰ ከመ ወለዶ ወኢፈጠሮ ፤
ወመንፈስ ቅዱስ ኢወለደ ከመ አብ ፡ ወኢተወልደ ከመ ወልድ ፡
ኢተገብረሂ ወኢተፈጥረ ።
አላ ፈጠረ ዓለመ እንዘ ኢያጸርዕ ሥላሴሁ እምህላዌ አብ ወወልድ ።
አብ እግዚአብሔር ፡
ዘኢየዐቢ እምወልዱ በከዊነ አብ ።
ወልድ እግዚአብሔር ፡



ዘኢይንእስ እምአቡሁ በእንተ ከዊነ ወልድ ።
ወመንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፡
ዕሩየ መለኮት ፡ ወኅቡረ ህላዌ ፡
ዘኢይትፈለጥ እምአብ ፡ ወኢይትሌለይ እምወልድ ።

አብ ህልው ዘአንበለ ጥንት ፡
ወልድ ህልው ዘእንበለ ጥንት ፡
ወመንፈስ ቅዱስ ህልው ዘእንበለ ጥንት ፤
ኢተድኅረ አሐዱ እምካልኡ ፡
ወካልእ እምሣልሱ ።
አብ አምላክ ፍጹም ፡
ወልድ አምላክ ፍጹም ፡
ወመንፈስ ቅዱስ አምላክ ፍጹም ።

ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር ፤
ዘኢያጸርዕ ትሥልስቶ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለመ ዓለም ።

አብ እግዚእ ዘላዕለ ኵሉ ፡
ወልድ እግዚእ ዘላዕለ ኵሉ ፡
ወመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ዘላዕለ ኵሉ ።

ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አጋእዝተ ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር ፤
ዘኢያበጥል ትሥልስቶ በአጽናፈ አጽናፍ ።

ወአመ ፈቀደ እግዚአብሔር ይግበር መድኀኒቶ ለእጓለ እመ ሕያው ፈነዎ ለገብርኤል ሀገረ ገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ኀበ ድንግል እንተ ተፍኅረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ዘእምቤተ ዳዊት ፤ ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም ።

ቦአ መልአክ ኀቤሃ ወይቤላ

«ተፈሥሒ ፍሥሕት ። እግዚአብሔር ምስሌኪ ፡ ወቡርክት አንቲ እምአንስት ። ወናሁ ትፀንሲ ፡ ወትወልዲ ወልደ ፡ ወትሰምዮ ስሞ ኢየሱስ ፤

ውእቱ ዐቢይ ፡ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ፡
ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ መንበረ ዳዊት አቡሁ ፡
ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ፡
ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ።»

www.ethiopianorthodox.org

ወትቤሎ ማርያም ለመልአክ

«እፎ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ ።»

አውሥአ መልአክ ወይቤላ

«መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ። »

መንፈስ ቅዱስ ሐወፃ ለቀድሶ ፤ና

ባሕቱ ውእቱሰ ኢተሰብአ በጠባይዒሃ ።

ወካዕበ ይቤላ ።

«ኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ። »

ኃይለ መለኮተ አብ አጽንዓ ለከዊነ እመ ወልዱ ፤

ባሕቱ ውእቱሰ ኢተሠገወ እምኔሃ ።

ወሶበ ሠለሰ ብሂሎታ

«ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወልደ ልዑል ፤»

ውእተ ጊዜ ትቤ ማርያም

«ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ።»

ውእተ ጊዜ ኮና ወልደ እግዚአብሔር ወልድ ። ወበዝ ነአምር ከመ አልቦቱ ቱስሕት ለመለኮተ ሥላሴ ። ወእመሰ ቦቱ ቱስሕት ለመለኮተ ሥላሴ እምተሠገዉ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እማርያም ፤ ኢያሰ ፈዋ መልአክ ወሊደ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ዘእንበለ ዳዕሙ ወሊደ ወልድ ዘልዑል ።

ነገራ መልአክ አሐደ ዘይቄድሳ ፤

ወአሐደ ዘያጸንዓ ፤

ወአሐደ ዘይትወለድ እምኔሃ ።

ዘሂ ቀደሳ እግዚአብሔር ፍጹም በህላዌሁ ዘእምኔሁ ይትወሀብ ነቅዓ ቅድሳት ።

ዘሂ አጽንዓ እግዚአብሔር ፍጹም በህላዌሁ ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ ፤

ወማየ ባሕርኒ እንዘ ኢተዓዱ እምወሰና ፤

ወምድርኒ እንዘ ኢትምሖ እምዝብጠተ መዋግዲሃ ።

ወዘሂ ተወልደ እምኔሃ እግዚአብሔር ፍጹም በህላዌሁ ዘአስተሰነአወ እሳተ ምስለ ዕፀ ጳጦስ ፤

እንዘ ዕፃ ኢትውዒ



ወእሳት ዘዲቤሃ ኢይጠፍእ ።

አስተሰነአወ ነበልባሎ ምስለ ማኅፀነ ሥጋ ዕብስት ፤

እንዘ ማኅፀነ ብእሲት ኢትውዒ

ወነባልባለ መለኮት ኢይትመየጥ እምህላዌሁ ።

ወኮነ ፍጹመ ሰብአ ከማነ ፤

እንዘ እግዚአብሔር ፍጹም ከመ አቡሁ ።

ተሐቅፈ በአብራኪ እሙ ፤

እንዘ ይመልእ ዓለመ ከመ ወላዲሁ ።

ተሐፅነ በአጥባተ እሙ ፤

እንዘ ሲሳየ ሰብእ ወእንስሳ ውስተ እዴሁ ።

ወልሀቀ በበሕቅ ፤

ወወርዘወ በአምጣነ ብእሲ ፤

ወአስተርአየ ውስተ ዓለም ።

አኮ በምትሐት አላ በዐፅም ፤ ወደም ፤ ወፀጕር ፤ ወአሥራው ፤ እንዘ ያንሶሱ ወያንሰሐስሖ መንፈሰ ሕይወት ዘጠባይዕ እንተ እኁለ እመ ሕያው ።

ወእለሰ ይብልዎ

«አልቦቱ ነፍስ ወልብ ፤

ወመለኮቱ ኮኖ ህየንተ ነፍስ ወልብ ፤»

ሕፁፃነ አእምሮ እሙንቱ እምልበ እንስሳ ።

ወእለሂ ይብልዎ

«ምትሀት ውእቱ»

ምትሀት ሃይማኖቶሙ እንተ ኢትትሜካህ በሕማማተ ሥጋሁ ለመድኃኒነ ።

ንሕነሰ ነአምን ከመ ደከመ ወሀፈወ ፤

ርኅበ ወጸምአ በሕገ ትስብእት ፤

ወገብረ መንክራተ በሥርዓተ መለኮት ።

ወበዮርዳኖስ ተጠምቀ በእደ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ። ወስምዐ ኮነ ሎቱ አብ እንዘ ይብል

«ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ፤ ወሎቱ ስምዕዎ ። »

ወእምዝ ርእየ ተሠጠ ሰማይ ፤ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ዲቤሁ በር

www.ethiopianorthodox.org

እየተ ርግብ ፀዓዳ ። ናሁኬ ሤመ ሥላሴሁ ውስተ ምጥማቃት ከመ ይትአመር አሠረ አምልኮቱ ለዐቢይ ክርስቲያን ።
ወእምዝ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ

« ሑሩ ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ ፤ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈሰ ቅዱስ ። »

ሐመ በፈቃዱ ፣ ወጥዕመ ሞተ በሥጋ ።
ወተቀብረ በሥምረቱ ።
ወተንሥአ በኃይለ መለኮቱ አመ ሣልስት ዕለት ።
ወካዕበ ይመጽእ ከመ ይፍድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ ።
ወንሕነኒ ነአምን ሥሉስ ዘእንበለ ተፈልጦ ፣

ወኅቡረ ዘእንበለ ተቶስሖ ፤
ከመ ኢሕፁፅ አሐዱ እምካልኡ ፣
ወካልኡ እምሣልሱ ፣
ኢአሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን ።
ወካዕብ ነአምን ከመ ኢየሐፅፅ ትስብእቱ እመለኮቱ እምድኅረ አሐደ ከዊን ።
ወዓዲ ነአምን ከመ ኢተመይጠ መለኮቱ ለከዊነ ትስብእት ፣
ወኢትስብእቱ ለከዊነ መለኮት ።

ዘንተ እንዘ ነአምን ፣ ወዘንተ እንዘ ንትአመን ፤ ንትሐፀን በሐሊበ አጥባቲሃ ለቤተ ክርስቲያን እንዘ ናወግዝ ኵሎ ዕልወተ ዘመናፍቃን ለዓለመ ዓለም ፤ አሜን ።
ወላዕሌነ ይኩን ምሕረቱ እስከ ለዓለም ፤ አሜን ።

ዘንተ ሃይማኖተ ጸሐፈ አትናትዮስ ዘሀገረ ባባ ፣ እንተ ይእቲ መንበረ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ።

ወአምጽአ ምስር ዛን ዘብሔረ አፍራቅያ እስከ ብሔረ ኢትዮጵያ ።

ወአዕለውክዋ አነ ጊዮርጊስ ሰግላዊ እንዘ እግዚአ ይረድእ ፣ ወቃሎ ያጸንዕ በትእምርት ዘይተሉ ፣ አሜን ።



## የአፍራቅያ ጸሎተ ሃይማኖት ፣

እንዲድን የሚፈልግ እያንዳንዱ ሁሉ ሐዋርያዊ በሚሆን በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ያለውን ሃይማኖት ይሻ ፤
መቀላቀል የሌለውን የሥላሴን አንድነት ፣
መለየትም የሌለውን መገናኘቱን ያስተምራል ።
አብ በአካሉና በህላዌው አብ ከመሆን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን የማይለወጥ ነው ፤
ወልድ በአካሉና በህላዌው ወልድ ከመሆን አብና መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን የማይለወጥ ነው ፤
መንፈስ ቅዱስም በአካሉና በህላዌው መንፈስ ቅዱስ ከመሆን አብና ወልድ ወደ መሆን የማይለውጥ ነው ።
በአንድነት ተያይዘው ፣
ባለመለየትም ተገናኝተው የሚኖሩ ናቸው ።
አብ ወላጅ ነው ፣ ተወላጅ አይደለም ።
ወልድ ተወላጅ ነው ፣ ወላጅ አይደለም፤ የአብ ህላዌ መልክ አምሳል ነው ።

መንፈስ ቅዱስም ወላጅ አይደለም ፣ ተወላጅ አይደለም ፤
ከአብና ከወልድ ህላዌ ተለይቶ የጐደለ ወይም የበዛ ፣
የተለየ ወይም የራቀ አይደለም ።

አምላክነታቸው አንድ ፣
የመንግሥታቸውም ክብር አንድ ነው ፤
የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ አምሳልና ብርሃን አንድ ፣
ሕሊናና ውዴታ አንድ ነው ።
የአምላካችን የአምላክነቱ ህላዌ አንድነት እንደዚህ ነው ።
ሦስት ሆኖ የማይለይ ፣
ግንኙ ሆኖ የማይቀላቀል ፣
ትክክል ሆኖ የማይጐድልና የማይበዛ ፣
ሙሉ ሆኖ የማያንስ ፣
ሰፊ ሆኖ ዘወትር የማይወሰን ።
በላይ ሆኖ የሚጋርደው ጠፈር የለም ፣
በታች ሆኖ የሚደግፈው መሠረት የለም ።

www.ethiopianorthodox.org

ከሰማየ ሰማያት ከፍ ከፍ እንደሚል
እንዲሁም ከቀላየ ቀላያት ይጠልቃል ።
የዓለም ስፋት እንደማይወስነው
የጠባቡ ጠባብ እያጣብበውም ።
በጥበብ ፋና ልቡን ይፈትናል ፤
የአለፈውን እንዳወቀ የሚመጣውን ያውቃል ።

አብ የተፈጠረ አይደለም ፤ ዓለም ሳይፈጠር ወልድን የወለደ ነው ።
እንግዲህ እንደወለደውና እንዳልፈጠረው እናምናለን ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ ሆኖ አልወለደም ፤ እንደ ወልድ ሆኖ አል ተወለደም ፤ አልተሠራም ፤ አልተፈጠረም ፤
ነገር ግን ከአብና ከወልድ ህላዌ ሥላሴነቱን ሳያስቀር ዓለምን ፈጠረ ።

አብ ፤ አብ በመሆኑ ከወልድ የማይበልጥ
እግዚአብሔር ነው ።
ወልድ ፤ ወልድ በመሆኑ ምክንያት ከአብ የማያንስ
እግዚአብሔር ነው ።
መንፈስ ቅዱስም በአምላክነት ትክክል ፤ በህላዌ አንድ የሆነ ፤
ከአብ የማይለይ ከወልድ ከፍ ከፍ የማይል
እግዚአብሔር ነው ።

አብ ጥንት የሌለው ነዋሪ ነው ፤
ወልድ ጥንት የሌለው ነዋሪ ነው ፤
መንፈስ ቅዱስም ጥንት የሌለው ነዋሪ ነው ።

ከአንዱ ሁለተኛው
ከሁለተኛው ሦስተኛው ወደ ኋላ አይልም ።
አብ ፍጹም አምላክ ነው ፤
ወልድ ፍጹም አምላክ ነው ፤
መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ነው ።

ዓለም ሳይፈጠር ጀምሮ ለዘላለም ሦስትነቱን የማያስቀር
አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም ፤
አብ በሁሉ ላይ ያለ ጌታ ነው ።
ወልድ በሁሉ ላይ ያለ ጌታ ነው
መንፈስ ቅዱስም በሁሉ ላይ ያለ ጌታ ነው ።



ከዳር እስከ ዳር ድረስ ሦስትነቱን የማያጠፋ
አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሦስት ጌቶች አይባሉም ።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መድኃኒትነቱን ለማድረግ በፈቀደ በት ጊዜ ፤ ከዳዊት ትውልድ ተወልዶ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ድንግል ፤ ናዝሬት ወደሚባል ወደ ገሊላ አውራጃ ከፍል ገብርኤልን ላከ ። የድንግሊቱ ስም ማርያም ናት ።

መልአኩ በእርስዋ ዘንድ ገባ ፤ አላትም
« በደስታ ደስ ይበልሽ ፤ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ። ከሴቶችም መካከል የተባረክሽ ነሽ ። እነሆ ትፀንሻለሽ ፤ ልጅን ትወልጃለሽ ፤ ስሙን ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ ።
ታላቅ ይሆናልና የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል ፤
እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ፤
በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፤
ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ። »

ማርያም ለመልአኩ እንዲህ አለች ፤
« ወንድን ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል ። »
መልአኩ መለሰ ፤ እንዲህ አላት ፤
«መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፤ »
መንፈስ ቅዱስ ለመቀደስ ጐበኛት ፤
በእርስዋ ጠባይ ብቻ ሰው አልሆነም ።
ደግሞ አላት ፤
«የልዑል ኃይል ይጸልልልሻል ። »

የአብ አምላክነት ኃይል የወልድ እናት ለመሆን አጸናት ፤
ከእርስዋ ሥጋ ብቻ ሥጋ አልሆነም ።
እንደገናም አላት
« ከአንቺ የሚወለድ የልዑል ልጅ ቅዱስ ይሆናል ። »
በዚህም ጊዜ ማርያም አለች
« እንዳልሽኝ ይሁንልኝ ። »

በዚህም ጊዜ ወልደ እግዚአብሔር ልጅ ሆነላት ። በሥላሴ አምላ ክነት መቀላቀል እንደሌለበት በዚህ እናውቃለን ። በሥላሴ አምላ ክነት መቀላቀል ቢኖር ኖሮ አብና ወልድ ፤ መንፈስ ቅዱስም ከማ

www.ethiopianorthodox.org

ርያም ሥጋ በሆኑ ነበር ፤ መልአክ የልዑልን ልጅ ለመውለድ እንጂ አብንና መንፈስ ቅዱስን ለመውለድ ተስፋ አልሰጣትም ።

መልአኩ አንድ ጊዜ የሚቀድሳትን
አንድ ጊዜ የሚያጸናትን ፣
አንድ ጊዜ ከእርስዋ የሚወለደውን ነገራት ።

ከራሱም የቅድስና ምንጭ የሚሰጥ ፣ በህላዌውም ፍጹም የሆነ እግዚአብሔር ቀደሳት ።

የባሕር ውኃ ወሰኑን ሳያልፍ ፣
ምድርም በማዕበል ተመትቶ ሳይጠፋ
በውኃ ላይ ምድርን ያጸና ፣
በህላዌው ፍጹም የሆነ እግዚአብሔር አጸናት ።

በላዩ እሳት ሳይጠፋና
ቅጠሉ ሳይቃጠል
እሳትንና ቍጥቋጦውን አንድ ያደረገው ፣ በህላዌውም ፍጹም የሆነ እግዚአብሔር ከእርስዋ ተወለደ ።

የሴቲቱ ማሕፀን ሳይቃጠል ፣
የአምላክነት ነበልባል ከህላዌው ሳይመለስ
ነበልባሉንና ደካምነት ያለውን የሥጋ ማሕፀን አንድ አደረጋቸው ።

እንደ አባቱ ፍጹም እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ
እንደ እኛ ፍጹም ሰው ሆነ ።

እንደ ወላጁ ሆኖ ዓለሙን ሲመላ ሳለ
በእናቱ ጉልበት ታቀፈ ።

የሰውና የእንስሳ ምግብ በእጁ ሳለ
በእናቱ ጡት ጠባ ።

በመጠን አደገ ፣
እንደ ሰው ሆኖ ጐለመሰ ፣
በዓለምም ውስጥ ታየ ።

በምትሀት (በመሰል) አይደለም ፣ በሰው ልጅ ጠባይ የሕይወት መንፈስ ሲያመላልሰውና ሲያንቀሳቅሰው አጥንት ፣ ደም ፣ ጠጕር ፣ ጡንቻ ኖሮት ነው እንጂ ፤



« ነፍስና ልብ የለበትም ፣
በነፍስና በልብ ፈንታ አምላክነቱ ሆኖታል »
የሚሉት ከእንስሳ ልብ አእምሮ ጐደሎዎች ናቸው ።

« ምትሀት ነው »
የሚሉት
መድኃኒታችን በሆነ በሥጋው ሕማማት የማይኰሩ ስለ ሆነ ሃይማታቸው ምትሀት ነው ።

እኛም « በሰውነቱ ረገድ ደከመ ፣ ወዛ ፣
ተራበ ፣ ተጠማ ፤
በአምላክነቱ ረገድ ተአምራትን አደረገ » ብለን እናምናለን ።
በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ። አብ እንዲህ ሲል ምስክር ሆነለት ፤
« የምወደው ልጄ ይህ ነው ፣ እርሱን ስሙ ። »
ከዚህ በኋላ ሰማይ ተሠንጥቆ አየው ፤ መንፈስ ቅዱስም በነጭ ርግብ አምሳል በእርሱ ላይ ወረደ ። እነሆ ፣ ለበሰለ ክርስቲያን የአምልኮት መንገድ ምልክት እንዲሆን በማጥመቂያ ውስጥ ሥላሴነቱን ሾመ ።

ከዚህ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ አላቸው ፤
« ሂዱ ሕዝቦችን ሁሉ አስተምሩ ፤ ስታጠምቁአቸው
በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም በሉ ። »
በፈቃዱ መከራን ተቀበለ ፣ በሥጋ ሞትን ቀመሰ
በውዴታው ተቀበረ ።
በሦስተኛው ቀን በአምላክነቱ ኃይል ተነሣ ።
እንደ ሥራው መጠን ለሁሉ እንዲከፍል ዳግመኛ ይመጣል ።

መለየት የሌለበትን ሦስትነት ፣
መቀላቀል የሌለበትን አንድነት ፣
ለአንዲት ሰዓት ፣ ለዓይን ጥቅሻ ስንኳ ከሁለተኛው አንዱ ፣
ከሦስተኛው ሁለተኛው ጕድለት እንደሌለበት እናምናለን ።

ደግሞም አንድ ከመሆን በኋላ ከአምላክነቱ ሰውነቱ እንደማይጐድል እናምናለን ።
ደግሞም ሰውነቱ ለመሆን አምላክነቱ ፣
አምላክነቱ ለመሆን ሰውነቱ እንዳልተመለሰ እናምናለን ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህን ስናምን ፥ ይህንም ስንታመን ፤ የመናፈቃንን ለውጥ ለዘለዓለም ስናወግዝ የቤተ ክርስቲያንን ጡቶች ወተት እንጠባለን ፤ አሜን ።

ምሕረቱ ለዘላለም በእኛ ላይ ይሁን ፤ አሜን ።

የጴጥሮስና የጳውሎስ ወንበር ያለበት የባባ አገር ሰው አትናትዮስ ይህን ሃይማኖት ጻፈ ።

የአፍራቅያ አገር ሰው ምስር ቁን ወደ ኢትዮጵያ አመጣው ።

እግዚአብሔርም ሲረዳና በሚከተለው ምልክት ቃሉን ሲያጸና እኔ ጊዮርጊስ ሰግላዊ ተረጐምሁት ፥ አሜን ።

———O———

<u>የምዕራባዊ ቤተ ክርስቲያን የአትናቴዎስ ጸሎተ ሃይማኖት</u> እንደሚከተለው ነው ፤ ( መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይሠርፃል ማለቱ የካቶሊኮችና ተከታዮቻቸው አስተያየት ነው እንጂ የኢትዮጵያ ሆነ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን አይቀበለውም ፥ ስለዚህም ቃሉን በኮከብ አመልክተነዋል ) ።

ለመዳን የሚፈቅድ ሰው ሁሉ ይህን በሁሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሃይማኖት መጠበቅ ይገባዋል ።

ይህን ሃይማኖት ፍጹምና ያለ ርኩሰት አድርጎ የማይጠብቅ ቢኖር ያለ ጥርጥር ለዘለዓለም ይጠፋል ።

በሁሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ማለት አካላትን ሳንደባልቅና ህላዌን ሳንከፍል አንዱን አምላክ በሦስትነት ሦስትነትንም በአንድነት እናመልካለን ማለት ነው ።

አንዱ አካል የአብ ሲሆን ሁለተኛው የወልድ ሦስተኛውም የመንፈስ ቅዱስ ነው ።

ነገር ግን የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንዲት ናት ።

ክብራቸውም የተካከለ ነው ። ግርማቸውም የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናት ።

አብ እንደሆነ እንዲሁም ወልድ ነው ፥ መንፈስ ቅዱስም ነው። አብ አልተፈጠረም ወልድ አልተፈጠረም መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም ።

አብ አይወሰንም ወልድም አይወሰንም መንፈስ ቅዱስም አይወሰንም ። አብ ዘለዓለማዊ ነው ፥ ወልድም ዘለዓለማዊ ነው ፥ መን



ፈስ ቅዱስም ዘለዓለማዊ ነው ። ነገር ግን በዘለዓለማዊነት አንድ ነው እንጂ ሦስት አይደሉም ።

እንዲሁም የማንወስነውና ያልተፈጠረ አንድ ነው እንጂ የማንወስናቸውና ያልተፈጠሩ ሦስት አይደሉም ።

እንደዚሁም አብ ሁሉን ቻይ ነው ፥ ወልድም ሁሉን ቻይ ነው ፥ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን ቻይ ነው ። ነገር ግን ሁሉን የሚችል አንድ ነው እንጂ ሦስት ሁሉን ቻዮች አይደሉም ።

እንደዚሁም አብ አምላክ ነው ፥ ወልድም አምላክ ነው ፥ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው ። ነገር ግን አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም ።

እንደዚሁም አብ ጌታ ነው ፥ ወልድም ጌታ ነው ፥ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው ። ስለሆነም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይደሉም ።

በክርስትና እውነትነት እንደምንለው እያንዳንዱ አካል በየራሱ አምላክና ጌታ ሆኖ ሳለ ፤ ሦስት አማልክትና ሦስት ጌቶች ከማለት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ትከለክለናለች ።

አብ ከማንም አልተሠራም ፥ አልተፈጠረም ፥ አልተወለደም ፤ ወልድም ከአብ ብቻ ነው ፤ ስለሆነም ተወልዶ እንጂ ተሠርቶ ወይም ተፈጥሮ አይደለም ።

* መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ነው ። ነገር ግን ሠርፆ እንጂ ተሠርቶ ወይም ተፈጥሮ ወይም ተወልዶ አይደለም ። *

እንግዲህ አንድ አብ አለ እንጂ ሦስት አባቶች የሉም ። አንድ ልጅ አለ እንጂ ሦስት ልጆች የሉም ። አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ እንጂ ሦስት መንፈስ ቅዱሶች የሉም ። በዚችም ሦስትነት መቅደም መከታተል የለም ፤ ከባልንጀራውም የሚበልጥና የሚያንስ የለም ።

ሦስቱ አካላት እየራሳቸው የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናቸው ። እየራሳቸውም የተተካከሉ ናቸው ። እንግዲያውስ እንደ ተባለው ሁሉ ሥላሴን በአንድነት ፥ አንድነትንም በሥላሴ ማምለክ ይገባል ።

www.ethiopianorthodox.org

መዳንን የሚሻ በሥላሴ እንደዚሁ ያስብ ።

ዳግም ስለ ዘለዓለም ሕይወቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትሥጉት በሚገባ እንዲያምን ለሰው ያስፈልገዋል ።

የቀናው ሃይማኖት ማለት ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና ሰው እንደሆነ ማመናችን ማለት ነው ።

እምቅድመ ዓለም ከአብ ሀላዌ በመወለዱ አምላክ ነው ፤ ድኅረ ዓለምም ከእናቱ ሀላዌ በመወለዱ ሰው ነው ።

በለባዊ ነፍስና በሰው ሥጋ ሆኖ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው ።

በመለኮቱም ከአብ ጋር ትክክል ሲሆን ፣ በሰውነቱም ከአብ አነሰ ። ነገር ግን አምላክና ሰው እንደ መሆኑ አንድ ክርስቶስ ነው እንጂ እርሱ ሁለት አይደለም ። አንድ ነው ፤ ግን መለኮቱ ሰውነትን በመገንዘብ ነው እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ በመለወጥ አይደለም ።

ፈጽሞ ተዋሐደ ፤ ስለሆነ በባሕርይ መደባለቅ ሳይሆን ፣ በአካል መዋሐድ ነው ።

ነፍስ ሥጋ አንድ ሰው እንደሚያሰኙ ሁሉ ፣ አምላክና ሰው የሆነ አንድ ክርስቶስ ነው ።

እርሱም እኛን ለማዳን መከራን ተቀበለ ፣ ወደ ሲኦልም ወረደ ። በሦስተኛም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ።

ወደ ሰማይም ዐረገ ።

ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ ።

በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ ከዚያ ይመለሳል ።

እርሱም በሚመጣበት ጊዜ ሰው ሁሉ በሥጋው ይነሣል ። ባደረገውም ሥራ ሁሉ ይቈጣጠረዋል ።

መልካም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ፣ ክፉ የሠሩም ወደ ዘለዓለም እሳት ይገባሉ ።

ከሁሉ በላይ የምትሆን የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ይህች ናት ፤ ያላመናት ሰው ሊድን አይችልም ።

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ፤ በመጀመሪያ እንደ ነበረ ፣ አሁንም እንዳለ ፣ ለዘወትርም እንደሚኖር ለዘለዓለም ፤ አሜን ።

ምዕራፍ ፲ ።

## የአፄ ገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ ።

አፄ ገላውዴዎስ ከ፲፭፻፴—፲፭፻፶፪ ዓ. ም. የነገሡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ናቸው ። በእርሳቸው ዘመን ኢየሱሳውያን የተባሉ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሚሲዮናውያን (ሰባኪዎች) ወደ ኢትዮጵያ ተልከው የሃይማኖት ክርክርን ስላሞቁ ፣ አፄ ገላውዴዎስ የኦርቶዶክስ ሃይማኖታችን እንዲህ ነውና አንተወውም ብለው የሚከተለውን መልስና ውሳኔ አዘጋጅተው ሰጡአቸው ።

ኢየሱሳውያን ሃይማኖታችሁ አይሁዳዊ ነው ስላሉ አፄ ገላውዴዎስ የግዝረት ፣ የመብል ፣ የሰንበት ነገር የአይሁድን ሥርዓት ይመስላል ፤ ሆኖም በሰውም በአገርም ልማድ እንጂ እንደ አይሁድ ሆነን በኦሪት እየተገደድን የምናደርጋቸው አይደለንም ብለው መለሱላቸው ።

« በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ።

ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ ፣ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥት እስራኤላውያን ፣ ወሃይማኖተ መርዔትየ እለ ሀለዉ በዐፀደ መንግሥትየ ።

ንሕነ ነአምን በአሐዱ አምላክ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ውእቱ ቃሉ ፣ ወውእቱ ኃይሉ ፣ ውእቱ ምክሩ ፣ ወውእቱ ጥበቡ። ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ፤ ወበደኃሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየዐርቅ እመንበረ መለኮቱ ። ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ። ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በሠላሳ ክረምት ወኮነ ብእሴ ፍጹመ ። ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ። ሐመ ፣ ወሞተ ፣ ወተቀብረ ፣ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት ። ወእምዝ በዓርብዓ ዕለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ ። ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ፣ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ።

ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ፣ እግዚእ ማሕየዊ ፣ ዘሠረፀ እምአብ።

ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ። ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ለሕይወት ዘይመጽእ ለዓለም ፤ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዩሕ እማናዊ ። ወኢናጸንን ኢለየማን ወኢለፀጋም እምትምህርተ አበዊነ ፤

እሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት ፥
ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ፥
ወሰብአ ወክልኤቱ አርድእት ፥
ወሠለስቱ ምዕት እሠርቱ ወሰመንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ዘተጋብኡ በኒቅያ ፥
ወምዕት ወሃምሳ በቍስጥንጥንያ ፥
ወክልኤቱ ምዕት በኤፌሶን ።

ከመዝ እሰብክ ፥ ወከመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ ።

ወበእንተ ምክንያተ አከብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አኮ ዘናከብራ ከመ አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ ። እስመ እሙንቱሰ አይሁድ ኢይቀድሑ ማየ ፤ ወኢያነድዱ እሳተ ፥ ወኢያበስሉ ጸብሐ ፥ ወኢየኀበዙ ኅብስተ፥ ወኢይትፋለሱ እምቤት ውስተ ቤት ።

ወባሕቱ ንሕነሰ ናከብራ እንዘ ናዐርግ ባቲ ቍርባነ ፥ ወንገብር ባቲ ምሳሐ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ ። አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ እሑድ ፥ እንተ ይእቲ ዕለት ሐዳስ ፤ ዘይቤ ዳዊት በእንቲአሃ ፥ ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ፥ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ ። እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ። ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ። ወባቲ ይመጽእ ዳግመ ለዕሴተ ጻድቃን ወለፍዳ ኃጥኣን ።

ወበእንተ ሥርዓተ ግዝረትኒ አኮ ዘንትገዘር ከመ አይሁድ ። እስመ ንሕነ ናአምር ቃለ ምህሮሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ፥ ዘይቤ ፥ ተገዝሮሂ ኢይበቍዕ ወኢተገዝሮሂ ኢያሰልጥ ፥ ዘእንበለ ዳዕሙ ሐዳስ ፍጥረት ዝ ውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ ፥ ዘሂ ነሥአ ግዝረተ ኢይንሣእ ቍልፈተ ። ኵሉ መጽሐፈ ትምህርቱ ለጳውሎስ ሀለወ በኀቤነ ፤ ወይሜህረነ በእንተ ግዝረት ወበእንተ ቍልፈት ። ወባሕቱ ግዝረትሰ



ዘኮነ በኀቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥሐተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወኖባ ፥ ወከመ ስቍረተ ዕዝን ዘሰብአ ሕንድ ። ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በዐቂበ ሕገገ ኦሪት ዳዕሙ በልማደ ሰብእ ።

ወበእንተ በሊዐ ሐራውያኒ አኮ ዘንትከላእ በዐቂበ ሕገገ ኦሪት ከመ አይሁድ ። ለዘኒ በልዐ ኢናስቈርሮ ወኢናረኵሶ ፤ ወለዘኒ ኢበልዐ ከመ ይብላዕ ኢናጌብሮ ። በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል ፥ ዘኒ በልዐ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ ፥ ወለኵሎሙ እግዚአብሔር ተወከፎሙ ። መንግሥተ እግዚአብሔርሰ ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ ። ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን ፤ ወእኩይሰ ለሰብእ በሊዐ ምስለ ዕቅፍት ። ወማቴዎስ ወንጌላዊ ይቤ ፥ አልቦ ዘይክል አርኵሶቶ ለሰብእ ዘእንበለ ዘይወፅእ እምአፉሁ ። ወዘሰ ውስተ ከርሥ ይበውእ ፥ ወይትገመር ጽመ ፥ ወይትገደፍ ፥ ወይትከዐው ። ወያነጽሕ ኵሎ መባልዕተ ። ወብሂለ ዝንቱ ቃሉ ነሠተ ኵሎ ሕንፃ ስሕተቶሙ ለአይሁድ እለ ተምህሩ እመጽሐፈ ኦሪት ።

ሊተሰ ሃይማኖትየ ፥ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለ ይሜህሩ በትእዛዝየ በዐፀደ መንግሥትየ ። ወኢይትገሐሡ እምፍኖተ ወንጌል ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማን ወኢለፀጋም ።

ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሎ በመጽሐፈ ዚአነ ፥ እስመ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ አዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለኵሎሙ እለ ተጠምቁ አይሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ወባሕቱ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ እንስሳ ። ቦ ዘያፈቅር ሥጋ ዓሣ ፥ ወቦ ዘያፈቅር በሊዐ ሥጋ ዶርሆ ፥ ወቦ ዘይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ በግዕ ፤ ወኵሎ ዘከመ አደሞ ልቡ ይተሉ ፥ ከመዝ ውእቱ ሥምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ ። በእንተ መብልዐ ሥጋ እንስሳ አልቦ ሕግ ፥ ወአልቦ ቀኖና ውስተ መጽሐፍ ሐዳስ ። ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን ። ወጳውሎስኒ ፥ ዘሰ የአምን ኵሎ ለይብላዕ ።

ዘንተ ኵሎ ጽሕቀ ለጽሒፍ ከመ ታእምር ጽድቀ ሃይማኖትየ ። ተጽሕፈ በዐሠርቱ ወሃምስቱ ምዕት በሃምሳ ወሃምስቱ ዓመት እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ እመ እሥራ ወሠሉሱ ለሰኔ በሀገረ ዳሞት ። »

www.ethiopianorthodox.org

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ፥ በአንድ አምላክ ስም ።

ሃይማኖቴና የእስራኤላውያን ነገሥታት የአባቶቼ ሃይማኖት ፥ በመንግሥቴም በረት ውስጥ ያለው የመንጋዬ ሃይማኖት ይህ ነው ።

እኛ በአንድ አምላክና የእርሱ ቃል ፥ ኃይሉ ፥ ምክሩ ፥ ጥበቡም በሆነ ፥ ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ዘንድ በነበረ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። እርሱም ከአምላክነቱ መኖሪያ ተለይቶ ሳይቀር በኋለኛው ዘመን ወደ እኛ መጣ ። ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ከማርያም ሰው ሆነ ። በሠላሳኛው ዓመት በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፤ ፍጹም ሰው ሆነ ። በጰንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ ። መከራን ተቀበለ ፥ ሞተ ፥ ተቀበረ ፥ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ ።

ከዓርባ ቀን በኋላ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ። በሕያዋንና በሙታን እንዲፈርድ ዳግመኛ በክብር ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።

ከአብ በሠረፀ ፥ ሕያው በሚያደርግ ጌታ ፥ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።

ለኃጢአት ሥርየት በምትሆን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።

ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚነሡበትን የሙታንን ትንሣኤ በተስፋ እንጠባበቃለን ፤ አሜን ።

እኛስ ቅንና እውነተኛ በሆነ በንጉሣዊ መንገድ እንመላለሳለን ። ከአባቶቻችን ትምህርት ወደ ቀኝ ሆነ ወደ ግራ ዘንበል አንልም ። አባቶቻችንም ፥

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፥
የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ፥
ሰባ ሁለቱ አርድእት ፥
በኒቅያ የተሰበሰቡ ፥ የቀናውን ሃይማኖት የያዙ ሦስት መቶ
አሥራ ስምንቱ ፥

በቍስጥንጥንያ የነበሩ መቶ ሃምሳው ፥
በኤፌሶን የነበሩ ሁለት መቶው ናቸው ።

በንግሥ ስሜ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ ተብዬ የተጠራሁ እኔ ገላውዴዎስ የኢትዮጵያ ንጉሥ እንዲህ ብዬ እሰብካለሁ ፤ እንዲሁም ብዬ አስተምራለሁ ።



ሰንበት የተባለውን መጀመሪያ ቀን ስለ ማክበራችን « ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» (ማቴ. ፳፯ ፡ ቍ. ፳፭) ብለው ክርስቶስን እንደ ሰቀሉት አይሁድ አናከብረውም ። እነዚያ አይሁድ፤ ውኃን አይቀዱም ፥ እሳትን አያነዱም ፥ ወጥን አያበስሉም ፥ ዳቦን አይጋግሩም ፥ ከቤት ወደ ቤት አይመላለሱም ።

ነገር ግን አባቶቻችን ሐዋርያት በመጽሐፈ ዲድስቅልያ እንዳዘዙን እኛ ቍርባንን ስናቀርብበትና ሰንበቴን ስናደርግበት እናከብረዋለን ። እንደ ሳምንት መጀመሪያ ቀን አናከብረውም ፥ አዲስ ቀን ነውና ዳዊት ፥ « እግዚአብሔር የሠራው ቀን ይህ ነው ፤ በእርሱ ደስ ይበለን ፥ ሐሴትን እናድርግ » ብሎ ስለ እርሱ ተናገረ (መዝ. ፻፲፯ ቍ. ፳፬) ። በዚህ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሣ ። በዚህ ቀን በኢየሩሳሌም በቤት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወረደ ። በዚህም ቀን ዘወትር ድንግል በሆነች በቅድስት ማርያም ማሕፀን ውስጥ ሰው ሆነ ። በዚህ ቀን የጻድቃንን ዋጋ ለመስጠትና ኃጥአንን ለመቅጣት ዳግመኛ ይመጣልና ስለዚህ ነው ።

ስለ ግዝረት ሥርዓት እንደ አይሁድ አንገዘርም ። እኛ የጥበብ ምንጭ የሆነውን የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና ፤

« በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን የሆነ አዲስ ፍጥረት እንጂ መገረዝ አይጠቅምም ፥ አለመገረዝ ፍጹም አያደርግም » አለ (ገላ. ፭ ፡ ቍ. ፮ ም. ፮ ቍ. ፲፭) ። ደግሞም ለቆሮንቶስ ሰዎች «ግዝረትን የተቀበለ ቍልፈትን አይያዝ» አለ (፩ ቆሮ. ፯ ፡ ቍ. ፲፰ ፥ ተገዛሪ ወደ አለመገረዝ አይመለስ) ። የጳውሎስ ትምህርት መጽሐፍ ሁሉ በእኛ ዘንድ አለና ስለ ግዝረት ፥ ስለ ቍልፈትም ያስተምረናል ። ነገር ግን የኢትዮጵያም የኖብያም ሰው ፊቱን እንደሚበጣና የህንድ ሰው ጆሮውን እንደሚበሳ በእኛ ዘንድ ግዝረት እንደ አገር ልማድ ነው። ይህንስ የምናደርገው በሰው ልማድ ነው እንጂ የኦሪትን ሕጎች በመጠበቅ አይደለም ።

አሳማን ስለ መብላት እንደ አይሁድ ሆነን የኦሪትን ሕጎች በመጠበቅ አንከለክለውም ። የበላውን አንጠየፈውም ፥ ርኩስ ሆኖ አናየውም ፤ የማይበላውን ብላ ብለን አናስገድደውም ። አባታችን ጳውሎስ ለሮሜ ሰው እንዲህ ብሎ ጻፈ ፦ « እግዚአብሔር ሁላቸውን ተቀብሎአቸዋልና የሚበላ የማይበላውን አይናቀው ፤ የእግዚ

www.ethiopianorthodox.org

እብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለም ። ለንጹሐች ሁሉ ንጹሕ ነው ፤ በመሰነካከል መብላት ግን ለሰው ክፉ ነው » (ሮሜ. ፲፬ ቍ. ፫ ፲፯ ቲቶ. ፩ ቍ. ፲፭ ፩ ቆሮ. ፰ ቍ. ፱—፲፫) ። ደግሞም ማቴዎስ ወንጌላዊ እንዲህ አለ ፥ « ከአፍ ከሚወጣ ነገር በቀር ሰውን ማርከስ የሚችል የለም ። በአፍ ውስጥ ያለው ወደ ሆድ ይገባል ፥ በፀጥታ ይከታተል ፥ ይወድቃልና ይፈስሳል » (ማቴ. ፲፭ ፥ ቍ. ፲፩ ፲፯) ። መብልንም ሁሉ አነጻው (ማር. ፯ ቍ. ፲፭) ። ይህን ቃል በመንገሩ አይሁድ ከመጽሐፈ ኦሪት የተማሩትን የስሕተታቸውን ሕንፃ አፈረሰው ።

ይህ የእኔ ሃይማኖትና በመንግሥቴ በረት ውስጥ በትእዛዜ የሚያስተምሩ የተማሩ ካህናት ሃይማኖት ነው ። ከወንጌል መንገ. ድና ከአባታችን ከጳውሎስ ትምህርት ወደ ቀኝ ሆነ ወደ ግራ ፈቀቅ አይሉም ።

በመጽሐፈ ታሪክ በመጽሐፋችን ውስጥ እንዲህ ሲል የተጻፈ አለ ፤ « የተጠመቁ አይሁድ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በዓል የአሳማን ሥጋ እንዲበሉት ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ በዘመነ መንግሥቱ አዘዘ ። »

ነገር ግን ሰው እንደ ልቡ አምሮት የእንስሳን ሥጋ ከመብላት ይለያል ። የዓሣን ሥጋ የሚወድ አለ ፥ የዶሮ ሥጋን መብላት የሚወድ አለ ፥ የበግ ሥጋን ከመብላት የሚለይ አለ ። የሰው ውዴታና ፈቃድ እንደዚህ ነውና እንደ ልቡ አምሮት የሆነውን ሁሉ ይከተል ። የእንስሳን ሥጋ ስለ መብላት ሕግ የለም ። በአዲስ መጽሐፍም ውስጥ ትእዛዝ የለም ። ለንጹሐች ሁሉ ንጹሕ ነው ። ጳውሎስም « የሚያምን ሁሉን ይብላ » አለ (ሮሜ ፲፬ ቍ. ፳፪—፳፫) ።

የሃይማኖቴን እውነተኛነት እንድታውቅ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ተጋሁ ። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በ፩ሺ፶፻፹፱፻፭ ዓመት በሰኔ ፳፫ ቀን በሀገረ ዳሞት ተጻፈ ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

## የቅዱሳት መጻሕፍት ቍጥር ፤

የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ውሳኔዎች በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። እነዚህ መጻሕፍት እግዚአብሔር አስቀድሞ ቅዱስ ምንጭ ያደረጋቸው ናቸውና ፤ የኋላ መንፈሳዊ ድርሰት ሁሉ ከእነዚህ የተውጣጣ ነው ። ስለ ቍጥራቸውም የኢ. ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፹፩ መጻሕፍትን ተቀብሎአል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፪) ፤ በታችም ተዘርዝረዋል ። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የማይቀበሉአቸው በቅንፍ የተከለሉ ናቸው።

### ብሉያት ።

፩ ኦሪት ዘፍጥረት
፪ » ዘጸአት
፫ » ዘሌዋውያን
፬ » ዘኍልቍ
፭ » ዘዳግም
፮ ኢያሱ
፯ መሳፍንት
፰ ሩት
፱ ሳሙኤል ፥ ፩ኛና ፥ ፪ኛ ፤
፲ ነገሥት ፥ ፩ኛና ፪ኛ ፤
፲፩ ዜና መዋዕል ፩ኛ
፲፪ ዜና መዋዕል ፪ኛ ፥ ዕዝራ ፥ ነህምያ
፲፫ ( ኩፋሌ)
፲፬ ( ሄኖክ)
፲፭ ( ዕዝራ ሱቱኤል)
፲፮ ( ዕዝራ ካልእ )
፲፯ ( ጦቢት)

www.ethiopianorthodox.org

## ብ ሉ ያ ት ።

፲፰ ( ዮዲት)
፲፱ ( አስቴር)
፳ ( ፩ኛ መቃብያንም ዘብንያምና)
፳፩ ( ፪ኛ መቃብያን ዘሞዓብ ፤ ፫ኛ መቃብያን ዘአልዓዛር )
፳፪ ( ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን )
፳፫ ኢዮብ
፳፬ ዳዊት
፳፭ ምሳሌ
፳፮ ተግሣጽ
፳፯ ( ጥበብ )
፳፰ መክብብ
፳፱ መኀልየ መኀልይ
፴ ( ሲራክ )
፴፩ ኢሳይያስ
፴፪ ኤርምያስ ( ባሮክ) ሰቆቃው ( ተረፈ ባሮክ )
፴፫ ሕዝቅኤል
፴፬ ዳንኤል
፴፭ ሆሴዕ
፴፮ አሞጽ
፴፯ ሚክያስ
፴፰ ኢዩኤል
፴፱ ደቂቀ አብድዩ
፵ ነቢያት ዮናስ
፵፩ ናሆም
፵፪ ዕንባቆም
፵፫ ሶፎንያስ
፵፬ ሐጌ
፵፭ ዘካርያስ
፵፮ ሚልክያስ



## ሐ ዲ ሳ ት ።

፵፯ ወንጌል ማቴዎስ
፵፰ » ማርቆስ
፵፱ » ሉቃስ
፶ » ዮሐንስ
፶፩ የሐዋርያት ሥራ
፶፪ ሮሜ
፶፫ ቆሮንቶስ ፩ኛ
፶፬ ቆሮንቶስ ፪ኛ
፶፭ ገላትያ
፶፮ ኤፌሶን
፶፯ የጳውሎስ ፊልጵስዩስ
፶፰ መልእክታት ቈላስይስ
፶፱ ተሰሎንቄ ፩ኛ
፷ ተሰሎንቄ ፪ኛ
፷፩ ጢሞቴዎስ ፩ኛ
፷፪ ጢሞቴዎስ ፪ኛ
፷፫ ቲቶ
፷፬ ፊልሞና
፷፭ ዕብራውያን
፷፮ የጴጥሮስ ፩ኛ
፷፯ የጴጥሮስ ፪ኛ
፷፰ የሐዋርያት የዮሐንስ ፩ኛ
፷፱ መልእክታት የዮሐንስ ፪ኛ
፸ የዮሐንስ ፫ኛ
፸፩ የያዕቆብ
፸፪ የይሁዳ
፸፫ የዮሐንስ ራእይ
፸፬ ( ሥርዓተ ጽዮን )
፸፭ (ሲኖዶስ) ( አብጥሊስ )
( ግጽው )

www.ethiopianorthodox.org

## ሐ ዲ ሳ ት ።

፸፯ ( ትእዛዝ )
፸፰ ( ሁለቱ መጽሐፈ ኪዳን )
፸፱ »
፹ ( ቀሌምንጦስ )
፹፩ ( ዲድስቅልያ )

የእነዚህ መጻሕፍት ብልጫ ምንድር ነው ፥ በምን ተለይተዋል ? ሊቃውንት « የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል » የሚለውን የጳውሎስን ቃልና « ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ » የሚለውን የጴጥሮስን ቃል ተገንዝበው ፥ ቃለ እግዚአብሔር መባል የሚገባቸው መጻሕፍት እግዚአብሔር ራሱ ተንፍሶ ያስጻፋቸው ናቸው እንጂ ደግነታቸውና መጥፎነታቸው ከተመዛዘነ በኋላ መልካም ሆነው የተገኙ አይደሉም ብለዋል ( ፩ ጢሞ· ፫ ቍ· ፲፮ ፪ ጴጥ· ፩ ቍ· ፳፩ ፩ ጴጥ· ፩ ቍ· ፲-፲፪) ።

እንዲህ ከሆነ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ስለ ቍጥሩ ለምን አይስማሙም ? ምክንያቱ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጣ ነው ። የአይሁድ መምህራን ብሉያትን ቈጥረው ፴፱ኙን ተቀበሉአቸው ፥ እነ ጦቢት ፥ እነ ባሮክ ፥ የዕብራይስጥ ጥንት የላቸውም ብለው ከቍጥሩ ውጭ አደረጉአቸው ። ክርስቲያኖች ሁሉ እነዚህን ፴፱ ብሉያት ተቀብለዋቸዋል ፤ እነጦቢት በግሪክ ተጽፈው በብዙ አገሮች በተበታተኑ አይሁድ እጅ ሆነው ሲነበቡ ስለ ተገኙ ክክርስቲያኖች አንዱ ወገን ጨምሮ ተቀበላቸው ፤ ሌሎችም ቢነበቡ አይከፉም ፥ ሆኖም ከቃለ እግዚአብሔር ጋር አናስተካክላቸውም አሉ ።

ከሐዲሳትም ሐዋርያት የጻፉአቸውንና ያስጻፉአቸውን እንቀበላለን ብለው በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ ያሉ ፳፯ መጻሕፍትን



ተቀበሉ ። በአንዳንድ ሌሎች መጻሕፍት ፥ ሐዋርያት አልጻፉአቸውም አላስጻፉአቸውምም እያሉ ሊቃውንት ስላልተስማሙባቸው ከቍጥሩ ውጭ ሆኑ ። በኢትዮጵያ ግን ሲኖዶስ ፥ መጽሐፈ ኪዳን ፥ ቀሌምንጦስ ፥ ዲድስቅልያ ፥ ቃለ ሐዋርያት ናቸው ተብለው ታውቀዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፲፪ ።

# የቤተ ክርስቲያን አንድነት ።

ቤተ ክርስቲያን ማለት በአንድ ሥፍራ ያሉ ምእመናን ማለት ነው ፤ ( ፩ ፣ ቆሮ. ፩ ቀ. ፪ ) ። ደግሞ በዓለም ሁሉ ያሉ ምእመናን ማለት ነው ( ፩ ፣ ቆሮ. ፲ ቀ. ፴፪) ። ደግሞም የሞቱ ፣ ዛሬ ያሉ ፣ ያልተወለዱም የምእመናን ማኅበር ማለት ነው (ኤፌ. ፩፣ ቀ. ፳፪-፳፫)። ትርጕሙ እምብዛም ወደ ሰው እንጂ ወደ ሕንፃ አይደለም ፤ የጥንት ምእመናን የሰውን ቤት መሰብሰቢያቸው ሲያደርጉ ነበርና ፤ (ሮሜ ፲፮ ፣ ቀ. ፭ ) ።

ሊቃውንት እንደሚከተለው ተርጕመውታል ፥-

« የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሥላሴ የተጠመቁ ፣ ከኃጢአት ከግፍ ፣ ከክፉ ነገር ሁሉ የራቁ ፣ በሕገ ወንጌል ሥርዓት በአምልኮተ እግዚአብሔር የተጠመቁ፣ እግዚአብሔር በመንፈስ በልባቸው የሚያድርባቸው፣ እንደወንድማማች በፍቅር በሰላም አንድነት እርስ በርሳቸው ተስማምተው የሚኖሩ ምእመናን ናቸው ( ኤፌ. ፪ ቀ. ፲፱—፳፪ ፣ ፩ ቆሮ. ፫ ቀ. ፱—፲፯ ፣ ዕብራ. ፫ ቀ. ፭—፯) ።

የያዕቆብ ልጆች በአባታቸው ስም ቤተ እስራኤል እንደ ተባሉ ፣ እንዲሁም የክርስቶስ ወገኖች ምእመናን በክርስቶስ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ተባሉ ።

ከዕንጨት ከድንጋይ ከጭቃ ከኖራ የተሠራች ቤተ ክርስቲያንም ምእመናን ለአምልኮተ እግዚአብሔር የሚሰበሰቡባት ፣ የጉባኤ ጸሎት የሚያደርጉባት ቅዱስ ቃሉን የሚሰሙባት ፣ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉባት ፣ የእግዚአብሔርን ስም የሚያመሰግኑባት ስለሆነች ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያን ቤት ትባላለች ።»

ምእመናን አንድ አካል ናቸው ፤ ሃይማኖታቸው አንድ ነው (ኤፌ. ፬ ቀ. ፩- ፯) ። ወገናቸው ፣ ቋንቋቸው ፣ ባህላቸው ብዙ ነው ፤ ሆኖም ወገናቸውን ፣ ቋንቋቸውን ፣ ባህላቸውንም ምክንያት አድርገው ቢጣሉ አንድነታቸው ይፈርሳል (ዮሐ. ፲፯ ቀ. ፳፪- ፳፫) ። ሰው የተሳሳተውን ወንድም መምከር አለበት (ማቴ. ፲፰ ቀ. ፲፭- ፳) ፤ ነገር ግን ከምቀኝነት ፣ ከማይገባ ክርክር ፣ ሰውንም በከንቱ ከመንቀፍ ይራቅ ።



ክርስቲያኖች ሁሉ የኒቅያን ሃይማኖት ይቀበሉታል ። በሌላ ነገር ግን በብዙ ይለያያሉ ፣ ይጣላሉ ፣ መለያየታቸውንና መጣላታቸውን ለማሳነስ ፣ በአንድነት መኖር የሚገባቸውን ምእመናን ለማስታረቅ የተደረገ ጥረት አለን ?

በጥር ፯- ፲፫ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በአዲስ አበባ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ አደረጉ ። እነዚህም የኢትዮጵያ ፣ የግብጽ ፣ የአንጾኪያ ፣ የአርመን ፣ የህንድ አብያተ ክርስቲያን ማለት ናቸው ። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት የሚከተለውን መግለጫ ሰጡ ።

## « ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር የምናደርገው ግንኙነት ።

### ሀ) መግቢያ ፤

፩ በአሁኑ ዘመናችን ጥንት የነበረው የክርስቲያን አንድነት ዛሬም እንዲኖር ታላቅ ፍላጎት መኖሩን ስንመለከት በጣም ደስ ይለናል ። በዚህም መንፈስ ከልባችን እናብራለን ። እግዚአብሔርም የሰው ልጅ ሁሉ በአንዲትዋ በራሱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ አንድ እንዲሆን ፈቅዶአል ። ይሁን እንጂ በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ዛሬ በብዙ ክፍል እየተከፋፈሉ ሄደዋል ። ይህም በጣም ያሳዝናል ። ስለዚህ ከእነዚህ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የምናደርገው ግንኙነት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ማጥናት ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል ።

እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት በሦስት ትልልቅ ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ ፤ ማለት ፣

ኬልቄዶናውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፣

የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ፤

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውስጥ ያሉ ኦርቶዶክስ ያልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ( ፕሮቴስታንቶች ) ።

### ለ) እኛና ኬልቄዶናውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፤

፪ ምንም መሠረታዊ ምኞታችን መላው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጥንት የነበረውን የክርስትናን አንድነት እንዲያድሱ ቢሆንም ፣ ከኬልቄዶናውያን ኦርቶዶክሶች ጋር የእምነትና የመንፈሳዊ

www.ethiopianorthodox.org

ኑሮ መቀራረብ ስላለን ፤ ከሌሎች ይልቅ ከእነርሱ ጋር የተለየ መቅራረብ ማድረግ አለብን ። እንግዲህ ከኬልቄዶናውያን ኦርቶዶክሶች ጋር የምናደርገው መቀራረብ ከሁሉም ቀደምትነት አለው ። የኬልቄዶን ጉባኤ እስከተደረገበት እስከ ፬፻ ፶፫ ዓ. ም. ድረስ ከኬልቄዶን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር አንድ እምነት ነበረን ፤ ከዚህ በኋላ መለያየት መጣ ።

፫ መለያየት ስለ ተነሣበት ስለ ነገረ ሥጋዌ ፥ በመግባባት መንፈስ የጋራ ጥናት ቢደረግ የእያንዳንዳችንን የእምነት አስተያየት በደንብ ልናውቅ እንድንችል ተስፋ እናደርጋለን ። ስለዚህ ይህ የነገረ ሥጋዌ ጥያቄ ፥ ታሪካዊ መልኩን ሳይለቅቅ አዲስ ጥናት በሊቃውንቶቻችን እንዲደረግ በይፋ ወስነናል ። ይህም ጥናት ሲደረግ ስለ ዚሁ ጉዳይ ቀደም ብሎና አሁን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አማካይነት በይፋ ሳይሆን የተደረጉትን ውይይቶችና ጥናቶች ማስታወስ ተገቢ ነው ። ይህ እስኪሆን ድረስ ግን አብያተ ክርስቲያናታችን ከላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በጣም የቀረበ ግንኙነትንና የሥራ መረዳዳት እንዲያደርጉ ተስማምተናል ።

## ሐ) እኛና የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ።

፩ የኬልቄዶን ጉባኤ እስከሆነበት እስከ ፬፻፶፫ ዓ. ም. ድረስ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድነት ነበረን ፤ ከዚህ በኋላ ግን መለያየት መጣ ። ዛሬ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት በተለይም የኦርቶዶክስን አብያተ ክርስቲያናት እንደ አብያተ ክርስቲያናት አድርጋ መቍጠር አስፈላጊዋ ሆኖ ማግኘትዋ አስደሳች ነገር ነው ። በዚህም አዲስ መንፈስ መሠረት የቀረበ መግባባት እንዲገኝ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር አሳብ በአሳብ ለመለዋወጥ የተዘጋጀን መሆን አለብን ። የምናደርገውም ግንኙነትና ንግግር በእኩልነት ደረጃ መሆን አለበት ። በዚህም ነገር የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተተከለበት አገር ውስጥ ኦርቶዶክስን እየመሰሉ የሮም ሥርዓትን የሚከተሉትን አብያተ ክርስቲያናት ስለማቋቋምና የአብያተ ክርስቲያናቶቻችንን አባሎች ስለመንጠቅ ያላትን አስተያየት እንድትለውጥ መጠየቅ አለብን ።



፪ ኬልቄዶናውያን አብያተ ክርስቲያናትም ከሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነትና ንግግር ለማድረግ መፍቀዳቸው ሲታወስ የሚያስደስት ነው ። እኛም ከእነርሱ ጋር በመተባበር ይህን መሥመር ለመከተል ይቻለን ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

## እኛና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባሎች የሆኑት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ፤

፩ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አማካይነት ኦርቶዶክስ ካልሆኑት ከማኅበሩ አባሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት አለን ። በተቻለ መጠን በመካከላችን እውነተኛ መግባባትና መረዳዳት እንዲኖረን እግዚአብሔር መንገዱን እንዲከፍትልን እንለምናለን ። ከእነዚህም አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጥንታዊት ካቶሊክ የምትባለው ቤተ ክርስቲያንና የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በልዩ አስተያየት መታየት አለባቸው ። ለምሳሌ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ስለምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ያላትን ከፍተኛ አስተያየትና ፍቅር ብዙ ጊዜ ገልጣለች ። ይህም ሁናቴ በዚህች ቤተ ክርስቲያንና በእኛ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጠቃሚ ውጤትን የሚያስገኝ ንግግርን ለማድረግ የሚያነሣሣ ይሆናል ብለን እናምናለን ። ደግሞም የእኛ አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባሎች ከሆኑት ጋር ግንኙነትን አድርገዋል ። በፊትም ሆነ ዛሬም አንዳንድ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የእኛን አብያተ ክርስቲያናት አባሎች ለመንጠቅ ከማባባላቸው የተነሣ በምናደርገው ግንኙነት አንዳንድ እንቅፋት ይገጥመናል ፤ ይህም በቶሎ እንደሚቆም ተስፋ እናደርጋለን ። የእኛን አብያተ ክርስቲያናትና የሌሎቹን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በዚሁ ድርጅት አማካይነት በአንድ ቦታ አገናኝቶ የወዳጅነት ግንኙነት እንድናደርግ የፈቀደ አምላክ እርሱ በፈለገው ጊዜና ለእርሱ በመሰለው አኳኋን አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ወዳጅነት እንዲጸናና ጥንት የነበረው የክርስትና አንድነት ይመለስ ዘንድ እንደሚረዳን ተስፋ እናደርጋለን ።

## በዓለም ስለ አብያተ ክርስቲያናት አንድ መሆን ስለሚደረገው ጥረት ።

፩ ነገራችንን ከማቆማችን በፊት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አማካይነት ስለ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ስለሚደረ

www.ethiopianorthodox.org

ገው ጥረት በጣም የተደሰትን መሆናችንን እንገልጻለን ። በድርጅቱ አማካይነት የተገኘው አዲስ የወዳጅነት የመግባባትና የመረዳዳት መንፈስ በድርጅቱ ውስጥ ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጠቃሚ ውጤትን እንደ ሰጠ የሚታመን ነው ።

፰ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተባብረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያገለግሉ የሚያስችላቸው ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የአንድነታቸው ፍላጎት ፀጥለጠ እንዲጸናና ሥራው እንዲቃናለት እንጸልያለን ። »

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ።

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ የነገረ ሥጋዌ ክርክር ክርስቲያኖችን እንዳፈራረቃቸው ተረድተናል ። በኋላም የመንፈስ ቅዱስ አሠራረፅ ክርክር በወገን በወገን ለያቸው ። ቈይቶም እነሉተር የሮም ቤተ ክርስቲያን ተሳስታለች ብለው ከተነሡ በኋላ ብዙዎች ተከተሉአቸው ፤ የእነሉተር ወገኖች ፕሮቴስታንቶች ተባሉ ። በተለይም የሮም መምህራን የሮም ጳጳስ አልስትም ብሎ ሲያውጅ ተሳሳችነት የለበትም ብለው ማስተማራቸው ከፕሮቴስታንቶችና ከኦርቶዶክስ ለይቶአቸዋል ። የሮም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በጥብቅ የተወሰነበት ጊዜ ትሬንቶ በተባለው በኢጣልያ ከተማ በተደረገው ጉባኤ ነው (፲፭፻ ፵፭—፲፭፻፷፫ ዓ. ም.) ። ፕሮቴስታንቶችም በበኩላቸው ደግሞ ሃይማኖታቸውን ወሰኑ ፤ ለምሳሌ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን «፴፱ አንቀጾች » በሚል ጽሑፍና የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን « የዌስትምንስቴር ውሳኔ» በሚል ጽሑፍ ትምህርታቸውን ወሰኑ ።

ሰዎች እውነቱን ለማወቅ ታገሉ ፤ ፍላጎታቸው ምንም ቢመስገን ወደ መጣላት አደረሳቸውና ሌሎች «ክርስቶስ አንድ ነው ፤ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ሆና መጽናት አለባትና ተመካከረን የቤተ ክርስቲያንን ወገኖች እናስታርቃቸው» አሉ ። በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. ኤድንባረ በተባለው በእስኮትላንድ ከተማ «የሃይማኖትና የሥርዓት ጉባኤ» ተደረገ ። ከ፻፳፫ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና እንደራሴዎች ተልከው ተሰበሰቡ ፤ እነዚህም ከፕሮቴስታንትና ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ነበሩ ። ጉባኤውም የሚከተለውን ውሳኔ ወሰነ ፡-



«ሰው በሆነ በእግዚአብሔር ቃል በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን አንድ ነን ። የቤተ ክርስቲያን ራስ ፤ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ነው ብለን ለእርሱ በመገዛታችን አንድ ነን ። ከሚስበን ከሌላ ነገር ሁሉ ለእርሱ መገዛታችን ቀደምትነት የያዘ ነው በማለታችን አንድ ነን ።

ይህ አንድነት በአሳባችን ሆነ በፈቃዳችን ስምምነት ላይ የተመሠረተ አይደለም ። መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው ፤ እርሱም ወደ እግዚአብሔር አብ እንዲያቀርበን ተወልዶ ተሰቅሎ የተነሣና በመንፈስ ቅዱስ በኩል በራሱ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የሚኖር ነው ። እግዚአብሔር ስለወደደንና ጸጋውን ስለሰጠን ፤ የተከበረውንም ወንጌሉን በዓለም ሁሉ አስተምረን እንድንመሰክር በእርሱ ስለተጠራን አንድ ነን ።

አንድነታችን የልብና የመንፈስ ነው ። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ የፈቀደውን ነገር በልዩ ልዩ አስተያየት ስለምናየው በእርሱ ባለው ኑሮአችን በአፍአዊው ሥርዓት ተለያይተናል ።

ጠልቀን ማስተዋላችን ግን በኢየሱስ ያለ እውነቱን በአንድ አስተሳሰብ ወደ መያዝ ይመራናል ብለን እናምናለን ።

መለያየታችን የክርስቶስን ፈቃድ የሚጥስ ነው ብለን በትሕትና እንናገራለን ፤ እግዚአብሔር ምሮን የምንለያይበትን ዘመን እንዲያሳጥርና በመንፈሱ በኩል ወደ አንድነት ሙላት እንዲመራን እንለምነዋለን ።

ባለፉት ዓመታት እንድንቀራረብ ስለ ተሳብን እናመሰግናለን ፤ ያልተቃና አሳብ ትክክል ተደርጎአል ፤ አለመግባባት ተወግዶአል፤ የጋራ መተሳሰብ ወደ ሆነ ዓላማችን በጥቂት ቢሆንም ስንኳ በእውነት ተራምደናል ።

በዚህ ጉባኤ ዘመን እግዚአብሔርን እያመሰገንን የእርሱ መንፈስ እርስ በእርሳችን የመማማርን ፈቃድ ሰጠን ፤ እውነቱን የበለጠውን አድርገን ለማየት አስቻለን ፤ መንፈሳዊም ኑሮአችንን አበለጸገ (አዳበረ) ።

በአንድነት ጸልየናል ፤ በአንድነት መዝሙርን ዘምረናል ፤ በአንድነት ሆነን አንድ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ አንብበናል ። ከመለያየታችን አጥር የሚያሻግር የጋራ የክርስቲያንን አስተያየትና አስ

www.ethiopianorthodox.org

ተሳሰብ በእያንዳንዳችን እናያለን ። እንግዲህ መለያየታችን የማያፈርሰው አንድነት እንዳለን አረጋግጠናል ።

የመንፈስና የዓላማችን አንድነት በሚታይ ነገር ተገልጦ ለዓለም መከሠት እንዳለበት ተረድተናል ፤ ሆኖም እንደምን ሆኖ ሊታይ እንደሚችል ገና አናውቅም ።

፭

የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለእግዚአብሔር መንግሥት ደከመው ያለ ማስመሰል የሚረዳዱበት ነገር ሁሉ ወደ በለጠው መግባባትና ወዳጅነት ይሰባቸዋል ብለን እናምናለን ። ከአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያሉ ክርስቲያን ወንድሞቻችን እንዲረዳዱ ፥ እየታገሡ የመለያየትን ምክንያት መርምረው እንዲያስወግዱ ፥ ከመለያየታችን የተነሣ በማያምኑ ሕዝቦች መካከል የወንጌልን መስፋፋት የሚገጥሙትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንዲፈልጉና ጌታችን ለራሱ ቤተ ክርስቲያን ይህን የመሰለ አንድነት ፈቅዶታል ብለን ወደምናምነው አንድነት እንደርስ ዘንድ ዘወትር እንዲጸልዩ እናሳስባቸዋለን ።
ክብር ለዘላለም ይሁንለት ። »

በምእመናን ዘንድ ይህን የመሰለ ፍላጎት ስለ ተሰማ በ፲፱፻፵ ዓ. ም. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በሆላንድ ከተማ በአምስተርዳም ተመሠረተ ። ጽሕፈት ቤቱ በጄኔባ ነውና አባሎች የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ከ፪፻፳፭ በላይ የሚቈጠሩ ናቸው ። ሥራውም በተለያዩት አብያተ ክርስቲያናት መካከልም የመግባባትንና የዕርቅን መንፈስ ለማነሣሣት ፤ ደግሞ የውይይትንና የጥናትን ጉባኤ ለማድረግ ነው ። መሠረታዊው ቃል የሚከተለው ነው ፦

«የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና መድኀኒት ነው ብለው እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ቃል የሚቀበሉትና ስለዚህ በአንድነት ሆነው አንድ እግዚአብሔርን ፥ አብንና ወልድን መንፈስ ቅዱስንም ፥ ለማክበር በጋራ ጥሪአቸው የተጠሩለትን ሥራ ለመፈጸም የሚጣጣሩ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ነው ። »

ይህ ቃል አነስተኛ ሆኖ ይታይ ይሆናል ፤ ሆኖም ጌታችን «ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም » አለ (ዮሐ. ፮ ቍ. ፴፯ ) ። እርሱ የሃይማኖታችን መሥራችና ፈጻሚ ነው



(ዕብራ. ፲፪ ቍ. ፩-፪ ) ። እርሱን የሚንቅ ግን ከሃይማኖት ውጭ ነው ( ዮሐ. ፲፬ ቍ. ፮ ) ።

ከምእመናን መካከል አንድ ባሕርይ ባዮችና ሁለት ባሕርይ ባዮች አሉ ። ኅብስትና ወይን ወደ ሥጋና ወደ ደም ይለወጣሉ የሚሉና አይለወጡም የሚሉ አሉ ። ምጽአት ከሺሁ ዓመት በኋላ ይሆናል የሚሉና ከፊት ይሆናል የሚሉ አሉ ። የአሳማን ሥጋ የሚበሉና የማይበሉ አሉ ። ምእመናን እውነቱንና ሐሰቱን ለይተው ማወቅና የተሳሳተውን ወንድም መምከር ይኖርባቸዋል ። ስርቆ አመንዝሮ ንሰሐ አልገባም የሚል ሰው ራሱን ከማኅበረ ምእመናን ለይቶታል ፤ ስለ ምግብ ፥ ስለ በዓላት ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ አሠራረፅ ሌላ አሳብ የሚያስብ ሰው ተሳስቶ ይሆናል ፥ ሆኖም ከሃይማኖት ውጭ ልናደርገው አይገባንም ። ከሃይማኖት ውጭ መሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ቢክድ ነው ።

« ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ ። የእምነታችንን ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ »

( ዕብራ. ፫ ቍ. ፩ ፥ ም. ፲፪ ቍ. ፩-፪ ) ።

www.ethiopianorthodox.org